

## የዐቢይ አንድ ዓመት ውጤት ሲገመገም

ፕ/ር መሣይ ከበደ (በተለይ ለግዮን)




## በተስፋችን ላይ ጽልመት የጋረደው የዘር ፖለቲከኞች ጩኸት!

ጋዜጠኛ መሳይ መኮንን

## የኢትዮጵያ ሚዲያ ከቁልቁለት ጉዞ ቀጥሎ...

## ትኩረት የተነፈገው ነፃ ፕሬስና ቀጣይ ተግዳሮቶቹ!



## ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ "ዕንቁላሉን ሰብረው የወጡ" ታማኙ ፕሬዝዳንት!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 2 ቁጥር 54 ሚያዚያ 2011 ዓ.ም ዋጋ 14.99



## "ወያኔ በአዲስ አበባ ጉዳይ የታሪክ ቦንብ ነው የተከለው"


አምባሳደር ካሳ ከበደ (በተለይ ለግዮን)



# ከአወሊያ እስከ ሸራተን ከ2003-2011

ግዮን
ቅጽ 1 ቁጥር 54 ቅዳሜ ሚያዚያ 26 2011 ዓ.ም






ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
"ዕንቁላሉን ሰብረው የወጡ" ታማኙ ፕሬዝዳንት !
21

"ወያኔ በአዲስ አበባ ጉዳይ የታሪክ ቦንብ ነው የተከለው"
አምባሳደር ካሳ ከበደ
(በተለይ ለግዮን)
14

2 ከብራና እስከ ዲጂታላይዜሽን

3 << ትልቅና ዓይነ ግቡ የሆነውን ሀገራዊ ፓርቲ በቅርቡ ይፋ እናደርጋለን >>
አቶ አንዷለም አራጌ

4 ትኩረት የተነፈገው ነፃ ፕሬስና ቀጣይ ተግዳሮቶቹ!

የዐቢይ አንድ ዓመት ውጤት ሲገመገም
ፕ/ር መሣይ ከበደ
5

ከአሜሪካ እስከ አሜሪካ
በተስፋችን ላይ ጽልመት የጋረደው የዘር ፖለቲከኞች ጩኸት !
9 ጋዜጠኛ መሳይ መኮንን

11 ‹‹የእሥራቱ ዐዋጅ ተሽሯል!››... እውነት!?
በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

12 ይህቺ ኢትዮጵያ ናት ዓርብን አሳልፋ፤ ቅዳሜን ድል ነስታ እንደገና የምትነሳ፤ እንደገናም የምታሸንፍ

13 ለዛ

18 የሃገር ባለውለታዎችን ማክበር ታላቅነት ነው

23 የኢትዮጵያ ሙስሊም፡- ከአወሊያ እስከ ሼራተን ከ2003-2011
ሁሴን ከድር

25 "የይሁዳ ሠላምታ" በዘመኑ ፖለቲከኞቻችን ላይ !
ደረጄ ዘውዴ

26 ኢትዮጵያውያን ማሰብ አይችሉም? !
መታሰቢያ መልአክ ሕይወት

28 ሴቶች እና ዳግማይ ትንሣኤ
ፍቅርተ ተሾመ

የኢትዮጵያ ሚዲያ ነቀልቀለት ጉዞ ቀጥሎ...
መላክ ቢ..
7


ቀጣይ ዕትም ቅዳሜ ግንቦት 3 ይጠብቁን!




ቁጥር 53 ዕትም

# ከብራና እስከ ዲጂታላይዜሽን




“ማንበብ ወይም ምልክት ማድረግ ብቻ የበቃ አይደለም፤ የቅን ትምህርት ዋናው ምልክቱ የተነበበውን ከአእምሮ ጋር ማዋሃድ ነው። ላይ ላዩን ከማንበብ የሚገኝ ዕውቀትና ኮድ መጽሐፍ ውስጥ አንዳንድ ገፅ በመመልከት ብቻ ተገኝቶ የሚጠቀስ ቃል ሁሉ ለእውነተኛው የእውቀት መሻሻል እጅግ የሚያሰጋ መሰናክል ይሆናል። ስለዚህ ከዚህ መጻሕፍት ቤት ከሚገኘው የዕውቀት ምንጭ ለመቅዳት የሚመጡት ሁሉ መሰረት ከሌለው አፍአዊ ዕውቀት እንዲርቁ በጥብቅ እናስጠነቅቃችኃለን። … የምናስበው ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ለልጅ ልጆቻችንም ይሁን።” በማለት በቤተ መጻሕፍቱ የምረቃ መርሃ ግብር ላይ ቀ.ኃ.ሥላሴ የተናገሩት ንግግር ያስፈረው የ75ኛ አመት ኢዩቤልዩ በዓል የሚዘክር መፅሄት ላይ የተቀነጨበ ነው።

በአላማ የተከፈተውን የያኔው “የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት ወመዘክር” የአሁኑ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት ኤጀንሲ አሁን ላይ በሰው እድሜ አርጅቶ 75ኛ አመት የአልማዝ ኢዩቤልዩ በዓል በማክበር ላይ ይገኛል፡፡ ንጉሡ ሲከፈት የለገሷቸውን 600 መፃሕፍት ይዞ ከብራና የእጅ ስራዎች እስከ  አሁኑ ኢቡክ ድረስ ኤጀንሲው 200,000 ሺህ የሚጠጉ የመረጃ ሀብቶች እንዳሉት ይጠቅሳል። በመረጃ አለም ላይ ሳለን እንደ ሀገር ግን ካለብን የመረጃ እጥረት እና ችግር ባሻገር አሁንም ካሉን ጥቂት የመረጃ ማግኛ እና ማጣቀሻ ማዕከላት አንጋፋው ይህ ኤጀንሲ ነው።

ቤተ መዛግብቱ የያዛቸው ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ የሀገር ቅርሶች ሚናቸው ቀላል የማይባል ነው። 75ኛ አመቱን አስመልክቶ እየተካሄደ ባለው የቤተ መዛግብቱ አውደ ርዕይ ላይ በተደረገ ገለጻ ከተለያዩ ምዕራባዊያን ሀገራት የሚመጡ አጥኚዎች እድሜያቸውን ሙሉ እኒህን ቅርሶች በማጥናት እንደሚያሳልፉ ተናግረዋል።

ለዚህም በምክንያትነት የሚቀመጠው በቤተ መዛግብቱ የሚገኙት የእጅ ፅሁፎች በዓለም ላይ ጥቅም ላይ ያሉት የመፅሐፍ ቅዱስ እና ቅዱስ ቁርዓን የቆየው እና ትክክለኛዎቹ ቅጂዎች መሆናቸው ለጥናት ተመራጭ  እና ጠቃሚነቱ የላቀ በመሆኑ ነው። እንደ አብነት ለእይታ ከቀረቡት ውስጥ በ18ኛው ክ/ዘ የተፃፈ ቅዱስ ቁርዓን ከተፍሲር እና ሐዲስ ጋር፣ በህክምናው ዘርፍም ዕፅ መድሃኒት ወዕፀ ደብዳቤ (የአገር ባህል መድኃኒት) መፃሕፍት ይገኙበታል። አባቶች የታሪክ አስፈላጊነትን ዋጋ ከታሪክ ደግሞ አስፈላጊ ነው ያሉትን መርጠው የ249 የበግ ቆዳ በጨረሰው የብራና ስራ ላይ በአጠቃላይ 971 ገፆች ተጠቅመው፤ የከፈሉትን የጉልበት የእውቀት ዋጋ ሳንቆጥር ባለመሰልቸት እንደተሰራ በሚያሳብቀው ያሸበረቀ የቀለም ስብጥር የሚታየው፤ በኤጀንሲው ድልድይነት ለትውልድ የተሻገረው የብሉይ ኪዳን መፅሀፍ አንዱ ነው።

በ1899 በኦኔሲሞስ ነሲብ የተፃፈው የኦሮምኛ መፅሐፍ ቅዱስ ሌላው ነው። ኤጀንሲው በUNESCO በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ 4 መጻሕፍቶቹ መስፈርቱን አሟልተው በሂደት ላይ እንደሚገኙ የገለፀ ሲሆን፤ እነርሱም :- ክታብ አልፋራይድ፣ ክታብ አልሙሳጣፊ፣ መፅሐፈ ድጓ እና ባሕረ ሃሳብ ናቸው።

# ለላብ አደር

Sustainable Pension for all: The Role of Social Partners

አለም አቀፉ የላብ አደር አልያም “ወዝ አደር በዓል” ዘላቂ ጡረታ ለሁሉም፤ የማህበራዊ ትስስሮች ሚና በሚል መሪ ቃል በአለም አቀፍ ደረጃ ተከብሮ ውሏል።

ተነሱ እናንተ የምድር እስረኞች

ተነሱ እናንተ የምድር ጎስቋሎች

ፍትሕ በሚገባ ይበየናል

ሻል ያለ ዓለም እንግዲህ ይታያል

ከእንግዲህ ያለፈው ይብቃ ጣሉ ቀንበር …

መዝሙር በደርግ ስርዓት ወቅት ተማሪዎች በሰልፍ ላይ እንዲሁም በሌሎችም በዓላት ላይ የሚዘመር

በማለት የዘመሩ እና የተዘመረላቸው በእውነትም ለካፒታሊስትቶች ሃብት ማዳበሪያነት ላቡን ጠፍ አድርጎ የሚሰራው ላብ አደር በግሪጎሪያን ካላንደር 1886፣ ሜይ 1ን ቀኔ ይሁን ብሎ ይኸው እስካሁን ይከበራል። አጀማመሩ በአሜሪካ ቺካጎ  300ሺህ ሰራተኞች የመስሪያ ቤቶች አመቺ መሆን፣ በተለይም ደግሞ የስራ ሰዓታችን በህግ 8 ሰዓት ሆኖ እንዲፀድቅ እና ተመጣጣኝ ገቢ ማግኘትን አለብን፤ በአጠቃላይ ጥሩ የስራ ግንኙነትን እንፈልጋለን የሚል ይዘት በነበረው ሰልፍ ነበር። ምንም እንኳን ጅማሮው በካፒታሊስቷ አሜሪካ ቢሆንም በሶሻሊስት ሀገራት ውስጥ በተለያዩ የሰራተኛ እና ወታደራዊ ሰልፎች በድምቀት ከሚከበሩ በዓላት ተርታ ይመደባል።

የላብ አደሮች ቀን ወይም ሜይ ዴይ በኢትዮጵያ ታሪክ በተለያየ መልኩ ተከብሮ አልፏል። ከጊዜ ወዲህ ግን እቤት የመቀመጥ ቀን ተብሎ የሚከበር ይመስል ሰራተኞች ከስራ የሚያርፉበት ቀን ከመሆን ባለፈ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ እምብዛም ነው። ለአብነት በቱኒዚያ፣ ግብፅ እና ኦስትሪያ ባሉት የኮሚኒስት ፓርቲዎች አማካኝነት ሰራተኞችን የሚያንቀሳቅሱ የተለያዩ ሰልፎችን በማድረግ አሁንም ድረስ ይከበራል።

በኢትዮጵያ ሰራኞች ሲዘከሩ፣ ችግሮቻቸው ሲዳሰሱ፣ ሰራተኝነት ዋጋ ሲሰጠው የተሰማበት ጊዜ የአንድ ወጣት እድሜን አልፏል ማለት ያስችላል። ተማሪዎች በሜይ ዴይ ምክንያት ትምህርት መዘጋቱንና የእረፍት ቀን መሆኑን ከማወቅ ባሻገር ግንዛቤው ያላቸውን ማግኘት አዳጋች ነው። በተማሪዎች ዘንድ ከሜይ 1 ይልቅ አፕሪል 1 (አፕሪል ዘፉል)ን ለማስታወስ እና ለመዘከር በጣሙን የሚጠበቅ ቀን ነው። በእርግጥ ከስራ ክቡር ነው እስከ ሥራ ሥራ ሥራ የሙዚቃ ሥራዎችን ተዘፍነዋል፤ ሰራተኛውስ ማን አለው። አለም በዚህ ቀን “… ሻል ያለ ዓለም እንግዲህ ይታያል…” እያለች “… for you have nothing if you have no rights…” በማለት ታዜማለች።

ከደርግ ስርዓት ጋር ብቻ የተቆራኘ የሚመስለው የሰራተኞች ቀን ሰራተኞችን ወክሎ መከበር መቀነሱ ይህን ገፅታ ለመፍጠሩ ማሳያ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ከሰራተኞች መብት አቀንቃኝ ፓርቲዎች ይልቅ የዘውግ አቀንቃኝ ፓርቲዎች ሲበራከቱ ማየት ሀገሪቷ አዝማሚያዋ በአንድ ወገን ብቻ መሆኑን ማሳያ ነው። በ1955 የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሜይ 1ን የቅድስት ማርያም ጠባቂ በነበረው ‘ቅዱስ ዮሴፍ ሰራተኛው’ ብላ ቀኑን በስሙ ሰይማለች።

ከአፍሪካ ኢትዮጵያን ጨምሮ በአልጄሪያ፣ ጋና፣ ኬንያ፣ ሊቢያ፣ ሞሮኮ፣ ሞዛምቢክ፣ናሚቢያ፣ናይጄሪያ፣ ሶማሊያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ታንዛኒያ፣ቱኒዚያ፣ ኡጋንዳ፣ ዚምባቡዌ ብሔራዊ በአል አድርገው ከሚያከብሩ ሀገራት ተጠቃሽ ናቸው።

**ዜና ዘገባ**



## ጉዞ ወደ ዜግነት ፖለቲካ!

# < < ትልቅና ዓይነ ግቡ የሆነውን ሀገራዊ ፓርቲ በቅርቡ ይፋ እናደርጋለን > >

### አቶ አንዷለም አራጌ

በሀገር ዓቀፍ ደረጃ ጠንካራና ተፎካካሪ ሆኖ የሚወጣ አንድ ወጥ ፓርቲ ለመመስረት ከስምምነት ላይ የደረሱትና ለሀሳቡም ዕውን መሆን ከወዲሁ እየከሰሙ የሚገኙት ሰባት ፓርቲዎች ሚያዝያ 23 ቀን 2011 ዓ.ም በፍሬንድሺፕ ሆቴል ያዘጋጁት የገቢ ማሰባሰቢያ የእራት ፕሮግራም ሙሉ ለሙሉ በተሳካ ሁኔታ መከሄዱ ተገለፀ፡፡

“ጉዞ ወደ ዜግነት ፖለቲካ!” በሚል መርህ በተሰናዳው የእራት ግብዣ ላይ በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች የፓርቲዎቹን ጅምር እንቅስቃሴ በመደገፍ ተገኝተዋል፡፡ በፕሮግራሙ ላይ ከህብረተሰቡ በተጨማሪ የተለያዩ ታዋቂ ግለሰቦችና የፖለቲካ ሰዎችም ታድመዋል፡፡ የዜግነት ፖለቲካ አቀንቃኞችና በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ስማቸው ገዝፎ የሚጠራው የአርበኞች ግንቦት ሰባት ከፍተኛ አመራሮች ፕ/ር ብርሃኑ ነጋና አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ በእራት ግብዣው ላይ ለተገኙ ታዳሚዎች ንግግር አድርገዋል፡፡

አርበኞች ግንቦት ሰባት፣ ሰማያዊ ፓርቲ፣ ኢዴፓ፣ መኢዴፓ፣ የቀድሞው አንድነት አመራሮች፣ ኢትፓና ጋክን የተሰኙ ሰባት ፓርቲዎች ከጥቂት ቀናት በኋላ በውህደት ወደ አንድ ወጥ ፓርቲነት የሚመጡበት ሂደት ወጪ መሸፈኛ ታስቦ የተዘጋጀው የገቢ ማሰባሰቢያ የፕሮግራሙ አስተባባሪ የሆኑት አቶ አንዷለም አራጌ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት ረብዕ ሚያዝያ 23 ቀን የተካሄደው ፕሮግራም በገንዘብ ረገድ ውጤታማ ከመሆኑ ባሻገር፤ በቀጣይ ይፋ የሚሆነው ሀገራዊ ፓርቲ በህዝብ ደረጃ ያለው ተቀባይነት የጠነከረ ሊሆን እንደሚችል ያሳየ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

‹‹ሰባት ድርጅቶች አንድ ትልቅና ዓይነ ግቡ የሆነ ሀገራዊ ፓርቲ ለመፍጠር ጥረት እያደረግን ነው፡፡ ይህም ፓርቲ የፊታችን ግንቦት አንድና ሁለት በህዝብ ፊት ዕውን ይሆናል፤ በይፋ በሚመሰረትበት ወቅት ከውጭ ሀገር እንዲሁም ከተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ውስጥ ከሚገኙና እስካሁን ከተጠናቀቁ ሶስት መቶ አምስት ወረዳዎች የተውጣጡ ወደ አንድ ሺህ ስምንት መቶ የሚጠጉ አባሎቻችን ወጪ ለመሸፈን ሲባል የእራት ግብዣው ተካሄዷል›› ብለዋል፡፡

ቀደም ሲል ሰማያዊ፣ ኢዴፓ፣ ኢትፓና መኢዴፓ በአሁኑ ወቅት ሙሉ ለሙሉ መክሰማቸውን ያረጋገጡት አቶ አንዷለም አራጌ ከውጭ ሀገር የመጡት ጋምቤላ ክልላዊ ንቅናቄና አርበኞች ግንቦት ሰባት አዲሱ ወጥ ፓርቲ ይፋ ከሚሆንበት ሁለትና ሶስት ቀን በፊት አባላቱ ከውጭ ወደ ሀገር ቤት ተሰባስበው ድርጅቶቹ እንደሚከስሙና ታሪክ ሆነው እንደሚቀሩ ለደጋፊዎቻቸው ይፋ ያደርጋሉ ሲሉ ገልፀውልናል፡፡

“በእራት ግብዣው ላይ ባገኘነው ገንዘብ ልክ ሳይሆን ባገኘነው የህዝብ ድጋፍና ፍቅር እንዲሁም መነሳሳት ቀጣዩ ውህድ ፓርቲ የገዘፈና ጠንካራ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት ከወዲሁ አሳድረናል” በማለት የሚናገሩት የቀድሞው አንድነት ፓርቲ አመራር አባልና ታዋቂው ፖለቲከኛ አቶ አንዷለም አራጌ ‹‹የኢትዮጵያ ሕዝብ በተፈጥሮው ህብረ ብሔራዊ ነው መልካችንን፤ አንዱን ከሌላው በብሔር ልትለየው አትችልም፡፡ ትግርኛ ተናጋሪውን ከኦሮምኛ ተናጋሪው መልኩን አይተህ አትለየውም፡፡ አማርኛ ተናጋሪውን ከሌላ ቋንቋ ተናጋሪው እንደዚሁ መልኩን አትለየውም፡፡ ይሄ የሚያሳየው የሕዝቡ ደም በዘመናት ውስጥ ተጋብቶ፣ ተዋልዶ የኖረ ሕዝብ እንደሆነ ነው፡፡ የተወሰኑ ኤሊቶች የተለያየ የብቻው ታሪክ፣ የብቻው ደም ያለው የማይተዋወቅና የማይገናኝ አድርገው ቢያስቡም ህዝቡ ግን አንድ ሕዝብ ነው፤ ይሄ ለእኛ የዜግነት ፖለቲካ የተመቸ ለም መሬት ነው ብለን እናስባለን፡፡ በተለይ ደግሞ አሁን ሀገራችንን ሰቅዞ ለያዛት የዜሮ ፖለቲካ ይዘነው የመጣነው በፊት የነበረና አሁን እንደ አዲስ እየተደራጀንበት ያለው አስተሳሰብ ትልቅ መድህን ይሆናል ብለን እናስባለን፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብም ከጎናችን እንደሚቆም ተስፋ እናደርጋለን›› ሲሉ ዕምነታቸውን ለግዮን መጽሔት ገልፀዋል፡፡

## ዛሬም በጌድኦ

# < <ለሪፖርት ማሟያ የሚሆን እንጂ ለተፈናቃዮች ጠብ ያለ ነገር የለም> >

### አቶ ሲሳይ ማሞ

ከኦሮሚያ ክልል እና ከጌድኦ ዞን ተፈናቅለው የነበሩ ከ528 ሺ 700 በላይ ሠዎች ወደቀዬአቸው መመለሳቸውን የመንግስት መገናኛ ብዙኃን እየተናገሩ ቢሆንም የተጠቀሰውን ቁጥር 2 በመቶ እንኳ ወደቀደመው መንደራቸው ያልተመለሱ መሆኑን ምንጮቻችን ፡፡ የኦሮሚያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽንም ባሳለፍነ ሳምንት ባወጣው መረጃ ላይ በክልሉ ከሚገኙ 1 ነጥብ 4 ሚሊዮን ተፈናቃዮች ውስጥ ከ500 ሺዎች በላይ ወደ ቀዬአቸው መመለሳቸውን መጥቀሱ የሚታወስ ነው፡፡ ሚያዝያ 16 ቀን 2011 ዓ.ም ተፈናቃዮች ባሉበት ቦታ የተገኙት የደቡብ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኤልያስ ሽኩርና የኦሮሚያ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አህመድ ቱሳ ከጌድኦ የተፈናቀሉ ጉጂዎችን ወደ ጌድኦ እንዲሁም ከምዕራብ ጉጂ የተፈናቀሉ ጌድኦዎችን ወደ ነበሩበት ምዕራብ ጉጂ ስለሚመለሱበት ሁኔታ ከተፈናቃዮቹ ጋር ውይይት ያደረጉ መሆናቸው ቢገለፅም እስካሁን ድረስ የተጀመረ ዕርምጃም ሆነ ቅድመ ዝግጅት ያለመኖሩን ተፈናቃዮቹ በምሬት ይናገራሉ፡፡ ለሚዲያ ሽፋን የሚሆኑና ያልተከናወኑ ተግባራትን እውነት አስመስሎ በማቅረብና የተዛባ መረጃ በመስጠት ችግራችንን ማባባስ ተገቢ አይደለም ሲሉም ቅሬታቸውን ገልፀዋል፡፡

በሁለቱ የክልሉ መስተዳድሮች በኩል እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 2011 ዓ/ም ድረስ ከጉጂና ከጌድኦ ዞኖች የተፈናቀሉትን ወደ ነበሩበት ቦታ ለመመለስና ለማቋቋም ስምምነት ላይ መድረሳቸውን በተመለከተ ላቀረብንላቸው ጥያቄ ኮሚቴውን በመወከል አቶ ሲሳይ ማሞ የሚከተለውን ብለውናል፡፡

“ወደ ቀዬአችን ብንመለስም በመንግስት በኩል የሚገቡልን የተስፋ ቃላት በተግባር ስለማይፈፀሙ፤ ይደረጋል፣ ተድርጓል የሚባለው ሁሉ ለሪፖርት ማሟያ የሚሆን እንጂ ለተፈናቃዮች ጠብ ያደረገው ነገር የለም፡፡ በዚህ የተነሳ በአሁኑ ሰዓት መረጃ ታፍኖ ሠዉ በረሃብ እየተቀጣ ነው የሚገኘው፡፡ በተደጋጋሚ እስከ ጠ/ሚሩ ቢሮ ድረስ ጥያቄያችንን ብናቀርብም መልስ አጥተናል፡፡ ነገር ግን በውይይት መግባባት ላይ ተደርሷል፣ በቅርቡም እስከ ሚያዝያ 30 ድረስ ሁሉም ተፈናቃይ ወደነበረበት ተመልሶ ሠላማዊ ህይወት መምራት ይጀምራል የሚለው ነገር ተፈፃሚ ይሆናል የሚል ዕምነት የለንም›› በማለት ያስረዳሉ፡፡

ችግሩ እየተባባሰ በመምጣቱ በተለይም ህፃናትና አረጋውያን ለከፋ ህመምና ለሞት እየተጋለጡ መሆኑን በማሰብ ሠሚ ጆሮ ፍለጋ ሠላማዊ ሠልፍ ለማድረግ ተዘጋጅተው ሳለ ባልተወቀ ምክንያት ሠልፉን ለሚያዝያ 23 ቀን 2011 ዓ.ም እንዲያዛውሩት እንደተነገራቸው፤ ሆኖም በእለቱ ሰልፉን ለማካሄድ ቅስቀሳና ቅድመ ዝግጅት ከተደረገ በኋላ በድጋሚ ሠልፉን ማካሄድ እንዳልተቻለ የኮሚቴው አባላት ይናገራሉ፡፡

‹‹ወደ ነበርንበት ሥፍራ ለመመለስ ፍላጎቱ አለን፤ ነገር ግን እንኳን ለመመለስ የሚያስችል ሁኔታ ቀርቶ አሁንም ድረስ ችግሩን ተቋቁመው እዚያ የነበሩትም ወደኛ የመምጣት ፍላጎት ነው ያላቸው፡፡ ምክንያቱም በመንግስት በኩል እየተነገሩ ያሉት ፕሮፓጋንዳዎች ፍፁም ከዕውነታው ጋር የማይመሳሰሉ በመሆናቸው ነው፡፡ በመገናኛ ብዙኃን በኩል አሁንም ድረስ ለተፈናቃዮቹ ምቹ ሁኔታ ተመቻችቷል ቢሉም እኛ የችግሩ ገፈት ቀማሾች በመሆናችን ያለውን ነገር ለመናገርና ለማስረዳት አጋጣሚው ሊፈጠርልን አልቻለም፡፡ እነሱ (የመንግስት አካላት) ደጋግመው የሚናገሩትን ለማመንም እንቸገራለን፡፡ ትልቁም የተፈናቃዮች ችግር ይሄ ነው፡፡ በተረፈ ግን ጥያቄም እያቀረብን ያለው ወደ ቀድሞ የተረጋጋ ህይወታችን እንድንመለስ ስለሆነ በጤና፣ በምግብና በተለይ በመጠለያ ጉዳይ ላይ ያለውን ችግር መንግስት በአስቸኳይ መፍትሄ እንዲያበጅለትና ተጨባጭ የሆነ ዕርምጃ እንዲወስድ ነው የኛ ፍላጎት›› በማለትም የመገናኛ ብዙኃኑን ዘገባዎች ያስተባብላሉ፡፡

# ትኩረት የተነፈገው ነፃ ፕሬስና ቀጣይ ተግዳሮቶቹ!

በያዝነው ሳምንት የፕሬስ ቀን በመላው አለም በተለያዩ ደማቅ ዝግጅቶች እየተከበረ ይገኛል፡፡ ነፃ ሚዲያ ለአንድ ሀገር ዴሞክራሲያዊ ሂደትና አጠቃላይ የዕድገት ገፅታ፤ ስለሚኖረው ጠቀሜታ የተለያዩ ኢንተርናሽናል ተቋማት ታላላቅ ኮንፈረንሶችን በማዘጋጀት እንደየ ሀገራቱ ነባራዊና ተጨባጭ ሁኔታ ጥልቅ የሆኑ ሙያዊ ውይይቶች እየተካሄዱ ናቸው፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ "ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሰፍኗል" ተብሎ ነፃ ሚዲያዎች በስፋት መቋቋም የጀመሩት በ1980ዎቹ አጋማሽ መሆኑ ይታወሳል፡፡ የመለስ ዜናዊ መንግስት የመፃፍ፣ የመናገር፣ ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት በዚህች ሀገር ላይ በይፋ እንደተሰጠ ባወጀ ማግስት፣ ብዛት ያላቸው የህትመት ውጤቶች ከአንባቢያን ዘንድ መድረስ ጀምረው ነበር፡፡

መንግስታዊ የሚዲያ ተቋማት ከሚያስተጋቧቸው የሀሰት ፕሮፓጋንዳዎችና ድብቅ የፖለቲካ ተልዕኮዎች ተቃራኒ በሆነ መልኩ፤ የስርዓቱን ግድፈትና ዘርፈ ብዙ ችግሮች ነቅሰው በማውጣት፣ በዜጎች ላይ የሚደርሰውን ግፍና በደል በማጋለጥ ረገድ ትኩረት ሰጥተው የሰሩት የነፃው ፕሬስ ውጤቶች፤ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ወያኔ/ ኢህአዴግ ከአደረጃጀት ቅርፅና ዓላማው አንስቶ፣ ይዞት መሀል ከተማ የገባው ፖለቲካ ለኢትዮጵያ አንድነትና ህልውና አደጋ መሆኑ፤ በዛው መጠንና ልክ አምባገነኑ ስርዓት በፖለቲካው መድረክ የሚገዳደሩትን ኃይሎችና ተቋርቃሪ ዜጎችን የሚደፈጥጥበትን የረቀቀ ስልት ገሀድ በማውጣት ረገድ፣ ፕሬሱ ከማለዳው ጀምሮ ያበረከተው አስተዋፅኦ እንዲህ በቀላል የሚገለፅ አይደለም፡፡

አንዳችም አስተማማኝ ዋስትና በሌለበት የስራ ሂደት ውስጥ፣ ብዛት ያላቸው ጋዜጠኞች ላለፉት 25 ዓመታት ራሳቸውን ለመስዋዕትነት አዘጋጅተው ሕወሓት/ኢህአዴግ መራሹን መንግስት ሞግተዋል፡፡ ተጨባጭ ማስረጃዎችንና ዳታዎችን በማስደገፍ የእዚህ ሀገር ሀብትና ንብረት ያለ አግባብ እየተዘረፈ መሆኑን አጋልጠዋል፡፡ ዛሬ ብዙዎች የሚገረሙበትን የሰብዓዊ መብት ጥሰት ከ1980ዎቹ መጨረሻ አንስቶ በርካታ የነፃው ፕሬስ ውጤቶች በስፋት ሲዘግቡት የኖሩት ሀቅ መሆኑም አይዘነጋም፡፡

ይህ ሁሉ በሚሆንበት ሂደት ውስጥ ነፃው ፕሬስ ከመንግስት ጋር አይጥና ድመት ከመሆኑ በተጨማሪ፤ በርካታ በደሎችም ይደርሱበት ነበር፡፡ "ሙዚየም ይሆናል" በተባለለት ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ እንደነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች አታካች በሆነ መልኩ የተመላለሰበትም ሆነ የታሰረበት የለም ብሎ በድፍረት መናገርም ይቻላል፡፡

በሙያቸውና በእውነተኛ ሀገር ፍቅር ስሜት የተለከፉ በርካታ ጋዜጠኞች ከተደጋጋሚ እስር ባሻገር ድብደባ፣ ግርፋትና የከፋ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ያለ ርህራሄ ተፈፅሞባቸዋል፡፡ ከራሳቸው አልፎ በቤተሰቦቻው ላይ የሚደርሰው ግፍና መከራ በማየሉም ጥቂት የማይባሉ ሙያተኞች ሳይወዱ በግድ ይህችን ሀገር ለቀው ኑሮን በስደት ሕይወት ለመግፋት ተገደዋል፡፡

በዚህን መሰሉ መከራ ውስጥ ያለፈው ነፃው ፕሬስ ዛሬ ላይ ከከባድ አሳሳቢ ችግር ላይ ይገኛል፡ ፡ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ በመጡ ማግስት ተመናምኖ የነበረው ፕሬስ ዳግም በመመለሱ፤ በተወሰነ ደረጃ መነቃቃት ቢታይበትም፣ አሁንም ከፊት ለፊቱ ዘለቄታዊ ሕልውናው የሚገዳደሩ ዘረፈ ብዙ ችግሮች ተጋርጠውበታል፡፡

ለውጡን በማበረታቱና በመደገፉ ረገድ የራሱን አስተዋፅኦ እያበረከተ የሚገኘው ነፃው ፕሬስ፣ አስቀድሞ ከስርዓቱ ይደርስበት የነበረው አፈና፣ ዕስርና ማዋከብ ቢቀልለትም፤ ዘርፉን የሚደግፉት ተዛማጅ ጉዳዮች ግን አሁንም መፍትሄ ለማበጀት ፍላጎት ያለ አይመስልም፡፡ መንግስታዊ መዋቅሮች ፕሬሱን በጠላትነት ከፈረጁበት አባዜ ያልተላቀቁ በመሆናቸው፤ እነሆ ለግል ሚዲያዎች መረጃዎችን መስጠትና በመግለጫቸው ላይ እነርሱን መጋበዝ ሞት መስሎ እንደታያቸው ሰንብተዋል፡፡በየሳምንቱ የሚጨመምረው የማተሚያ ቤቶች ዋጋ፣ የወረቀትና የቀለም ዋጋ ውድነት በዚህ ወቅት ዋነኛ የነፃው ፕሬስ ማነቆዎች ናቸው፡፡

አምባገነኑ የወያኔ ስርዓት ፕሬሱን ለማፈን የተጠቀመበት አንዱ መንገድ በየጊዜው ዋጋው የሚጨምረውን የወረቀት ዋጋ፣ የራሱ ጥቂት ታማኝ ነጋዴዎች እንዲቆጣጠሩት በማድረግ እንደነበር አይዘነጋም፡፡ ከመጠን በላይ የሚቆለለው የወረቀት ንግድን አሁንም ሙሉ በሙሉ የተቆጣጠሩት እነዛው የቀድሞው ስርዓት አገልጋዮች መሆናቸው ደግሞ ችግሩን የበለጠ እንዲወሳሰብ አድርጎታል፡፡

የጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ መንግስት የነቃና የተማረ ትውልድ ለመፍጠር ንባብ ግድ መሆኑን እስካመነ ድረስ፤ በየጊዜው የሚለዋወጠውን የወረቀት ዋጋ በተስተካከለ ስርዓት ውስጥ እንዲጓዝ፣ ትውልድ ቀራጭ የሆኑ ጸሐፊያን እንዲበራከቱ ፤አስፈላጊውን ድጎማ ከማድረግ ባሻገር፣ የወረቀት አስመጪነቱ ንግድ ከሞኖፖል አሰራር ነፃ ወጥቶ ሌሎች ባለ ሀብቶችም በዘርፉ እንዲሰማሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡ በመጨረሻም ጠ/ሚኒስትሩ በርካታ የሙያ ዘርፍ የተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ሰብስበው እንዳወያዩት ሁሉ፤ ከ25 ዓመታት በላይ አምባገነኑን ስርዓት ለመገርሰስ፣ ዘመን የማይሽረው ትግል ያደረገውን ነፃውን ፕሬስም ትኩረት ሰጥተው ሊያነጋግሩት፣ ሀሳብ ጥያቄዎቹን ሊያደምጡለት እንደሚገባ ሳንጠቁም አናልፍም ፡፡


**ግዮን መጽሔት**

**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**

**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**
ሮቤል ምትኩ
አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ
ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 475

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ብሩክ መኮንን
መለስ ሽኔ

**ተባባሪ ዘጋቢያችን**
ቶማስ አያሌው(ከአሜሪካ)

**አምደኞች**
ወንድሙ ነጋሽ(ኢ/ር ከለንደን)
ተረፈ ወርቁ
ሁሴን ከድር

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ባሳዝነው ወንድምነህ

**ጸሐፊ**
ሠላም ግርማ


**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09
የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 2ተኛ
ፎቅ ቢሮ ቁ. 207
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 22 76 61
+251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011meg@gmail.com
**Facebook**
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013



በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም



**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ
0911223335/ 0911420506



መሳይ ከበደ (ፕሮፌሰር)

# የዐቢይ አንድ ዓመት ውጤት ሲገመገም

*"ሰዎች የራሳቸውን ታሪክ ይሰራሉ፤ የሚሰሩት ግን እንዳሻቸው አይደለም፡፡ የሚሰሩት ራሳቸው በመረጧቸው ሁኔታዎች ውስጥ ሳይሆን እያጋጠሟቸው ካሉና ካለፈው በተላለፉ ሁኔታዎች ውስጥ ነው፡፡" (ማርክስ)*

በአንድ ዓመት ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስትር ከሆነ ጀምሮ ዐቢይ ታላላቅ ነገሮችን በተለይም በፖለቲካ መስክ ውስጥ እንዳከናወነ የማይካድ ነው፡፡. ይሁን እንጂ ከባድ መሰናክሎች እንደገጠሙት እና አንዳንድ ጊዜም ባለፈው መንግስት ታፍነው የነበሩ የጥፋት ሀይሎችን ሳይፈልግ እንደለቀቃቸው የማይካድ ሌላው ሀቅ ነው፡፡ ከፍተኛ ስኬት ካላቸው መካከል ተለይተው የሚታዩ ውጤቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡ 1) የቀድሞው መንግስት ከፋፋይና እና አድሎአዊ (ዘውጋዊ) አመላካከትን በአዲስ የኢትዮጵያን አንድነት እና ሉአላዊነት የሚያጎላ እይታ መቀየሩ፡፡ 2) ሁሉን አቀፍ ብልጽግናን ለማምጣት የሚችል ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለመመስርት የሰጠው ተስፋ እና ያሳያቸው የመጀመሪያ ደረጃ ተግባራት፡፡ 3) የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ ካለቅድመ ሁኔታ ነጻ መለቀቃቸው፡፡ 4) በነፃ የመናገር፤ ሰላማዊ ስብሰባ የማድረግ እና ማህበር የመመስረት መብቶች ላይ ተጥለው የነበሩት እገዳዎች (የአዲስ አበባ ጉዳይ ሳይካተት) ማንሳቱ፡፡ 5) የወያኔን የበላይ አገዛዝ ለፍጻሜ ማድረሱ፡፡ 6) ከኤርትራ ጋር በፊት የነበረውን የሰላም እጦት ሁኔታ ወደ ሰላማዊና ትብብራዊ አቅጣጫ እንዲሄድ ማደረጉ፡፡ 6) ተቋማትን ወደ መልካም አስተዳደር እና ተጠያቂነት ለማሸጋገር ያሳየው አበረታች ጥረቶች፡፡ በማንኛውም መለኪያ በዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥና በሚያውክ ሁኔታ ውስጥ እነዚህ አስደናቂ ማሻሻያዎች ተግባራዊ መደረጉ የሚደንቅ ውጤት ነው፡፡ ምንም ሳልቆጠብ ለዐቢይ እንኳን ደስ አለህ አላለሁ!

እንደ ኢትዮጵያ ውስብስብ ችግሮች ውስጥ የተዘፈቀ አገርን የመለወጥ ጥረት ብዙ ፈተና እንደሚገጥመው አይቀሬ በመሆኑ ያስመዘገባቸውን ውጤቶቹንና በህዝብ ዘንድ ያገኘውን ተወዳጅነት እስከ መቀነስ የደረሱ ፈተናዎች ዐቢይን ገጥመውታል፡፡ ይዞ የተነሳው መተማመንና እሱ፣ ፓርቲውና የኢትዮጵያ ህዝብ ያከናውናሉ ብሎ ያሰማው ተስፋ ለተከሰቱት አዳዲስ ችግሮች መንስኤ ናቸው፡፡ በእሱ ብሩህና የሚያነሳሳ ራዕይ የተነሳ ብዙ ሰዎች የወያኔ የ27 አመታት ከፋፋይ፣ ሙሰኛና ዘውጋዊ አገዛዝ ያከማቻቸውን ሥር ሰደድ ችግሮች ማየት ተስኗቸዋል፡፡ በመሆኑም አሳማኝና ሚዛናዊ የሆነ ግምገማ ላይ ለመድረስ ዐቢይ ከቀድሞ መንግሥት የወረሳቸውን መሰናክሎችና በራሱ ሃሳባዊ እይታ የተጀመረው ለውጥ ያስከተላቸውን ችግሮች ለማቆም ያልወሰዳቸው እርምጃዎች ከፈጠሩት እንቅፋቶች መለየት ያስፈልጋል፡፡

## የተወረሱ መሰናክሎች

በተደጋጋሚ የሚሰማው ቅሬታ የሚለው የዐቢይ መንግሥት አንድን አካባቢ በሚጋሩ የተለያዩ ዘውጎች መካከል እየደረሰ ያለውን ደም መፋሰስና የብዙ ህዝቦች መፈናቀልን ማቆም አልቻለም ነው፡፡ ሆኖም ግን ለእነዚህ አሳዛኝ ፈተናዎች ዐቢይን ተጠያቂ ማድረግ የተሳሳተ አመለካከት ነው፡፡ እውነት ነው፤ ሰላምንና የሰዎችን መሠረታዊ መብቶች ማስከበር የመንግስት ዋነኛ ሃላፊነት ነው፡፡ ይህ ግን ሊያስወቅስ የሚችለው በእርግጥም ዐቢይ የተረከበው በሰላም የሚኖር አገር ነበረ ስንል ብቻ ነው፡፡ ከአንድ ዓመት በፊት በተከታታይ በሚነሱ ሕዝባዊ ተቃውሞዎችና አመጾች ኢትዮጵያ የእርስ በርስ ጦርነት አፋፍ ደርሳ እንደነበረች ማስታወስ ያስፈልጋል ወይ?

ከአንድ ዓመት በፊትና በአሁን መካከል ያለው ልዩነት አቢይ ያልነበረውን ሰላም መጠበቅ አለመቻሉ ሳይሆን፤ ባለፈው መንግሥት የጭቆና ስልቶችና መሳሪያዎች መጠቀም አለመፈለጉ ነው፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት በከፊል በዴሞክራሲያዊ እምነቱ ለመጽናት፣ በከፊል ደግሞ በመንግሥቱ አፍና መሳሪያ ላይ ያለው ቁጥጥር በበቂ የተጠናከረ ደረጃ ላይ አለመሆኑ ነው፡፡ ከአንድ ዓመት በፊት በዘውግ የተለያዩ ሰዎችን ለመጉዳት እና ለማፈናቀል ፍላጎት ነበር፤ ነገር ግን በመንግስት አስገዳጅ ኃይል የተነሳ ፍላጎቱ በግልጽ መውጣት አልቻለም ነበር፡፡ በተጨማሪ ከአንድ ዓመት በፊት የተቃውሞው ዋነኛ ትኩረት የህውሀትን አገዛዝ ማስወገድ ስለነበር ግቡን ለመምታት አስፈላጊው ከዘውጋዊ ልዩነት ይልቅ አንድነት ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን የህውሀት አምባገነናዊ አገዛዝ ወድሞና ዴሞክራሲያዊ እምነቶችን ሥራ ላይ ለማዋል በሚጥር መንግሥት በመተካቱ፤ አንድን ክልል በሚጋሩ የተለያዩ ዘውጎች መካከል አለ የሚባለውና በአመዛኙ በጽንፈኛ ቡድኖች የሚራገበው ቅራኔ ከሁለተኛ ወደ አንደኛ ደረጃ ተሸጋግሯል፡፡

ሌላው የተወረሰ መሰናክል የቀድሞው መንግሥት በዘረጋው መዋቅርና ባፈራቸው ካድሬዎች እና ባለሥልጣናት በመጠቀም ጥልቅ የሆነ መንግሥታዊ ለውጥ ለማምጣት ከሚደረገው ሙከራ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይህ በቀድሞ መሳሪያ አዲስ ነገር የመመሥረት ፖሊሲ የተሃድሶውን ስርጭት እና ጥልቀት በእጅጉ የሚገድብ ነው፡፡ ከፓርቲው ውጭ ያሉ ብቁና ለውጥ ፈላጊ ግለሰቦችን በመጥራት ዐቢይ ይህን መሰናክል ማስወገድ ይችል ነበር ብሎ ማሰብ ይቻላል፡፡ ወደድንም ጠላንም በአሁኑ ጊዜ ኢህአዴግ ማዕከላዊ መንግሥትንና ክልላዊ መንግስታትን ሊያስተዳድር የሚችል ብቸኛ ፓርቲ ነው፡፡ እሱን ወደ ጎን ለመተው የሚደረግ ማንኛውም ሙከራ በተለያዩ ዘውጎች መካከል በቀላሉ ወደ ግጭት የሚወስድ የትርምስ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል፡፡ ዐብይ ከኢህአዴግ ካድሬዎችና ባለሥልጣናት ጋር ከተቃረነ እራሱን አስከፊ ሁኔታ ውስጥ ያስገባ ነበር፡፡ ከዚህም ሌላ አንጻራዊ ሰላም ባለበት ሁኔታ ወስጥ የሚቻለውን ለውጥ ለማምጣት እንኳን ዕድል አይኖርም ነበር፡፡

ከተወረሱት መሰናክሎች መካከል በግንባር ቀደምትነት መቀመጥ ያለበት የህውሀት ሙሉ በሙሉ ሳይሸነፍ በክልሉ መሽጎ መቀመጡ የሚያስከትለው ውስብስብ ችግር ነው፡፡ በግልጽ እንደሚታየው የዐቢይን መግሥት በተለያዩ ዘዴዎች በማዳከም ወደ ነበረው የበላይነት ለመመለስ አሁንም ህውሀት እየሰራ ነው፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ዐቢይን የሚቃወሙ የተለያዩ ቡድኖች፤ ከኢህአዴግ ውስጥም ሆነ ውጪ ያሉትን ጽንፈኞች ጨምሮ፤ በህውሀት የገንዘብ እና ወታደራዊ ድጋፍ በመተማመን ወደ ነበረበት ሥልጣን እንደገና ለመመለስ ከውስጥ መንግሥትን የሚቦረብሩ ቡድኖች ከማበራከት፤ በተለይም በተለያዩ ዘውጎች መካከል ሰላም ከማደፍረስ፤ የበለጠ አመቺ ሁኔታ የለም፡፡

በመጨረሻም የኢኮኖሚው እጅግ አስከፊ ሁኔታ ዐቢይ ከበፊቱ መንግሥት የወረሰው ሌላው ዋና ማነቆ ነው፡፡ ከፍተኛ የሥራ አጥነት በተለይም በወጣቱ መካከል በሚታይበት፤ ከባድ የውጭ ምንዛሪና መሠረታዊ ነገሮች እጥረት ባለበት፤ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ግሽበትና ዝቅተኛ ደመወዝ በሰፈነበት፤ ይህ ሁሉ ደግሞ ከጸያፍ ብክነት፤ በጣም ከተስፋፋ ሙስናና ከጥቂቶች በሕገ-ወጥነት መበልጸግ ጋር በተዳመረበት ሁኔታ በሰላማዊ መንገድ ለውጥን ለመተግበር መሞከር በተለያዩ ኢትዮጵያዊ የሕብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ የታመቀውን ውጥረት ለመቀነስ አያስችልም፡፡ ይህ ኢኮኖሚያዊ እድገትን እና እኩል እድልን ባለማግኘት የሚነሳው ሥር የሰደደ ቅሬታ አክርራሪነትን ይመግባል፤ በተለይ በዘውጎች መካከል ውጥረትን ይቀሰቅሳል፡፡ ሰዎችን እንደ ባዕድ ስለሚያይ እነሱ፣ እኛ የሚለው ከዘውጋዊነት የሚመነጨው ▶

ልዩነት የሕዝቦችን መሰደድና መነጠቅ በቀላሉ ያስከትላል፡፡

## አዳዲስ ችግሮች

የኦሮሞ ህዝብ በተለይም ወጣቱ የህወሀትን የበላይነት በማሽነፍ ትግሉ ውስጥ ወሳኝ ሚና መጫውቱና የለውጡ ቀስቃሽና አመራር የተገኘውም ከአገዛዙ የኦሮሞ ክንፍ አባላት(ኦዴፓ) በመሆኑ፤ ሥልጣን በኦሮሞ ልሂቃን እጅ ወድቋል የሚል ትርጓሜ በቀላሉ አግኝቷል፡፡ ከመነሻው ዐቢይ ያተኮረው ኢትዮጵያዊነት ላይ ቢሆንም፤ እራሱንም ያስተዋወቀው እንደ የኢትዮጵያውን ሁሉ መሪ እንጂ እንደ የአንድ ዘውግ አለቃ ባይሆንም፤ የኦሮሞ የበላይ ክፍል የትግሬን ልሂቃን እየተካ ነው የሚለው ስዕል ከመቀረጹም ባሻገር የኦሮሞ ልሂቃኖች ሁሉ ከየትም ፖለቲካዊ አቅጣጫ ተቀብለውታል፡፡

በእኔ አመለካከት ኢትዮጵያን ስጋት ላይ ከሚጥሉ አደጋዎች ሁሉ ለለውጡ መቀጠልና ለሰላም መጠበቅ እጅግ አደገኛ የሆነው ይህ የኦሮሞ ልሂቃኖች የበላይነት ፍላጎት ነው፡፡ ፍላጎቱ ለ27 ዓመታት በነበርንበት ሁኔታ ውስጥና ወደ አየነው የህውሀት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ የበላይነት በመቃወም ወደተነሳው ሕዝባዊ አመጽ መልሶ የሚከተን ነው፡፡ ይህ የኦሮሞ ልሂቃኖች የበላይ ቁጥጥር ፍላጎት በአጭሩ ካልተቀጨ ለውጥ ለማምጣት የሚኖር ማንኛውም ፍላጎት ይዳፈናል፡፡ ምክንያቱም ያገኙትን የበላይነት በመጠበቅ ሥራ ይጠመዳሉ፤ ሊያቆዩትም የሚችሉት በመበቀል ስሜት የሚመራ አምባገነናዊ ሥርአት ሲያመጡ ነው፡፡

ወደ ፊት ሊመጣ የሚችለውን እያሳየን ያለው ሌላው ጉዳይ የኦሮሞ ልሂቃኖች በአዲስ አበባ ላይ የወሰዱት አቋም ነው፡፡ የከተማው ነዋሪዎች የሚሉትን ወደ ጎን በመተው፤ ህገመንግሥቱ የሰጠውን ነጻነትና የራስ ገዝ መብት በመሻር አዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ሥር ትጠቃለል የሚለው ጥሪ የሚያንጸባርቀው የራስን ፍላጎት ሌላው እንዲቀበል የማስገደድ ዝንባሌን ነው፡፡ ይሄም የሚሆነው ልክ ህውሀት በአምባገነናዊ የ27 ዓመታት አገዛዙ ውስጥ እንዳደረገው፤ ግዳጁ መፈጸም ያልበት ትክክል ስለሆነ ሳይሆን የአሸናፊው ፓርቲ ፈላጎት ስለሆነ ብቻ ነው፡፡ ዐቢይና ተከታዮቹ ይህንን የኦሮሞ ልሂቃኖች የበላይነት አዝማሚያ በቆራጥነት ካላስቆሙት ምንም ዓይነት ለውጥ ሊመጣ አይችልም፡፡ ማርክስ እንዳለው "ታሪክ እራሱን ይደገማል፤ መጀመሪያ እንደ መከራ፤ ሁለተኛ እንደ ቀልድ፡፡"

እንደ ብዙ አክቲቪስቶችና ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች አመለካከት ዋነኛው የኢትዮጵያ በርካታ ችግሮች ምንጭ አሁን ያለው የዘውግ ፌዴራሊዝም ሥርዓት ነው፡፡ በመቀጠልም የዘውግ ፌዴራሊዝም እስካልተቀበረ ወይም እስካልተቀየረ ድረስ ለውጡ የታሰበውን ፍሬ በምንም ዓይነት ሊያስገኝ አይችልም ይላሉ፡፡ በሌላ አባባል ዐቢይ የኢትዮጵያን ሕብረተሰብ ለማሻሻል በሚያደርገው ጥረት ውስጥ ለገጠሙት ችግሮች መንሳኤው የዘውጋዊ ፌዴራሊዝምን ስርአት አስወግዶ በዘር ሳይሆን በዜግነት ላይ የተመሰረተ ፖለቲካዊ ስርዓት መተካት አለመፈለጉ ነው፡፡ የቀረበው መፍትሔ ማራኪ ቢሆንም በኢትዮጵያ ውስጥ ጥልቀት ያለው የዘውጋዊ ማንነት ፖለቲካ መኖሩን ይክዳል፡፡ ዐቢይን ከማጠናከር ይልቅ እንዲህ ዓይነቱ ሐሳብ በራሱ ፓርቲ ውስጥ ያለውን መሪነት ያዳክማል፡፡ የማይካድ ነገር ቢኖር በጠቅላይ ሚኒስትርነት እንዲቀጥል የፓርቲው ድጋፍ አስፈላጊ እንደሆነ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአንድ ዘውግ አለቃ ሆኖ ከተወሰነ ዐቢይ የያዘውን የኢትዮጵያዊነት አጀንዳ ተግባራዊ ሊያደርግ አይችልም፡፡

ይህ ሁሉ የሚያሳየው ሁለት የማይጣጣሙ ፖለቲካዊ አዝማሚያዎች እንዳሉ ነው፡፡ በአንድ በኩል ኢትዮጵያዊነት አለ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ዘውጋዊነት አለ፡፡ ዘውጋዊ ክልሎችና መንግሥታት ይወገዱ የሚለው ሀሳብ የዘውግ ማንነት ሥር የሰደደና ከተወስኑ የክልል ጥቅሞች ጋር የተቆራኘ በመሆኑ ሰፊ ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም፡፡ አሁን በኢትዮጵያ ዘውጋዊ ክልሎችን ሊደመስስ የሚችል መንግሥት ሊኖር ይችላል ብለን ብናስብም የተጠቀሰው መፍትሔ በኃይልና በአምባገነናዊ ዘዴዎች መጠቀም ይኖርበታል፡፡ ይህም ሆኖ አገሪቷን የማረጋጋት ችሎታው በጣም አጠራጣሪ ነው፡፡ በሌላ በኩል ኢትዮጵያዊነትን የማይቀበሉና ባለው ዘውጋዊ ፌዴራሊዝም እንቀጥል የሚሉት ሁኔታው ጨርሶ እንደማያዋጣ አልታያቸውም፡፡ የጋራ ማንነትና ዕጣ እንዲሁም የአንድነት ባህላዊና ፖለቲካዊ ድጋፍ ከሌለ አሁን ያለው ዘውጋዊ መበታተን ተጨማሪ ግጭቶችና መፈናቀሎችን ከማስከተሉ ባሻገር የአገሪቷን አንድነት እያደከመ ወደ መገነጣጠል የሚወስድ ነው፡፡ ይህ ውጤት ደግሞ የአፍሪካን ቀንድ በሙሉ እሳት ውስጥ የሚከት ነው፡፡

በመሆኑም መከተል የሚያስፈልገው ብሔራዊ አንድነትንና የዘውጋዊ ክልሎችንና ማንነቶችን አጣምሮ ሊሄድ የሚችለውን መካከለኛ መንገድ ነው፡፡ በተለያዩ ጽሁፎች ከዚህ በፊት እንደገለጽኩት፤ መካከለኛ መንገድን የሚሹ ኃይሎች (ብሔራዊ ተቋማትና ምልክቶች) መሀከልን የሚሸሹ ኃይሎችን (ዘውግን) ሊመክቱ የሚችሉ ተቋማት መፍጠርን ይመክራል፡፡ መሀከልን የሚሹና መሀከልን የሚሸሹ ኃይሎችን የሚያጣጥመው አንዱ ወሳኝ መንገድ ትልቅ ፖለቲካዊና ተምሳሌታዊ ትርጉሞች ያሉት ፕሬዝዳንታዊ ሥልጣንን መፍጠር ነው፡፡ ከብዙ ልዩ መብቶች ውስጥ ለምሳሌ ፕሬዝዳንቱ ጠቅላይ ሚኒስትሩን የመሾም ሥልጣን ሊኖረው ይችላል፡፡ ይህ ማለት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፓርላማው የተለያዩ ዘውጋዊ ውክልናዎች በአስተባባሪነት አብላጫ ድጋፍ እንዲወጣ ያደርጋል ማለት ነው፡፡ እንደ ክልላዊ ሥልጣን ከክልል ምርጫ የማይወጣው ፕሬዚዳንታዊ ሥልጣን የሚገኘው በሁሉም ክልል ቀጥተኛና አብላጭ ምርጫ ስለሚሆን በግድ መካከለኛነትን የሚይዝ ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ አድማስ ያላቸው የፖለቲካ ሰዎችን ይፈጥራል፡፡ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚካፈልበት አብላጫ ምርጫ የግል መብቶችን ከቡድን መብቶች ጋር አጣምሮ ከመግለጹም በላይ መካከለኛ አመለካከት ያላችውን ፖለቲከኞች ያመነጫል፡፡ ምክንያቱም ለፕሬዝዳንትነት የሚፎካከሩት ሁሉ ከራሳቸው ዘውግ ውጪ የሆኑ መራጮችን መማረክ አለባቸው፡፡ በአጭሩ የዚህ መፍትሄ መሰረታዊ አስተሳሰብ የዘውግን ፖለቲካ ከመከልከል ይልቅ በሂደት እንዲከስም በማድረግ ለሰላምና ለዴሞክራሲ የተሻለ ዋስትና ይሰጣል የሚል ነው፡፡

የብሔራዊ አንድነትንና የዘውጋዊ ማንነትን ሚዛን ለመጠበቅ አስፈላጊ ነው ተብሎ የሚወሰደው ማንኛውም መፍትሄ በአገሪቱ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ መሆን እንዳለበት መዘንጋት የለበትም፡፡ በማሻሻያ ሓሳቡና እና በአገሪቱ ሁኔታ መካከል የሚከሰተው ማንኛውም ልዩነት ከመዋቅራዊ ችግሮች እኩል ፈተና ሊሆን ይችላል፡፡ የፖለቲካ መሪዎች ሊፈጽሟቸው የማይችሏቸውን ተስፋዎች ሲያራግቡ አሁን ያለውን ብስጭት ያባብሳሉ፡፡ ይህ ደግሞ ለጽንፋዊ ቅስቀሳዎች አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ለምሳሌ ዴሞክራሲ የሚለውን ቃል የኢትዮጵያ የፖለቲካ መሪዎች፤ የመብት ተሟጋቾች፤ ታዛቢዎችና ተመራማሪዎች በብዛት ይጠቀማሉ፡፡ ነገር ግን ተመሳሳይ ፍች አይሰጡትም፡፡ ለኢትዮጵያ ችግሮች ሁሉ እንደ ተአምራዊ መፍትሄ ከመቅረቡ ሌላ በሀገሪቱ ከሚታዩት ተጨባጭ ሁኔታዎች የተፋታ በመሆኑ ዴሞክራሲ ሥራ ላይ ሊውል የሚችል ነገር አይመስልም፡፡ በመሆኑም በልሂቃኖችና በሰፊው ሕዝብ ዘንድ የዴሞክራሲ መንፈስ ወደ አሉታዊ አቋም ይቀየራል፡፡ ይህ ደግሞ ፍጹማዊ ካልሆነው በስተቀር አልቀበልም ማለትን ያስክትላል፡፡

ይህ ፍጹማዊውን ብቻ የመሻት ዝንባሌ የሚነሳው፤ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ተፈጥሮአዊ ባለመሆኑ፣ ብዙ ውጣ ውረድ ካለው የመማር ሂደትና ተፈጥሯዊውን ሰው ከሚገድቡና አንድ በአንድ ከሚገነቡ ተቋማት እንደሚገኝ ነው፡፡ የምዕራባዊ አገሮች ዴሞክራሲያዊ ሥርአትን ለማምጣት የሄዱበት ረጅምና ጠመዝማዛ ታሪክ ለዚህ ምስክር ነው፡፡ እንደ ሌሎቹ የአፍሪካ አገሮች፤ በኢትዮጵያ ውስጥም ያለው ችግር ከመገንባት ይልቅ ከምዕራቡ ቀድሞ የተሠራውን ማስመጣት መምረጣቸው ነው፡፡ ይህ የመቅዳት ልምድ ተግባራዊ ሊሆኑ ከማይችሉ መርሆች ጋር ኢትዮጵያውያን እንዲታገሉ ያደርጋቸዋል፡፡

በመሆኑም በልካቸው ያልተሰፋ ልብስ ለብሰው በመሄዳቸው ኢትዮጵያውያን ባገኙት አዲስ ነጻነት ቢደናበሩ ሊገርመን አይገባም፡፡እንደሚታየው የመበቀል ስሜትና ጽንፋዊ ማስፈራራት ከሚወልዷቸው የጥላቻ ንግግሮች ጀምሮ ሕዝቡን የጥላቻ ዘመቻ ውስጥ ለማስገባት ፖለቲካው ያለውን ሁሉ መርዝ እየረጨ ነው፡፡ ይህ ራሱን ገና ያልገራ አዲስ ነጻነት በጽንፈኛ ቡድኖች ብቻ ከተወሰነ አደጋው በጣም አነስተኛ ነው፤ ሆኖም ቁጥጥር ካልተደረገ በሽታው ሊሰራጭና ወደ ሕዝቡ ሊደርስ ይችላል፡፡ መሰራጨቱን ሊያመቻች የሚችለው ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነጻነትና ራስን ለማስተዳደር መብት እንግዳ መሆኑ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ተሃድሶ አራማጆች ስለዴሞክራሲ ሲያስቡ በፍጹማዊ ሳይሆን ራሱን ማረም እስከሚችልበት ጊዜ በአዝጋሚ ለውጥ የሚራመድ መሆኑን ቢገነዘቡ ችግሮቻቸውን በብዙ ያቃልላሉ፡፡

መሳይ ከበደ

University of Dayton

https://udayton.academia.edu/MessayKebede

# የኢትዮጵያ ሚዲያ ነቁልቁለት ጉዞ ቀጥሎ...

መለክ ቢ.

ዊሊያም ፒተር በኔሽን ሚዲያ ግሩፕ ከሚታተሙት ጋዜጦች አንዱ ለሆነው የኬንያው ዴይሊ ኔሽን ጋዜጣ ፍሪላንስ ዘጋቢ ነው። ባሳለፍነው ሳምንት አዲስ አበባ ውስጥ ለአራት ቀናት ቆይታ አድርጓል። ዊሊያምን ኢትዮጵያ ያመጣው ጉዳይ ካለፈው ረቡዕ ሜይ 1 እስከ ትናንት ሜይ 3 ድረስ በአዲስ አበባ የተከበረው የዓለም የፕሬስ ነጻነት ቀን ነው። ዊሊያም "የዓለም የፕሬስ ቀን አፍሪካ ውስጥ መከበር ካለበት ወይ አክራ አለያም ናይሮቢ እንጂ አዲስ አበባ መሆን አልነበረበትም" ይላል። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ "ኢትዮጵያ አሁንም በፕሬስ እድገቷ ምናልባት ኤርትራን ትቀድም እንደሆን እንጂ ከየትኛውም የአፍሪካ ሃገር ጋር ስትነጻጸር ኋላ ቀር ናት" የሚለው መደምደሚያው ነው። እንደዊሊያም አባባል የ100 ሚሊዮን ህዝብ ሃገር የሆነችው ኢትዮጵያ በሌሎች ሃገራት ለአንድ ከተማ ህዝብ እንኳን የማይበቃ የራዲዮ፣ የቴሌቪዥን እና የጋዜጣ ብዛት ይዛ ሳለ 'ሚዲያ አላት' ተብላ የዓለም የፕሬስ ነጻነት ቀን ሊከበርባት የምትችል ሃገር አይደለችም። "ሃገሪቱ አሁን ካላት ሚዲያ ይልቅ ከመላው አለም ይህንን በዓል ለማክበር ወደአዲስ አበባ የገቡት መገናኛ ብዙሃን በቁጥር ይበልጣሉ" ይላል ዊሊያም።

የጋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን አርታኢ የሆነው ኢማኑኤል ኒያምባ ግን በዊሊያም ሃሳብ አይስማማም። እንደኢማኑኤል ገለጻ በጋናም ይሁን በኬንያ የሚገኙ ሚዲያዎች ሙሉ በሙሉ ከባለቤቶቻቸው እና ከመንግስት ተጽዕኖ የተላቀቁ ናቸው ማለት ያስቸግራል። "ጋና በአሁኑ ወቅት ከ400 በላይ የራዲዮ ጣቢያዎች፣ 70 የቴሌቪዥን ጣቢያዎች እና 40 ዕለታዊ ጋዜጦች ያለባት ሃገር ሆና ሳለ ሚዲያዎቹ ከሚያስተዳድሯቸው የሃይማኖት ተቋማት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የመንግስት እና የግል ባለቤቶች ተጽዕኖ ሊላቀቁ አልቻሉም" ይላል ኢማኑኤል።

ይህ ጋዜጠኛ እንደሚለው የዓለም የፕሬስ ነጻነት ቀን በኢትዮጵያ እንዲከበር ምክንያት የሆነው በሃገሪቱ ያለው የዘመናዊ ሚዲያ ዕድገት እና ብዛት ሳይሆን ጋዜጠኝነት ወንጀል ሆኖ የኖረባት ኢትዮጵያ ዛሬ በአንጻራዊነት ከዚህ የፕሬስ ሲዖልነት መላቀቋ ነው። ኢማኑዔል አስተያየቱን ሲቀጥል እንዲህ ይላል። "ኢትዮጵያ ያሰረቻቸውን ጋዜጠኞች መፍታቷና ያባረረቻቸውን ጋዜጠኞች ወደሃገር ቤት መመለሷ እንዲሁም በታሪኳ ምንም ጋዜጠኛ ሳይታሰር እና ሳይሰደድባት አንድ አመት ማሳለፍ መቻሏ ለዩኔስኮ የፕሬስ ቀን መከበር ምርጫ ብቁ ያደርጋታል። ከዚህ በተረፈ ግን በኢትዮጵያ ያለው ሚዲያ አሁንም እንኳን ለጠቅላላ ህዝብ ቀርቶ ለአዲስ አበባ ከተማ እንኳን በቂ ነው ማለት አይቻልም። በብዙ መንገድ ስልጣኔ ከአፍሪካ ቀድሞ የደረሳት ኢትዮጵያ በዚህ ዘመን የአነስተኛ መጠን እና ብዙም ያልዘመነ ሚዲያ ባለቤት መሆኗ የሚመጥናት አይደለምና ደስ አይልም" ብሏል።

ሁለቱም ጋዜጠኞች የኢትዮጵያ ሚዲያ ውግንና አልባ ዘገባ ለማቅረብ እና የተደራሲውን እምነት ይዞ ለመቀጠል አሁን ባለበት ደረጃ ብቁ ባለመሆኑና በተለይም ከዘመናዊ አወቃቀርና ተቋማዊ ቅርጽ ይዞ ከመጓዝ ጋር እጅግ ብዙ ርቀት የሚጠብቀው በመሆኑ ላይ ይስማማሉ። እንደሁለቱም አባባል ኢትዮጵያ ሚዲያ እና

> በኢትዮጵያ የህትመት እና ብሮድካስት ሚዲያ ታሪክ ከ1983 ዓ.ም የመንግስት ለውጥ በኋላ የነበረው ጊዜ የኢትዮጵያ ሚዲያ ኢንዳስትሪ ገና ማበብ የጀመረበት ወይም "ሚዲያው እንደአዲስ ማቆጥቆጥ የጀመረበት ወቅት" ነበር ተብሎ ቢጠቀስ ስህተት አይሆንም።

ጋዜጠኝነት ገና ከዳዴ ጉዞ ያላለፈባት ሃገር ናት። ለዚህ ደግሞ በየደረጃው የነበረው የመንግስት አስተዳደር ቀዳሚ ተጠያቂ ነው ይላሉ።

የዛሬው ርዕሰ ጉዳያችን ሰሞኑን በተባበሩት መንግስታት የሳይንስ፣ የባህል እና የትምህርት ድርጅት ዩኔስኮ እና በኢትዮጵያ መንግስት የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ ከነበረውና ለሶስት ቀናት ከተካሄደው የዓለም ፕሬስ ነጻነት ቀን ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ የሚዲያ ነጻነት እና ጉዞ ምን ይመስላል የሚለውን በመጠኑ ይቃኛል።

## የሚዲያ ነጻነት በኢትዮጵያ

ስለኢትዮጵያ ሚዲያ ነጻነት ካወራን ልናወራ የምንችለው ከ1983 ዓ.ም በኋላ ያለውን ጊዜ ብቻ ነው። ከዚያ በፊት የነበረው ዘመን ከፕሮፓጋንዳ ማሽንነት በዘለለ የሚዲያ ነጻነት ቀርቶ የሚዲያ ታሪክ በቅጡ ሊነገርበት በሚችል ደረጃ የተደራጀ ስላይደለ እዚህ ላይ ቃላት ከመከመር ውጪ ረብ ያለው ነገር ከውስጡ ማውጣት ይከብዳል።

በኢትዮጵያ የህትመት እና ብሮድካስት ሚዲያ ታሪክ ከ1983 ዓ.ም የመንግስት ለውጥ በኋላ የነበረው ጊዜ የኢትዮጵያ ሚዲያ ኢንደስትሪ ገና ማበብ የጀመረበት ወይም "ሚዲያው እንደአዲስ ማቆጥቆጥ የጀመረበት ወቅት" ነበር ተብሎ ቢጠቀስ ስህተት አይሆንም።

ይህ ከሆነ ዘንዳ በኢትዮጵያ የሚዲያ ነጻነትን በ3 የተለያዩ ጊዜያቶች ከፍሎ ማየቱ ይጠቅማል። ቀዳሚው የኢህአዴግ መንግስት ሃገሪቱን መምራት ከጀመረበት 1983 ዓ.ም ተነስተን እስከ 1996 ዓ.ም መጨረሻ አካባቢ ድረስ የምንዘልቅበት 13 ዓመታት ነው። ሁለተኛው ዘመን በኢትዮጵያ "መሬት ያንቀጠቀጠ ምርጫ" ከተካሄደበት ከ1997 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ ኢህአዴግ በውስጥ ተሃድሶ ዳግም በአዲስ አስተዳደር እስከተከሰተበት 2010 ዓ.ም አጋማሽ ድረስ ያለውን የ14 ዓመታት ጊዜ ያካትታል። ቀሪው አሁን ያለንበት እና ገና አመት የደፈነውን የአዲሱ ኢህአዴግ አስተዳደር ዘመን ፕሬስ የሚቃኝ ይሆናል።

በዚህ ስሌት መሰረት ካየነው የሶስቱ ዘመን የኢትዮጵያ ፕሬስ ጉዞ ከወጣ ገባ ሂደት ▶

ያልተሳቀቀና በሚፈለገው መጠን የፕሬስ እድገት በኢትዮጵያ እንዳይመጣ እንቅፋት ተደንቅሮበት ለአዝጋሚ ጉዞ የተዳረገበት ጊዜ ነው፡፡

## የ1983–96 የፕሬስ ዘመን

ኢህአዴግ በዴሞክራሲ አስተሳሰብ ራሱን እያሸ መንግስት መሆን ሲጀምር በሙሽርነቱ የፈጠረውን የማገዶ እሳት ነጻነት ፕሬሱ ቀድሞ ሞቆታል፡፡ አስቀድሞ እንደአዲስ መንግስት የቀድሞው መንግስት ህዝቡን ያሳጣውን መብት በመተግበር “አለሁልህ” ማለትን ስለመረጠ ኢህአዴግ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን እውቅና ሰጥቶ ፕሬሱ በለውጡ ማግስት እንዲያብብ መንገድ ከፍቷል፡፡ የኢትዮጵያ ህገመንግስት ከመውጣቱ አስቀድሞ በ1985 ዓ.ም የመረጃ ነጻነትና የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 34/85ን አጽድቋል፡፡ በ1987 ዓ.ም ህገመንግስቱን ሲያጸድቅ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን በመደንገግ የማይጣስ እና ገደብ የማይደረግበት መብት ነው ብሏል፡፡

ይህ ለጊዜው ፕሬስ ወዳድ የመሰለ አስተዳደር እነዚህን መብቶች ሲሰጥ በዴሞክራሲ ስም “ዴሞክራሲን በመለማመድ ሂደት ላይ ያጋጠሙ ናቸው” የተባሉ አንዳንድ ጥፋቶች ያስከተሉት ችግር እንደነበርም የሚዘነጋ አይደለም፡፡ የቅድመ ምርመራ (ሴንሰርሺፕ) ተነስቶ መንግስት በማንኛውም በሚጻፍ ጉዳይ ላይ ጣልቃ መግባቱን ትቶትም ነበር፡፡ ብስራት ወልደገብርዔል ሃንዲሶ የተባሉ ጸሃፊ censorship in Ethiopia በሚለው መጽሃፋቸው ይህንን የቅድመ ህትመት ምርመራ የሃሳብ ዘር ማጥፋት (Genocide of thought) በማለት እንደገለጹት ሁሉ ይህ መረጃዎች አስቀድሞ ይፋ ከመውጣታቸው በፊት የሚመረመሩበት ሂደት በኢትዮጵያ የመረጃ ነጻነት ላይ አሉታዊ ጥላ ጥሎ የቆየ እንደነበርም አይዘነጋም፡፡

በዚህ ዘመን የሃሳብ ነጻነት ህግ አተገባበር ያለምንም ተጽዕኖ የተከናወነ ነበር ለማለት እና ከመንግስት ቁጥጥር ሙሉ ለሙሉ ወጥቶ የነበረ ነው ባይባልም ቢያንስ ህግ ተበጅቶለት የተከበረ መሆኑ በራሱ በበጎ ጎን ሊወሰድ ይችላል፡፡ ይህ አካሄድ የነጻ ፕሬስ መንፈስ ተነቅሎ ብዛት ያላቸው የፕሬስ ውጤቶች በነጻ መንፈስ ስራ ላይ እንዲውሉ ምክንያት ሆኗል፡፡ በጊዜው በብሮድካስት በኩል ያለው ፍቃድ ሙሉ በሙሉ ዝግ ቢሆንም በህትመት ሚዲያ ረገድ ግን  ለአንባቢው ግን በምርጫ የቀረቡ ብዛት ያላቸው ውጤቶች ነበሩ፡፡ በዚህ ዘመን ብቻ በኢትዮጵያ ታሪክ ቀድሞም ያልነበረ ኋላም ያልተደገመ የህትመት ውጤት ቁጥር ተመዝግቧል፡፡ ለምሳሌም 1985 ዓ.ም ብቻ በኢትዮጵያ ውስጥ 28 ጋዜጣና 65 መጽሄቶች በህትመትና ስርጭት ላይ ነበሩ፡፡ በዚህ ዘመን የሚታተሙ መጽሄቶች እና ጋዜጦች በአብዛኛው ከፕሮፌሽናል ስራ ይልቅ ሴንሴሽናል የሚባለው የጋዜጠኝነት ዘውግ ላይ ያቆሙ በመሆናቸው ፣ በሌላም በኩል ሲመሰረቱ በአብዛኛው የቀድሞ መንግስት ጦር አባላት የነበሩ እና ከስነጽሁፍ ጋር የተያያዘ ችሎታ የነበራቸው ሰዎች እጅ ላይ የብዙ ህትመት ባለቤትነቶች በመግባታቸው የጋዜጠኝነት ጅምሩ በመፋጠጥ (ሚሊታንሲ) ዘውግ ሆኖ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የወሲብ፣ አለያም ጭልጥ ያለ የተቃውሞ ፖለቲካ እና በብዛት ደግሞ ያልተረጋገጡ መረጃዎች መታተም መጀመራቸው ግራ አጋቢነቱ በመጨመሩ ህብረተሰቡ በራሱ ሰላማዊ ሰልፍ ወጥቶ አንዳንድ መጽሄቶች እና ጋዜጦች እንዲታገዱለት እስከመጠየቅም ደርሶ ነበር፡፡

በ1986 ዓ.ም ከአመት በፊት የነበሩት መጽሄቶች ቁጥር ከ 65 ወደ 38 መውረዱም የዚህ አንዱ መገለጫ ነው፡፡ እንዲያም ሆኖ ለውጥ ማምጣት የቻሉ እና መንግስትን ወደመስመር የከተቱ ብዛት ያላቸው የፕሬስ ውጤቶችም እንደነበሩ ሳይዘነጋ፡፡ በዚህ ዘመን የነበረው የፕሬስ ውጤት አንድም በራሱ ሌላም በመንግስት የማይታዩ እና ይፋ ያልወጡ ጫናዎች ቢያዳክሙትም አደጋ ውስጥ የገባው ግን ምርጫ 97 ሲቃረብ ሆነ፡፡

## ፕሬስ ከ1997–2010

ኢህአዴግ ደብቆ ያቆየውን ፕሬስ ጠል ስትራተጂ ደረጃ በደረጃ መዘርጋት የጀመረው በዚህ ጊዜ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ ዴሞክራሲያዊ ነበር የተባለው ፣ መዘዙ ግን የብዙዎችን ህይወት ቀጥፎ እና ከባድ ተቃውሞ አስነስቶ ህዝብንና ኢህአዴግን ለ13 ዓመታት በከባድ ቅራኔ ውስጥ ያኖረው ምርጫ 97 በዚያ መጠን ህዝቡ ኢህአዴግ ላይ ጣቱን ቀስሮ በምርጫ ካርድ እንዲባረር ለማድረግ ጫፍ መድረሱ የፕሬሱ ቅስቀሳ ውጤት ነው ብሎ አምኗል፡፡ በዚህ መሰረትም ጋዜጠኞችን ሰብስቦ በማሰር እና ሁሉንም አካል ከቅንጅት ጋር ደርቦ በመክሰስ በኢትዮጵያ የፕሬስ ታሪክ የማይረሳ ጠባሳ አሳረፈ፡፡ በምርጫው ሰሞን ከፍ ያለ መረጃን የማቀበል እና ህብረተሰቡን የማንቃት ስራ ያከናወኑትን ጋዜጦች እና መጽሄቶች ባለቤቶች በሙሉ አስሮ “በሃገር ክህደት ወንጀል” መክሰሱ የዚህን መንግስት አደገኝነት ያሳየ ሆነ፡፡ ይህ ፍርዱ ሞት የሆነ አንቀጽ እንደወታደር ጋዜጠኞች ላይ ተግባራዊ ለማድረግ ቢሞከርም፤ ከአለምአቀፉ ማህበረሰብ እና ከሃገር ውስጥ በተደጋጋሚ ጊዜ የደረሰበት ወቀሳ ታሳሪ ጋዜጠኞችን “ይቅርታ ጠይቀው እንዲወጡ” እንዲያደርግ ገፍቶታል፡፡

ይህ ከሆነ በኋላ ኢህአዴግ የፕሬስ ማነቆውን እያጠበቀ፣ የጠላቸውን የሚበቀልበትን መንገድ እያመቻቸ፣ እያስፈራራ፣ እያሳደደ እና እያባረረ አብቦ ነበር የተባለውን ፕሬስ ለማጠውለግ አመት አልፈጀበትም፡፡

በመጠነኛ ሁኔታ ታይቶ የነበረውን የፕሬስ ነጻነት ሙሉ በሙሉ በመዝጋት ባይባልም እያለ እንዳይኖር በማድረግ መንግስትን መተቸት የማይሞከር እስኪመስል ድረስ በኢትዮጵያ ጋዜጠኝነትን ከባድ አድርጎታል፡፡ ብዙ ጋዜጠኞች ሃገር ለቅቀው ተሰድደዋል፡፡ ብዙዎች በኢኮኖሚ ችግሮች ተመትተው ከገበያ ወጥተዋል፡፡ ብዙዎች በተመሳሳይ ሁኔታ በመንግስት ተከስሰው እና ተፈርዶባቸው በወህኒ ቤቶች ስቃይን ተቀብለዋል፡፡ ሚዲያ ተቋማት ተዘግተው ያሉትም እንዳይሰሩ መረጃ ተነፍገው እና ታስረው ተንገታግተዋል፡፡ የሃሳብ ነጻነት የሚሞትለት እና የሚደማለት የሌለበት ሃገር ተፈጥሮ መንግስት በፈለገው መንገድ ሚዲያው ላይ ጢባጢቢ ተጫውቷል፡፡ ይህ ዘመን ፕሬሱ አለሁ ለማለት ብቻ ቢኖርም በከባድ አደጋ ውስጥ ወድቆ እንደሌለ ሆኗል፡፡ የኮምፒውተር ወንጀሎች አዋጅ፣የብሮድካስት አዋጅ፣ የጸረሽብር ህግ አዋጅ፣ ወዘተ ፕሬሱን ለማፈን ሆን ተብለው የተቀረጹና በሌላ አነጋገር በሃሳብ ነጻነት ላይ የተዘረጉ ልጓሞች ነበሩ፡፡

በዚህ ሳቢያ ሁለት ከባድ ችግሮች ተከሰቱ፡፡ አንደኛው ብዙ ልምድ ያለውና ፕሬሱን በሚገባ የሚያውቀው ጋዜጠኛ አንድም ከሃገር ተሰደደ አለያም ወደመዝናኛ ጋዜጠኝነት ሸሸ፡፡ የዚህችን ሃገር ውሎ በሚወስኑ እና መንገዷን በሚቀርጹ የዕለት ከዕለት ኮሙኒኬሽን ውጤቶች ላይ ገና ያልበሰሉ እና በሙያው ብዙም ልምድ የሌላቸው ሰዎች ወሳኝ ሆነው ሲመጡ በዚያው መጠን የጥራት እና ተዓማኒነት ማጣት አደጋው ሰፋ፡፡ ከመንግስት ድጋፍ ሙሉ በሙሉ የተሰረዘው ፕሬሱ የማተሚያ ወረቀት እና የህትመት ዋጋ መናር በፈጠረው ጦስ ተመታ፡፡ በገበያው ውስጥ የማስታወቂያ ማጣት ያስከተለበት ሁሉንም ከራስ ኪስ መሸፈን ጉዳይም ዘርፉን አቀጨጨው፡፡ ብዙዎችም ጠፉ፡፡

በዚህ ዘመን ልናወራ የምንችለው ጥቂት የሚጠቀስ አወንታዊ ነገር ካለ የብሮድካስት አዋጅ ከወጣ በኋላ በጥብቅ ክትትል ስር እና መመሪያ ቢሆንም አንዳንድ የራዲዮ ጣቢያዎች ተከፈቱ፡፡ የቴሌቪዝን ፍቃድም መሰጠት ተጀመረ፡፡

## ፕሬስ ከ2010 በኋላ

የቲም ለማ ዘመን መጥቶ የዶክተር ዐቢይ አስተዳደር ወንበሩን ከተቆጣጠረ በኋላ የወሰዳቸው እርምጃዎች ሙሉ በሙሉ ከቀደመው የኢህአዴግ አዲስ አበባን መቆጣጠር ጋር ተመሳሳይ ነበሩ፡፡ ያኛው የኢህአዴግ አስተዳደር ህዝቡን የነፈገውን መብት ወዲያው መመለስ፡፡

ከነዚህ የዶክተር ዐቢይ ስራዎች አንዱ መገናኛ ብዙሃንን እና ጋዜጠኞችን ከተመሰረተባቸው ክስ እና ቅጣት ነጻ በማድረግ ወደስራቸው እንዲመለሱ ማድረግና የሚዲያውን ኢንደስትሪ ከ“እግር ከወርች” ማላቀቅ ነበር፡፡ በዚህ መነሳሳት ሳቢያ በሃገር ውስጥ ተዳክሞ የነበረው የፕሬስ ህትመት ሲነቃቃ በአንጻሩ በውጭ ሃገር የነበሩ የብሮድካስት ሚዲያ ተቋማትም ሃገር ቤት ገብተዋል፡፡ የተሰደዱ ጋዜጠኞች ወደሃገራቸው ተመልሰዋል፡፡ ለዘመነ ኢህአዴግ አስተዳደር የጎን ውጋት ሆኖ የኖረው እና በአስተዳደሩም ቀንደኛ አሸባሪ ሚዲያ ተብሎ የተፈረጀውን ኢሳትን ጨምሮ ተደራሲውን በዋናነት አንድ

ቀሪውን በ ገጽ 27 ይመልከቱ



መሳይ መኮንን

## ከአሜሪካ እስከ አሜሪካ

# በተስፋችን ላይ ጽልመት የጋረደው የዘር ፖለቲከኞች ጩኸት !

### ክፍል አምስት

የሚሌኒየሙ የኢሳት በዓል ታሪካዊ ሆኖ አልፏል። ለሁላችንም የማይረሳ ትዝታ በልባችን መንበር አስቀምጦልናል። ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚደርሱን መልዕክቶች የሚያረጋግጡትም የኢሳት ቀን በአዲስ አበባ ዳግም ኢትዮጵያዊነትን ማንገሱን ነው። ኢሳት ባለበት፡ በተገኘበት ኢትዮጵያ ስሟ ከፍ ይላል። የዘር በሽታ ስጋዋን እየበላት ያለች ሀገራችን መቼም ጠፍታ እንደማትቀር የተስፋ ብልጭታ ያየችበት ዕለት ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም። ኢትዮጵያዊነት በመከራ የሚፈተን፡ ሲመቱት ይበልጥ የሚጠብቅ ማንነት ነው። ኢትዮጵያዊነት በዘር ልክፍት ልቦናቸው በታወሩ፡ በጎጥ አስተሳሰብ ህሊናቸውን ባጡ ጥቂቶች ጩኸት የሚፈርስ አይደለም። ትላንት ወራሪዎች ለማድረግ ሞክረውት ያልተሳካላቸውን የኢትዮጵያን መበታተን ዛሬ በገዛ ልጆቿ አጀንዳው እየተገፋ ቢሆንም በቀላሉ እጅ የምትሰጥ አልሆነችም። የእናት ሆድ ዥንጉርጉር ሆነና የሚታደጓትንም ልጆቿን ማህጸኗ አልነፈጋትም። ለአንድነቷና ለክብሯ ዘብ ሊቆሙ ከተነሱላት ልጆቿ ኢሳት ውስጥ የተሰባሰብነው ልንጠቀስ እንችላለን ብዬ በድፍረት እናገራለሁ። ያገናኘን ኢትዮጵያዊነት ነው። ስንዘምር የቆየነው ኢትዮጵያዊነትን ነው። ይህ ማንነት ማህተባችን ነው። አንገት የሚያስደፋ ሳይሆን በኩራት ቀና የሚያደርገን ማንነት። ለዚህ ማንነት ክብር የትኛውንም ተራራ እንወጣለን። ማንኛውንም ዋጋ እንከፍላለን። ይህ ቃልኪዳናችን ነው። ለራሳችን የገባነው፡ ለልጆቻችንም የምናስተላልፈው ክቡር ቃል። በሚሌኒየም አዳራሽ በህዝብ ፊት ያስከበረንም ይህንኑ ቃላችንን ጠብቀን በጽናት በመዘለቃችን ነው።

የዚያን ዕለት ጥሩ እንቅልፍ ተኝቼ አደርኩ። አዲስ አበባ በደንብ ሞሽራናለች። አክብራ አንግሳናለች። የጫጉላ ሽርሽራችን ደግሞ በሌሎች ከተሞች ይሆናል። በመጪዎቹ ሳምንታት ወደተረኞቹ ከተሞች ተጉዘን ወገናችንን እናገኛለን። በሕወሓት የጎሳ ፖለቲካ የተነሳ ኢትዮጵያዊነት የተመቱባቸው አካባቢዎች ላይ ትኩረት አድርገን በመጓዝ የወገናችንን ትንፋሽ እናዳምጣለን። ህመሙን ተጠግተን እንታመመዋለን። ጂጂጋ፣ አፋር ሰመራ፣ ጋምቤላ፣ ሀዋሳ፣ ጎንደር፣ ባህርዳር፣ አዳማ፣ ጂማ፣ አርባምንጭ ጊዜው እንደፈቀደልን፤ ሁኔታዎች እንዳመቹልን የማንደርስበት የኢትዮጵያ ክፍል አይኖርም ብለን ተነስተናል። መቀሌም ቢሆን ከእቅዳችን ውጪ አልሆነችም። ከዋሽንግተን ዲሲ ከመነሳታችን በፊት ስለጉዞአችን በተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ይኸው የመቀሌ ጉዳይም ተነስቶ በእኛ በኩል "ሁሉም ቦታ ሀገራችን ነው፤ የሚከለክለን ማንም ሃይል አይኖርም " የሚል ምላሽ መሰጠቱን አስታውሳለሁ። መግለጫ ለማሳመር የተደረገ ዲስኩር ሲሉ የተሳለቁብንም ነበሩ። "ኢሳት የትግራይ ህዝብ ጠላት" የሚል ታፔላ የለጠፉብን የሕወሓት አጋፋሪዎች ከወዲሁ የማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ መዓት ማዥጎድጎድ ጀምረዋል። የሕወሓት ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች የዘር ፖለቲካ አቀንቃኞችም ''እኛ ጋ ትመጡና እንተያያለን'' ዓይነት መልዕክቶችን በማህበራዊ ሚዲያዎች ማሰራጨታቸውን እየታዘብን ነው።




ኢሳት መለያው የኢትዮጵያ አንደነት ነው። በኢሳት ሰማይ ኢትዮጵያዊነት እንጂ ከዚያ ዝቅ ያለ ማንነት ገንኖ የሚወጣ አይደለም። ኢትዮጵያውያን የብሄር ማንነታቸው፣ ቋንቋ ባህላቸው ተከብሮ፣ በፍቅር የሚኖሩባት አንድ ሀገር እንዲኖራቸው ነው የኢሳት ህልምና ተስፋው። ''ጋሞነቴ ከኢትዮጵያዊነቴ ተጋጭቶብኝ አያውቅም'' የሚለው የጋሽ አሰፋ ጫቦ ድንቅ አባባል የኢሳትን መስመር በትክክል የሚገልጸው ይመስለኛል። የብሄር ማንነት ከኢትዮጵያዊነት ጋር መላተም የለበትም። አንዱ በአንደኛው ውስጥ የሚኖር እንጂ የአንዱ መኖር ሌላኛውን የሚያጠፋ ሊሆን አይገባውም። የዘመኑ የዘር ፖለቲካ አራማጆች የሳቱት እውነት ይህንን ነው። ኢትዮጵያዊነት የብሄር ማንነታችንን ሊቀማን ነው ከሚል የተወላገደ አስተሳሰብ ላይ ቆመው ኢትዮጵያ ብለው የሚንቀሳቀሱ ተቋማትንና የፖለቲካ ሃይሎችን እንደጠላት ፈርጀው ሲራገሙ ማየት የተለመደ ሆኗል። አዲስ ብሄርተኛ ወደ መድረኩ ብቅ ሲል ሀሁ ብሎ የሚጀምረው ኢትዮጵያዊነትን በማንኳሰስ ነው። በግድ የተጫነብን ማንነት ሲሉም በድፍረት የሚናገሩን ሰምተናል። እንደነዚህ ዘመን አመጣሽ፣ ወፍ ዘራሽ አስተሳሰቦች ኢትዮጵያን ብለው ለተነሱ ኢትዮጵያውያን ተቋማት ብርቱ ፈተና ሆነው ተደቅነዋል።

ኢሳት አንዱ የዚህ አስተሳሰብ ሰለባ ነው። በዚህ አስተሳሰብ የተሸነፉ የዘር ፖለቲካ አቀንቃኞች ኢሳትን የብሄራቸው ጸር ነው የሚል ድርጅታዊ መግለጫ እስከማውጣት መድረሳቸውን ታዝበናል። በኢትዮጵያ ቆይታችን ከመነሻው ዳር ዳር ማለት የጀመረው ''ወደእኛ ትመጡና ወየውላችሁ'' ዓይነት ማስፈራሪያ በሚሊኒየም አዳራሽ ከተሰጠን ክብርና አድናቆት ጋር ባይገናኝም አንገታችንን ግን አላስደፋንም። በእነዚህ የዘር ፖለቲካ አቀንቃኞች ዛቻና ፉከራ የሚቆም የኢሳት ጉዞ አልተጀመረም። መንግስታዊ ቁመና ይዞ፣ እስከአፍንጫው የታጠቀ ሰራዊት አሰልፎ፣ የሀገሪቱን ገንዘብና ሀብት ተቆጣጥሮ ለእኛ መጥፋት አያሌ ሙከራዎችን ላደረገው የሕወሓት አገዛዝ እንኳን የተሰበረ አንገት የለንም። ልባችን ሙሉ ነው። ወኔአችን እንደብረት የጠነከረ ነው። ኢትዮጵያ ብለን ወጥተናል። ኢትዮጵያዊነትን ከትልቁ ማማ ላይ ሰቅለን እንጂ ከዚያ ሳንደርስ የሚያቆመን ምድራዊ ሃይል ከቶም ሊኖር አይችልም። ለማንኛውም ነገሮችን በሂደት እያየን ለማከናወን ወስነን የኢትዮጵያ ቆይታችንን ቀጥለናል።

በማግስቱ እሁድ ነው። የካቲት 10። አዲስ አበባ ብሩህ ቀን ገጥሟታል። ጸሀዩ ቢበረታም ምቾት የሚነሳ አይደለም። ባልደረባዬ ሲሳይ አጌና በትውልድ ሰፈሩ የአቀባበል ፕሮግራም በመዘጋጀቱ አጅቤው እንድሄድ ጠየቀኝ። አላመነታሁም። ሽሮ ሜዳ ቀልጣ ጠበቀችን። ከመነን ትምህርት ቤት የጀመረ ከሶስት ኪሎሜትር በላይ በቀኝና በግራ ህዝብ በረድፍ ተሰልፎ ተቀበለን። በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያሸበረቀው፣ በጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና ፎቶግራፎች የደመቀው አቀባበል ልዩ ነበር። ዳርና ዳር፣ በንግድ ቤቶች ደጃፍ ►

የተኮለኮለው ህዝብ እጆቹን እያወዛወዘ ሰላምታውን ከአድናቆት ጋር እያቀረበልን ስናይ ስሜታችንን መቆጣጠር አቃተን። የትላንቱ የሚሊኒየም አዳራሹ ዓይነት ስሜት ወረረኝ። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ሲሳይን አስመልክተው የተናገሩት አጭር መልዕክት በጽሁፍ የታተመበትና የሲሳይ ምስል የሚታይበት ቲሸርት ሰዉ በነፍስ ወከፍ ለብሶታል። የሽሮ ሜዳ ነዋሪ ቤቱ የቀረ ያለ አይመስልም። የአካባቢው ወጣት በሚገባ ተዘጋጅቶ ያሰናዳው የአቀባባል ፕሮግራም ለመሆኑ ድምቀቱና ስነስርዓቱ ይመሰክራሉ። የእኔን መምጣት ያላወቀው የሽሮ ሜዳ ነዋሪ ወደ ተንጣለለው ድንኳን ስንገባ ስሜን በመጥራት በሞቀ ስሜት ተቀበለኝ።

የሽሮ ሜዳው የሲሳይ አጌና አቀባበል ፕሮግራም መለስተኛው የሚሌኒየም አዳራሽ ትዕይንት ቢባል ያስኬዳል። ሲሳይን ያሳደጉ እናትና አባቶች፣ አብሮ አደግ ጓደኞች፣ በሲሳይ ስራ አድናቆት ለመስጠት የመጡ በርካታ ሰዎች በታደሙበት ፕሮግራም በአዘጋጆቹ የተለያዩ ዝግጅቶች ቀረቡ። በተለይ ስለሲሳይ የልጅነትና የጉልምስና ጊዜ፤ እንዲሁም አሁን እያበረከተ ስላለው ሀገራዊ ተግባር በአንድ አባት የቀረበው መግለጫ መሳጭ ነበር። ሲሳይ አጌና በትውልድ መንደሩ አርዓያ ተደርጎ የሚታይ ለመሆኑ የሚያስረግጡ ምስክርነቶች በተለያዩ ሰዎች ቀረቡ። እኔም እንደሙያ ባልደረባነቴና የትግል አጋርነቴ ሲሳይን የሚገልጽ አጭር ንግግር አደረግሁ። የአቀባበል ፕሮግራሙ ከማብቃቱ በፊት ሲሳይ በሰፈር ውስጥ ያሳደጉትና በህመም ምክንያት በአካል መገኘት ያልቻሉትን ቤት ለቤት እየሄደ ጠየቃቸው። የሽሮ ሜዳው የአቀባበል ስነስርዓት በጥሩ ሁኔታ ተጠናቆ ወደ ሆቴላችን ተመለስን።

የኢሳት የልዑካን ቡድን ወደ ተለያዩ ከተሞች ከመንቀሳቀሱ በፊት በአዲስ አበባ ለቀናት ይቆያል። ከወዲሁ ግብዣዎች በርክተው መጥተዋል። ሳምንቱን ሙሉ የምሳና የእራት ፕሮግራሞች ተይዘዋል። በጣም የተጣበበ ጊዜ በመሆኑ የተወሰኑ የግብዣ ጥሪዎችን መቀበል አልቻልንም። ለቃለመጠይቅ በሚፈልጉ ሚዲያዎች ስልካችን ስራ በዝቶበታል። በመጽሀፍ ምርቃት መድረኮች እንድንገኝላቸው የሚጠይቁንም ቁጥራቸው ቀላል አልነበረም። የሚጎርፍልን አድናቆት፣ የሚቀርብልን ግብዣ፣ እዚህም እዚያም በሰዉ የሚደረግልን ልዩ አቀባበል ቃላት ከሚገልጸው በላይ ሆኖብኛል። የምንችለውን ያህል እየመለስን ነው። ከባለሀብቶች፣ ከታዋቂ ሰዎች፣ ከመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናትና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የሚያገናኙን በርካታ ፕሮግራሞች ከፊታችን ይጠብቁናል። የኢትዮጵያ ጉዞአችን አንዱ ዓላማም ይኸው ነበር።

አራተኛው ቀናችን የካቲት 12 ላይ አርፏል። የኢሳት የልዑካን ቡድን አባላት በዕለቱ ለየካቲት 12 ሰማዕታት ክብር ለመስጠት የአበባ ጉንጉን የሚያኖሩበት ፕሮግራም ተዘጋጅቷል። ዛሬን የደረስነው የአያት አባቶቻችን ሕይወት መስዋዕት መሆኑን ከሚመሰክሩ ታሪኮች አንዱ የካቲት 12 ነው። ኢትዮጵያዊነት ሕይወት የተገበረለት፣ ከደምና አጥንት ዋጋ የተከፈለለት ለመሆኑ የየካቲት 12 ሀውልት መሀል አዲስ አበባ ቆሞ ታሪክን ይነግረናል። በጨካኙ የፋሺስት ጄነራል ግራዚያኒ ትዕዛዝ የተጨፈጨፉት አያት አባቶቻችን ታሪካቸው ህያው ሆኖ ለትውልድ ይተላለፍ ዘንድ የየካቲት 12 ሀውልት ስድስት ኪሎ አደባባይ ላይ ቆሟል። ያን ጊዜ ኢትዮጵያውያን ሞታቸው አንድ ነበር። ስለኢትዮጵያ ሲሉ ያንን መራር የሞት ጽዋ ተጎንጭተዋል። ዘር አልተቆጠረም። ክርና ማህተብ አልተፈተሸም። ኢትዮጵያዊነት ከዘርም በላይ ነው። የያኔዎቹ ኢትዮጵያውያን ሞታቸው እንኳን አልተለየም።ይህቺን ምድር በግፍ ሲሰናበቱ ከኢትዮጵያዊ ክብራቸው ጋር ነበር። የእምነት ልዩነት ያልበጠሰው፣ የዘር ድንበር ያልገደበው ኢትዮጵያዊ ክብር የተገለጠበት መስዋዕትነት ነበር የካቲት 12 ላይ የተከፈለው። ዛሬ በቀላሉ አልደረስንም። በታሪክ ምንጣፍ ተራምደናል። ትላንት ባይኖር ዛሬን አንኖርም። የትላንቶቹ አባቶቻችን ማዲያት መገለጫ ነን። የጥሩም የመጥፎም አሻራቸው ውጤቶች ነን። የካቲት 12 ይህንን ሀቅ ሲመሰክር ይኖራል። ለእነዚያ ታላላቅ ኢትዮጵያውያን መስዋዕትነት ከቆመው ሀውልት የደረሱት የኢሳት የልዑካን ቡድን አባላት የተዘጋጀውንና የኢሳት ስም የሚታይበትን የአበባ ጉንጉን አኖሩ። ክብር ለሚገባው ክብር መስጠት የትውልድ ሃላፊነት ነው።

በሚቀጥሉት ቀናት በተለያዩ ፕሮግራሞች አሳለፍን። የምሳና የእራት ግብዣዎቹ እንደተጠበቁ ናቸው። በዚያው ሳምንት ውስጥ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር አንድ አዲስ ቴአትር እንድመለከት ተጋብዘን ነበር። በተክሌ ደስታ የተደረሰውና ታላቆቹ አርቲስቶች የተሳተፉበት “መንታ መንገድ” የተሰኘውን ባለሙሉ ጊዜ ቴአትር ተመለከትን። ለምን እንደሆነ ቴአትር ቤት አይቀናኝም። በህይወቴ ቲያትር ቤት ስገባ ለሁለተኛ ጊዜ መሆኑ ነው። ከ17 ዓመት በፊት “ውበትን ፍለጋ” የተሰኘውን የጌትነት እንየውን ቴአትር በአንድ ወዳጄ ጉትጎታ ተመልክቼአለሁ። ከቴአትር ይልቅ ለፊልም ቀልቤ ያደላል። ቲያትር አድካሚ ስራ መሆኑን ያወኩትም ውበትን ፍለጋን ከተመለከትኩ በኋላ ነው። በመንታ መንገድ ቴአትር ዋናውን ገጸባህሪ የሚጫወተው ሽመልስ ነው። ከኢትዮጵያ የቴአትር ባለሙያዎች ሽመልስ የእኔ ምርጫ ነው። የምር የሙያው ደም አለው። የሽመልስ አበራ የትወና ብቃት በእጅጉን መስጦኛል። በመንታ መንገድ ቴአትር ላይ የአያልቅበት ትወናም ልዩ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። የቴአትሩ ሞገስ አያልቅበት ይመስለኛል። ሽመልስ ሲጨመርበት ቴአትሩን ህይወት ዘራበት። ወድጄዋለሁ። ፊልምና የስማርት ስልኮች ቴክኖሎጂ መስፋፋት የቴአትሩን ዓለም ጭር ቢያደርገውም ታዳሚው አሁንም ከቴአትር ቤቶች አልጠፋም። ብሄራዊ ቴአትር ጢም ብሎ ሞልቶ ነበር።

የአዲስ አበባ ቆይታችን በመልካም ነገሮች ብቻ የታጀበ አልነበረም። ደስታችንን የሚያደበዝዝ፣ የሞቀውን ስሜታችንን የሚያቀዘቅዝ፣ በተስፋችን ላይ ጽልመት የሚጋርድ ክስተት መፈጠሩ አልቀረም። ቀደም ሲል እንደገለጽኩትም የኢሳት የኢትዮጵያ ጉዞ በጥሩ ወቅት ላይ የተደረገ አይደለም። የለውጥ ሃይሉ ብርቱ ፈተና በተደቀነበት፣ የዘር ፖለቲካ አቀንቃኞች ከዚህም ከዚያም ጩኸታቸው በበረከተበት፣ የኢትዮጵያ ህልውና አጣብቂኝ ውስጥ በገባበት ወቅት ነው ኢሳት ወደ ኢትዮጵያ ያመራው። የ27ዓመቱ ቡቃያ ፍሬ አፍርቷል። በሕወሓት የተዘራው የጎሰኝነት እህል ለለቀማ ደርሷል። በኢህአዴግ ውስጥ ሰብረው ወጥተው፡ ሕወሓትን ወደ መቀሌ ሸኝተው የተስፋ ብርሃን ይዘው ብቅ ያሉት እነዶ/ር ዐቢይ ከራሳቸው ድርጅት በሚመነጩ ችግሮችና በሌሎች ምክንያቶች ወደፊት መራመድ አቅቷቸዋል። መፈናቀሉ፣ የብሄር ግጭቱ፣ ከምንጊዜውም በላይ የበረታበት ጊዜ ነበር። የኢሳት የልዑካን ቡድን አባላት እግራቸው የኢትዮጵያን መሬት መርገጥን ተከትሎ ለገጣፎ የተከሰተው መፈናቀል ልባችንን ሰብሮታል። በእውነት አሳዛኝ ነገር ነው። ጊዜው የእኛ ነው በሚል በሽታ የተለከፉ የዘር ፖለቲካ አቀንቃኞች በለውጡ ሂደት ላይ የደቀኑት አደጋ እንዲሁ በቀላሉ የሚሻገሩት አይደለም። ለገጣፎ ተረኛ ሰለባ ሆና ከአሳዛኝ ክስተት ጋር ተነስታለች። በሚሌኒየም አዳራሹ የኢሳት ቀን በደስታ የዘለለችው ልባችን በለገጣፎው አሳዛኝ አጋጣሚ ኩምሽሽ አለችብን። በእርግጥ ህይወት እንዲህ ናት። ደስታና ሀዘን። ሀዘን ባይኖር ኖሮ የደስታን ጣዕም እንደምን ማወቅ ይቻል ነበር? ይሄም ጊዜ ያልፋል።

ኢትዮጵያ በገባን በሁለተኛ ሳምንታችን ከአዲስ አበባ የሚያስወጣን የመጀመሪያው ጉዞ ተዘጋጀልን። የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የአድዋ ድል 123ኛ ዓመት በዓልን ለማክበር ባዘጋጀው መድረክ ላይ እንድንገኝ የግብዣ ጥሪ አደረገልን። ለእኔ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ የማደርገው የመጀመሪያው ጉዞ ሊሆን ነው። በደብረብርሃን መስመር ደግሞ በሰላማዊ ትግሉ ስማቸውን ዘውትር በዜናዎቻችንና ፕሮግራሞቻችን የምንጠራቸው መንደሮች እንደሚገኙ ስለማውቅ የመሄድ ጉጉቱ ጨመረብኝ። የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ወደ አንኮበር የሚደረግ ጉብኝትም ማዘጋጀቱን ስሰማ ጉዞአችን ታሪካዊ ሊሆን እንደሚችል ገመትኩኝ። ከአጼ ምንሊክ የመናገሻ ከተማ፣ ከመጀመሪያው ቤተመንግስታቸው መሄድ ትልቅ ትርጉም አለው። በለገጣፎው ክስተት የተኮማተረው ህሊናዬ ሲፍታታ ተሰማኝ። ደግሞ ደስታ ተረኛ ሆኖ ወረረኝ። በእርግጥም ህይወት ይህቺው ናት። ዓርብ የካቲት 22 ከጠዋቱ 12ሰዓት። የኢሳት የልዑካን ቡድን በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ በተዘጋጀለት መኪና ውስጥ ገብቷል። ቀኑ ዛሬም ደስ ይላል። አየሩን የምግብ ያህል መውሰድ ከጀመርኩ ሰንብቼአለሁ። ከሆቴላችን ተነስተን የሰሜኑን አቅጣጫ ይዘን ወደ ደብረብርሃን ጉዞ ጀምረናል። ለገጣፎን አልፈን እንደምንሄድ ሹፌራችን ነገርን። ጥሩ አጋጣሚ ነው።

**ክፍል ስድስትን በሚቀጥለው ሳምንት ይጠብቁን**



# ‹‹የእሥራቱ ዐዋጅ ተሽሯል!››…እውነት!?

በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

## ጨዋታ አንድ፡-

ለቤተሰቡ ኀዘን የሆነው አባት፤ የቤተሰቡን ክብር በልክ አልባ ስካሩ ዝቅ ያደረገው አባት፣ መሸታ ቤት አምሽቶ በእኩለ ሌሊት ወደ ቤቱ ይመጣል፤ በስካር መንፈስ የጎረቤቶቹን ሰላም ያደፈርሳል፤ ሚስቱን ይደበድባል፤ ልጆቹንም ጭምር፡፡

‹‹አባታችን ለምን ትጠጣለህ? ለምንስ ሰላማችንን ትቀማናለህ?›› ሲሉ ጠየቁት ልጆቹ መጠጥ ባልቀመሰበት በአንዱ ቀን፡፡ አባት ተበሳጨ፤ ‹‹ምን አጎደልኩባችሁ?›› በቁጣ መለሰ፡፡

‹‹የምትበሉት አጣችሁ!?›› በጥያቄ አፋጠጣቸው፤ ‹‹ተናገሩኣ! ያጎደልኩባችኹ ነገር አለ!?››

‹‹የለም!›› ልጆቹ ‹ምነው ባልጠየቅነው ዓይነት ስሜት ውስጥ ኾነው ተሸማቀቁ፡፡

‹‹ልብስ አልገዛም አልኩ!?››

‹‹ኧረ አላልክም!››

‹‹በእኔ ጠጪነት ምክንያት ትምህርታችሁ ተስተጓጎለ?››

‹‹ኧረ አልተስተጓጎለም!›› (የሚያስተምራቸው እኮ ሰፈር ውስጥ ያለ አንድ በጎ አድራጊ ድርጅት ነው፡፡)

‹‹‘አባቱ ይኼ ነገር ጎደለብን’ ብላችሁ ያላሟላኹላችኹ ነገር አለ?››

‹‹የለም!››

‹‹እና ምን ጎደለብን ነው የምትሉት?››

‹‹አልክሆል ስትጠጣ ባታበዛ መልካም ነው ለማለት ፈልገን ነው!›› አሉ ከመጠን በላይ ትኹት ለመኾን እየሞከሩ፡፡

‹‹ሂዱ ጥፉ ከዚህ!›› አለ አባት በቁጣ እጁ የገባውን እቃ አንስቶ ለመወርወር አካባቢውን እየቃኘ፡፡ ‹‹ሂዱ!›› ሁሉም እየሮጠ በየሥርቻው ተመሰገ፡፡ አባት ግን ንዴቱ ሊበርድለት አልቻለም፡፡ ‹‹ተደፈርኩ!›› አለ፤ ‹‹ለምን ተደፈርኩ!?››

‹‹ኑ ወዲህ!›› ከየተበተኑበት በቁጣ ጠራቸው፡፡

‹‹እሺ!›› ልጆቹ እየተንቀጠቀጡ አባታቸው ፊት ቀረቡ፡፡

‹‹ማነው ሰካራም እናንተ? …ማን ነው ጠጪ?››

…ልጆቹ ዝም፡፡

‹‹ተናገሩ!››

‹‹አይ እኛ ያልነው፣ ‹ሁሌ ስትጠጣ በልኩ ይኹን› ነው!›› እየተሽቆጠቆጡ መለሱ፡፡

‹‹አባት እንዲህ ይባላል?›› ግንባሩን ቋጥሮ፤ ‹‹ወላጅ እንዲኽ ይባላል ወይ!?››

‹‹አይባልም!›› ባንድ ድምፅ፡፡

‹‹ይቅርታ ጠይቁኝ አሁን!›› እጁን ለኩርኩም እያዘጋጀ፡፡

‹‹ይቅርታ!›› አሉ ልጆቹ ኀዘን በገባው ባንድ ድምፅ፡፡

‹‹እኔ ቆላ ወርጄ፣ ደጋ ወጥቼ ሆዳችሁን ስሞላው ጠገባችሁብኝ ማለት ነው?››

ሁሉም ጭጭ፡፡

‹‹በሉ አሁን ‹አባታችን ይህን ስላደረግኽልን እናመሠግናለን› በሉ!››

‹‹አባታችን ይህን ስላደረግኽልን እናመሠግናለን!››

‹‹ጮኽ በሉና ድገሙት!››

‹‹አባታችን ይህን ስላደረግኽልን እናመሠግንሃለን!››

አንደምታ፡- ችግሩን ዘርዝረው፣ ‹‹ኧረ እባክኽ ተው!›› ሲሉት ቁጣ እና በትር የሚቀድመውን ጌታ እንደምን ችሎ መኖር ይቻላል!? …የሚፈልገውን እንጂ ነውሩ እንዲነገረው የማይሻ፤ ወይም ራሱ ጉድለቱን ለማየት ካልፈለገ ወገን ጋር፣ እንደምን አብረውት መዝለቅ ይቻላል!? …እግዚሃር መቻያውን ይስጠን!

## ጨዋታ ሁለት፡-

ቴሌቪዥን ላይ ተጥጃለሁ፤ በየቴሌቪዥኑ የሚተላለፍ ፖለቲካ ጠላኹ፤ እዛው ባለበት ላይ እየረገጠ የሚንዛዛ ድራማ ማየት ጠላኹ፤ የ‹ባሕላችን ተበረዘ› ዓይነት ውይይት ጠላኹ፤ ሙዚቃ ጠላኹ፤ አብይ አጀንዳ እየተባለ የፖለቲካ ጨዋታ ከሚጫወቱ አስጨንቆ አደሮች ጋር የሚደረግ ቃለ ምልልስ ጠላኹ፤ ማዘኛ ይቅርታ መዝናኛ ፕሮግራም ማየት ጠላኹ፤ ዜና ጠላኹ፤ በጥቅሉ ብሶት ጠላኹ፡፡

በዚኽ ሁሉ የበረታ መታከት ውስጥ ሆኜ አንዱ መንፈሳዊ የቴሌቪዥኑን ጣቢያ ላይ ተጥጃለሁ፡፡ ራሱን ‹‹ሐዋርያ›› እና ‹‹የእግዚአብሔር ሰው›› ብሎ የሚጠራ አንድ ወጣት እየጸለየ ይኹን እያስተማረ ነው፡፡ …ብቻ ከኹለቱ አንዱን እያከናወነ ነው፡፡

‹‹ …ወገኖቼ ደስ ይበላችሁ፤ የእሥራት ዐዋጅ ተሽሯል፡፡ የእሥራት ዐዋጅ ተሰብሯል፤ አሜን በሉ፤ አሁን በዚች ሰዓት፤ በረከት ይለቀቃል፤ ታምራት ይለቀቃል፤ ሲሣይ ይለቀቃል፤ አሜን በሉ ወገኖቼ!››

‹‹አሜን!›› ይላሉ ምእመናኑ፤ ‹‹አሜን!››

‹‹የእስራት ዐዋጁ ተሽሯል፡፡ ዛሬ የብሥራት ቀን ነው፤ ዛሬ የየምሥራች ቀን ነው፤ በእሥራት ውስጥ ያለ ነገር ሁሉ ይለቀቃል!››

‹‹አሜን!››

‹‹ጌታ በእኔ ውስጥ አድሮ አሁንም እየተናገረ ነው፡፡ ዛሬ ዓለም ከእሥራት ነፃ ትወጣለች!››

‹‹አሜን!››

‹‹ወንድሜ አጠገብህ ያለውን ሰው ትከሻውን ንካውና፤ ‹ዛሬ ደስታህ ትለቀቃለች!› በለው፤ …አሜን!?››

‹‹አሜን!››

‹‹ፀጋ ይለቀቃል፤ ነፃነት ይለቀቃል፤ ተስፋ ይለቀቃል፤ መድኃኒት ይለቀቃል፤ ቸርነት ይለቀቃል፤… ››

ለመጀመሪያ ጊዜ የሐዋሪያውን ደጅ የረገጡ የሚመስሉ አንዲት አቅመ ደካማ ባልቴት በየዋህነት ጮኽ ብለው እንዲኽ አሉ፤

‹‹ፓስተር! የተፈቱት አንዴ ተፈትተዋል፤ ይልቅስ ስለሚሞቱት አንድ ነገር በልልን!››

የጨዋታው ማሰሪያ አንደምታ፡- ኤዲያ! ያጣነውስ… ሰላም ይለቀቃል፤ ፍቅር ይለቀቃል፤ መተሳሰብ ይለቀቃል፤ መቻቻል ይለቀቃል የሚለን የእግዚአብሔር ሰው ነው፡፡ ያጣነውስ ዘረኝነት በወለደው ሰይጣናዊ ተግባር ወደ ሞት እየተሸኙ ያሉትን ዜጎች ይለቀቃሉ የሚለን ሐዋሪያ ነው፡፡ ይልቅስ ያጣነው፣ ይኽን ጭቁን ሕዝብ፣ ከስጋት እና ከጭንቀት እስራት ይለቀቃል፤ ከስደት እና ከመፈናቀል ይገላገላል የሚለውን አዋቂ ነው፤ ያጣነውስ በሕዝብ እንባ እና ደም እየተጫወቱ ያሉትን ሹማምንት እና ፖለቲከኞችን ተዉ ብሎ የሚገስፅ የሃይማኖት አባት ነው፡፡ ያጣነውስ… ? እህ! …ለማንኛውም ለክርስቲያን ወገኖቼ እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው በሰላም አደረሳችሁ!?

እዚኽ ላይ፣ ‹‹ሰላሙን እንኳን ተወው!›› ባይ ብስጩ መጥቶ ኃይለ ቃል ቢናገረኝ አልፈርድበትም፡፡ እንዴ! እውነቱን ነዋ፤ በሞት እና በስደት ወሬ የተከበበን ሰው እንዴት፣ ‹‹ሰላም ነኽ?›› ብሎ መጠየቅ ይቻላል!? …እንዴትም!

በዚኽ ሰዓት፣ ከበጉ ዋጋ በላይ፤ ከቅቤው ዋጋ በላይ፤ ከዶሮው ዋጋ በላይ፤ ከሽንኩርቱ ዋጋ በላይ፤ ከሸዋ ዳቦ ዋጋ በላይ እጅጉን የተወደደው ሰላም ነውና፡፡ …ሰላም! ሰላም! ሰላም!

ወቅታዊ

# ይህቺ ኢትዮጵያ ናት ዓርብን አሳልፋ፤ ቅዳሜን ድል ነስታ እንደገና የምትነሳ፤ እንደገናም የምታሸንፍ

የክርስትና እምነት ተከታይ የሆናችሁ መላ የሀገሬ ህዝቦች፤

ለሁለት ወራት ያህል በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት እና ከአምላክ ጋርም በተመስጦ ልቦና

በመገናኘት ያሳለፍነውን ዐቢይ ጾም እንኳን በሰላም እና በፍቅር አጠናቀቃችሁ፤

እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ! አደረሰን!

ከመነሳት የበለጠ ታላቅ ነገር የለምና ትንሣኤ ታላቅ በዓል ነው። በዓሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙስና መቃብርን ድል አድርጎ መግነዝ ፍቱልኝ፣መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል መነሳቱን የምናበስርበትና የምናስብበት በዓል ነው። ከአእምሮ በላይ የሆነውን ሥራ ዕጹብ ድንቅ ብለን፤ በደስታና በፍቅር የምናከብርበት ታላቅ በዓል ነው፤ ከመሞት በላይ ውርደት፣ ከመነሣትም በላይ ክብር የለምና። ከሞት አጠገብ ሕይወት፣ ከመቃብር አጠገብ ትንሣኤ መኖሩን የምናስብበት፣ በአእምሯችንም ሰሌዳ የምናትምበት በአል ነው ትንሳኤ።

በትንሳኤ ጉዞ ውስጥ ዓርብ፣ ቅዳሜና እሑድ አሉ። ዓርብ እውነትና ሐሰት፣ ወዳጅና ጠላት፣ ተስፋና ስጋት፣ እምነትና ፍርሐት፣ እምባ እና ሳቅ፣ ብርሃንና ጨለማ፣ ጽናትና ድካም የተቀላቀሉበት ጊዜ ነው። እየነጋ ባለ ፀሐይና በድቅድቅ ጨለማ መካከል ያለውን ቀጭን መስመር ለመለየት የሚያስቸግርበት ቀን ነው-ዓርብ። በአንድ በኩል በጦር ጉልበታቸው የሚተማመኑ ሮማውያን፣ በሌላ በኩል እናውቃለን የሚሉ የአይሁድ ሊቃውንት አንድ ሆነው ፀሐይ እንዳትወጣ የሚታገሉበት ቀን ነው -ዓርብ። የተስፋ ፀሐይ እንጂ አማናዊት ፀሐይ ገና አልወጣችም። ውስጥ ዐዋቂ ነኝ የሚለውን ይሁዳን ያገኙ ግብዞች፣ ፀሐይን የቀበሩ መስሏቸው፣ ሐውልት ሊያቆሙባት የሚሮጡባት ቀን ነች-ዓርብ።

በእለተ ሆሳዕና ምንጣፍ ሲያነጥፍና፣ የዘንባባዝንጣፊ ይዞ ሲደግፍ የነበረው ሕዝብ፣ በዕለተ ዓርብ ‹ስቀለው ስቀለው› ይላል። ፀሐይ ይጨልማል፣ ጨረቃም ደም ይለብሳል፣ ከዋክብትም ይረግፋሉ። በዚያ ሰዓት ነገን አሻግሮ ማየት፣ ከእውነትም ጋር አብሮ መቆም ከባድ ነው። ሀገር ‹ስ› ብሎ ከሚነጉድበት ስሜት መውጣት፣ የግራ ቀኙን ጩኸት ታግሶ ዓርብ በሃሳብ፣ እሑድ ግን በተግባር ከሚታየው ትንሣኤ ጋር ለመቆም፣ እንደ ዮሐንስ ወንጌላዊ ያለ ጽኑዕ ሰብእና ይጠይቃል። ስቀለው ከሚለው ሳልስት የትንሣኤ ድል እንደሚኖር ማሰብ፣ ደም ከለበሰችው ጨረቃ ወዲያ አማናዊ ብርሃን እንደሚኖር ለማየት፤ ከሚረግፉት እልፍ አእላፍ ከዋክብት ባሻገር ሞትን በሞት በሚገድል አምላክ ክንድ የሚረግፉ ችግሮች መኖራቸውን ለማመን ብርቱ ሰው መሆን ይፈልጋል። ዓርብ ዕለት ከበዛው ጩኸት ይልቅ ከተሰቀለው እውነት ጎን ለመቆም ልብ ያለው ሰው መሆን ይጠይቃል።

ቅዳሜ ድንግዝግዝ ነው። እውነት ድል የተነሣች፣ ፀሐይም ጨልማ የቀረች፣ መቃብርም ታትማ የምትኖር፣ሞትም አንቆ የሚያስቀር፣ ሲያልም አሸጋ የምትቀብር የሚመስልበት ወቅት ነው። አሸናፊና ተሸናፊ አይለይም። እንዲህ ባለው ወቅት እምነት፣ ጽናትና ቆራጥነት እንጂ ማስረጃና መረጃ ለማቅረብ ከባድ ይሆናል። በመቃብሩ ዙሪያ ጠባቂዎች፣ በመቃብሩም ላይ ማኅተም አለ። ከሁሉ ይሻላሉ የተባሉት ሐዋርያት ተበትነዋል። ሕዝቡም የምሥራች ወሬውን ጨርሶ፣አቋሙም በወሬ ብዛት ተፈረካክሶ፣ የክፋት መልእክተኞች የክፋት ወሬ በሕዝቡ ውስጥ ተናፍሶ፣ ወሬውም ከብዙዎች ዘንድ ደርሶ ሥጋትና ተስፋ መቁረጥ አይሏል። ሕዝቡ የሽንፈትና የድካም ነገር ያወራል። ዓርብ ዕለት ያየው ስቅለት፣ደም ፣ግርፋት፣ጩኸት እና እንግልት



የመጨረሻው መጨረሻ መስሎት አለቀ፣ ደቀቀ ይላል። የትናንቱን የዓርብን ነገር የሚያወሩ ብዙ ናቸው። የነገውን የእሑድን ምሥጢር ለመተንበይ የቻሉ ግን ጥቂቶች ብቻ ናቸው። ገብቶናል፤ ተረድተናል፤ ተምረናል፤ አውቀናል የሚሉት እንኳን በወሬው ተሸንፈዋል፤ በስሜቱ ተውጠዋል። ነፋሱንና ጎርፉን መቋቋም አቅቷቸው፣በነፋሱና በጎርፉ ተወስደዋል።

አንድ የማይቀር እውነት ግን አለ-ትንሣኤ ይመጣል። ጩኸት ቢበረታም፣ ሽብር ቢነዛም፣ኃያላን ቢነሱም፣ እውነት የተሸነፈች ብትመስልም-ትንሣኤ ግን በግድ ይመጣል። ወሬውና ሽብሩ አስደናቂውን ትንሣኤና ትንሣኤውን ተከትሎ የሚመጣውን እልልታ ፈጽሞ ሊያስቀረው አይችልም። ጠባቂዎቹና ማኅተሙ፣ የሞት ፉከራ እና የጉልበተኞች ጉርምርምታ በጭራሽ ትንሣኤን አያግዱትም። የብዙዎች ተስፋ መቁረጥና የተሰናካዮች ወደ ኋላ መመለስ ከመምጣት አይገቱትም። ከሞት አጠገብ ሕይወት! ከመቃብርም አጠገብ ትንሣኤ አለ። እምባ እና ደም ያጠየሚት ዓርብ የሥርየትና የሐሴት መሠረት ነች። የጭንቋ ቀን ቅዳሜ የትንሣኤው የመዘጋጃ ቀን ናት። ከዚህ ሁሉ በኋላ በዝማሬ የምትደምቅ እና በትንሣኤም የምትከብር እሑድ መኖሯን ያመነ ሰው እርሱ እውነትም ወንዝ ተሻጋሪ ሰው ነው።

ትንሣኤ የዘገየ ይመስላል እንጂ አይቀርም። አለቀ፣ ደቀቀ፣ ሞተ፣ ተቀበረ፣ የሚሉትን ሁሉ አሳፍሮ ክርስቶስ በእኩለ ሌሊት ተነሥቷል። መቃብሩ ባዶ ነው። ‹ሞተ› የሚለው መርዶ ቀረ። ዜናው ተነሣ ሆነ። አለቀ የሚለው መርዶ ቀረ፤ዜናው -እንደገና ተጀመረ ሆነ። ተስፋ መቁረጥ ታሪክ ሆኖ፤ ራሱ ተስፋ ከሞት ተነሣ። የተበተኑት ተሰበሰቡ። ፈርተው የሸሹት ተመለሱ። ወሬና ሽብር ያስቀራቸው እንደገና መጡ። የተቀረጠ ተቀጠለ፣ የደከመ በረታ፣ ታሪክ ተለወጠ። ትንሣኤ መኖሩ ብቻ ሳይሆን በምንም ሰበብ፣በማንም ክልከላ፣ በየትኞቹም የመቃብር ጠባቂዎች ብርታት እንደማይቀር ተረጋገጠ- ይህንን ነው ከትንሣኤ በዓል የምንማረው።

ኢትዮጵያን ሰቅሎ መቅበር፣ ቀብሮም ማስቀረት አይቻልም። የተሰቀለች፣ የተቀበረች የምትመስልበት ጊዜ ግን አለ። በጠላቶቿ የተሸነፈች የምትመስልበት ቀን ግን ነበረ፤ አለም። ራቁቷን በጨለማ ውስጥ የቆመች የምትመስልበት ጊዜ ግን ነበረ፤አለ። ወዳጆቿ ሸሽተዋት፣ ልጆቿ ተስፋ ቆርጠውባት፣ አዋቂዎቿ ሟርት ነጋሪዎች ሆነውባት፣ ፀሐይ የጨለመባት፣ ጨረቃም ደም የለበሰችባት፣ ኮከቦቿም የረገፉባት የሚመስልበት ጊዜ ነበረ፤ አለ። ከዚህ ሁሉ በኋላ ግን ትንሣኤ ይመጣል። የዓርብም ሆነ የቅዳሜ ጉዞ ወደ ትንሣኤ ነው።

በግርግር ውስጥ፣ በስሜትና በነውጥ ውስጥ ያለ ሰው፣ አርቆ ለማየት ተስኖት እንጂ ትንሣኤ የሚጀምረው ከዓርብ ነው። ዕለተ አርብን ብዙ ሰው የሚያየው የሕዝቡን ጩኸት ነው፤ የክርስቶስን መሰቀል ነው፤ የፀሐይን መጨለምና የጨረቃን ደም መልበስ ነው! የከዋክብትን መርገፍ ነው።

የትንሣኤን ታሪክ ማየት የሚችሉ ጥቂቶች ግን የመጋረጃውን መቀደድ፣ የአለቶችን መሰንጠቅ፣ የመቃብሮችን መከፈት፣የሙታንንም መነሣት ዓርብ ዕለት ያያሉ። በዓርብ ጨለማ ውስጥ የትንሣኤን ብርሃን ከተሻሯቸው ሰንበት ጀርባ ይማትራሉ። በተአምራት፣በደም እና በጩኸት ከታረሰው የዓርብ ሰማይ አልፎ፣ ቀቢጸ ተስፋ ከተጣባው የቅዳሜ ጀምበር ወዲያ፣የተስፈኛው ብርቱ ልብ እሑድ ሌሊት ላይ የሚገለጠውን ትንሣኤን ያያል።

ኢትዮጵያችንም እንዲሁ ናት። የተሸነፈችና የደከመች፣ የተሰቀለችና የሞተች፣ያለቀላትና ያከተመላት በሚመስልበት ጊዜ ውስጥ ትንሣኤዋ ከሩቁ ይታያል። በዛሬው ማዕበል የማይወሰዱና፣ በአይሁድ የሐሰት ወሬ የማይናዱ የማይቀር ትንሣኤዋን ያዩታል። አየሩን ክፉ ወሬ ቢሞላውም፤ ከሙታን የተነሱት ግን ወደ ከተሞች ገብተው መልካሙን ወሬ ያወራሉ። ልጆቿ የተከፋፈሉ ሆነው ዓርብን ያሳልፉታል። እንደ ዮሐንስ ያሉት ጸንተው፣ እንደ ጴጥሮስ ያሉት ተጠራጥረው፣ እንደ ይሁዳ ያሉት ክደው፣ ሌሎቹ ደግሞ ፈርተውና ደንግጠው ዓርብን ያሳልፋሉ። ትንሣኤ ሲመጣ ግን የካዱት ይጠፋሉ፤ የተጠራጠሩት ያምናሉ፤ ያመኑት ይጸናሉ፤ የፈሩትም ይደፍራሉ። እንደገናም ተመልሰው ሳይበተኑ አንድ ይሆናሉ። በዕለተ ትንሣኤ ሁሉም ይደመራሉ።

ድንጋዩም ይነሣል፣ መቃብሩም ይከፈታል፤ሙስናም ይቀራል፣ መግነዙም ይፈታል። ትንሣኤው እንዳይኖር ከበበው የሚጠብቁ ይበተናሉ። አለቀ! ደቀቀ! እያሉ ሲተነትኑ የነበሩ ያፍራሉ። በነፍሳችን ሲወራረዱ የነበሩ ሁሉ ይደነግጣሉ። ኢትዮጵያ ከዚህ በኋላ ተስፋ የላትም ያሉ ሁሉ እነርሱ ራሳቸው የትንሣኤዋ ማስረጃዎች ይሆናሉ። ዓርብ የጀመረው ትንሣኤ እሑድ ይደመደማል። እንደ አይሁድ ለብቻቸው አድመው ዕጣ ፈንታችንን የወሰኑብን ሁሉ ከእውነቱ ጋር ይጋፈጣሉ። በሞት ተፈጸመ፣ በመቃብርም ተደመደመ ብለው ታሪካችንን ሊጽፉ የቋመጡ ሁሉ እንደገና ብዕራቸውን ለትንሣኤያችን ያነሣሉ።

እኛ የሞት መልእክተኞች አይደለንም! የሕይወት አብሣሪዎች እንጂ። እኛ የመቃብር ጠባቂዎች አይደለንም፤ የትንሣኤ መልከቶች እንጂ። እኛ የጨለማ አበጋዞች አይደለንም፣ የብርሃን መልእክተኞች እንጂ፤ እኛ ከጨለመች ፀሐይና ደም ከለበሰች ጨረቃ ይልቅ አዲሲቷ የተስፋ አድማስ፤ የተተረተረውን መጋረጃ፣ የተከፈቱትን መቃብሮች፣ የተነሱትን ሙታን፤ የተናወጡትን ተራሮች እናያለን። እኛ ከሕማማት በኋላ ፋሲካ፣ ከመከራም በኋላ ደስታ መኖሩን እናምናለን። ለእርሱም እንጋደላለን። የትናንቱን ዛሬ ዘግተን፣ የነገውን ዛሬ እንጀምራለን። ይህቺ ኢትዮጵያ ናት ዓርብን አሳልፋ፤ ቅዳሜን ድል ነስታ እንደገና የምትነሳ፤ እንደገናም የምታሸንፍ።

ኑ!የመቃብር ጠባቂነታችንን ትተን- የኢትዮጵያን ትንሣኤ እናብስር!

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!

ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!

ኢትዮጵያ፣ አዲሲቷ የተስፋ አድማስ!

መልካም በዓል!

# አንደበት



"‹እዚህ ላይ ብስጭቱን የሚገልፅ አድርግልኝ፣ እዚህ ላይ ደግሞ ደስታውን፣ ወይም ቁጣውን› እንደዚህ እያልኩ አማኒ ፒያኖ ይዞ በርከት ያሉ ዜማዎችን በማውጣትና ሙዚቃውን በመፃፍ ጉልህ አስተዋፅኦ አድርጓል። ከዚያ ሠራን፣ መቼም ሩጫ ነው። በመካከሉ ለበዓሉ አንድ አምስት ቀን ሲቀሩት የደርግ ባለስልጣናት ዝግጅቱን ሊገመግሙ መጡ። አይተው ሲጨርሱ አበዱ። ‹የደርግ ሥራና ያስገኘው ውጤት የት አለ? እዚህ ውስጥ ለውጡን ሕዝቡ በትግሉ፣ በራሱ ጥረት እንዳመጣው አድርጋችሁ ያቀረባችሁት ልክ አይደለም። ንጉሱን ማነው የጣለው? ደርግ አይደለም ወይ?› ብለው አበዱ። እኔ፣ ደበበ እሸቱ፣ አበበ በየነ ሆነን ለመከራከር ብንሞክርም የሚሰማን አጣን።"

**ታደሰ ወርቁ /የህዝብ ለህዝብ አዘጋጅ/**
**ታዛ መጽሔት ሚያዝያ 2011 ዓ.ም**



"የሙዚቃውን ኢንዱስትሪ ስመለከተው በአልበም ሳይሆን በተለይ በነጠላ ዜማዎች በጣም እየሞቀ መሆኑን ተገንዝቤያሁ። ኢንዱስትሪውን ህጉ ብዙ ባይደግፈውም፣ ሙያተኛው በራሱ ትግል ጥሩ እየተንቀሳቀሰ ነው ብዬ አምናለሁ። እንደውም አሁን እንደማየው፣ ብዙዎቹን ወጣት ድምፃውያን እየጠቀማቸው ያለው አይቲዩንስና ዩቲዩብ ነው። ወጣቶች የተፈጠረውን አጋጣሚ እየተጠቀሙበት ነው። ያ የሚያስከፋ አይደለም። ነገር ግን የበለጠ መንግስት ቢተባበር፣ ብዙ ነገሮች መልካም ይሆናሉ፤ ኢንዱስትሪው የበለጠ ልቆ፣ ሙዚቃው አድጎ፣ ሁሉም ተጠቃሚ ሆኖ ማየት ምኞቴ ነው።"

**ድምፃዊ ጎሳዬ ተስፋዬ**
**አዲስ አድማስ ጋዜጣ ሚያዝያ 19 ቀን 2011 ዓ.ም**



"የውድድር ሜዳዎች የጦር ሜዳ እስኪመስሉ ድረስ ዜጎቻችን እየተደባደቡ፣ እየደሙ፣ መሳሪያዎች እየተተኮሱ፣ ጨዋታዎች እየተቋረጡ መሄዳቸው የፊፋና የካፍ ህግ ከሚያዘው ውጭ የጎሳና የዘር ልዩነት እግር ኳሱ ውስጥ ሥር ሰዶ ደጋፊው በነፃነት ወደ ስታዲየም መጥቶ እንዳይደግፍ፣ ተጨዋቾች በነፃ አዕምሮ ጨዋታቸውን ተጫውተው እንዳይወጡ፣ ዳኞች ጨዋታውን በነፃነት መርተው የማይወጡበት ደረጃ ላይ በመድረሱ፤ ይሄም በአንድ ቦታ ብቻ ሣይሆን በየቦታው ከብርሃን ፍጥነት በበለጠ እየተዛመተ በመምጣቱ በጣም ስላሳሰበንና ሠላማችንን ስለነጠቀን ለችግሩ መፍትሔ ለመፈለግ ይረዳል ከሚል የተቀደሰ ሀሳብ የውይይት መድረኩን ለማዘጋጀት በቅተናል።"

**አቶ አብነት ገ/መስቀል /**
**የቅዱስ ጊዮርጊስ ስፖርት ማህበር የቦርድ ሰብሳቢ/**
**ሀትሪክ ጋዜጣ ሚያዝያ 23 ቀን 2011 ዓ.ም**



"በእነ ጌታቸው ጊዜ ግን፣ እያንዳንዱ የማህበረሰብ ክፍል ያልታሰረና ቂም ያልቋጠረ አልነበረም። ሙስሊሞች ታስረዋል፣ የማህበረ ቅዱሳን አባላትን ማሰር ጀምረዋል፣ ፖለቲከኞች ከሁሉም ዘርፍ ያሉትን ተቃዋሚዎች፣ ጋዜጠኞች፣ ምሁራን፣ ወታደሮች፣ የደህንነት ሰዎች፣ ብሎገሮች፣ የውጭ ሀገር ዜጎች ወዘተ ታስረዋል። የእስራት መንገዳቸው ማንንም የማይመርጥ፣ በትንሹም በትልቁም ያጠፋውን ወህኒ ቤት የሚያስገባ ነበር። የእስሩ መበራከትና መንግስታዊ አፈናው አሁን ያለው ሁኔታ እንዲፈጠር የራሱን አስተዋፅኦ አድርጓል። ሕዝቡን ለበርካታ ዓመታት መከራውን አብልቶት የነበረው ሰቆቃ፣ ግፍና ስቃይ ከልክ በላይ ሞልቶ መፍሰሱ የማይቀር ሆኖ ነበር።"

**ዛዲግ አብርሃ /የቀድሞ የህወሐት ከፍተኛ አመራር/**
**ኢትዮጲስ ጋዜጣ ሚያዝያ 20 ቀን 2011 ዓ.ም**



"የግል መገናኛ ብዙሃን ችግር የሚጀምረው ገና ከመጀመሪያው ነው። ከ1985 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ ክሶች፤ ማሳደዶች፤ እያነቁ እስር ቤት መከተት፣ ለተወሰኑ ቀናት ደብዛን ማጥፋት ነበር። በቤተሰብ ብዙ ፍለጋ ተሯሩጦ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ተደርጎ በዋስ ሲፈቱም፤ በድጋሚ ከመንገድ ላይ አፍሶ ሌላ ቦታ መሸሸግ መንግሥት ያደርግ ነበር።"

**ጋዜጠኛ መላኩ ደምሴ / የሪፖርተር ጋዜጣ ማኔጂንግ ኤዲተር/**
**አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሚያዝያ 23 ቀን 2011 ዓ.ም**



"የአቪየሽን ኢንሹራንስ አሰራር የተወሳሰበ ነው። አንድ የኢንሹራንስ ኩባንያ የሚባል ነገር የለም። የመድን ዋስትና ሽፋን ሰፊ በመሆኑ፣ የተለያዩ ኢንሹራንስ ኩባንያዎች በቡድን ሆነው ነው የመድን ሽፋን የሚሰጡት። የእኛ ደንበኞች አሥር የሚሆኑ ኢንሹራንስ ኩባንያዎች በመተባበር ለንደን በሚገኘው ሎይድ ኢንሹራንስ ገበያ አማካይነት ነው የመድን ሽፋን የሰጡን። እነዚህ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ዓለም አቀፍ የአቭየሽን መድን አሰራር ተከትለው ለአደጋ ተጎጂ ቤተሰቦች ተገቢውን የካሳ ክፍያ ይፈፅማሉ"

**አቶ ተወልደ ገብረ ማርያም**
**/የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ/**
**ሪፖርተር ጋዜጣ ሚያዝያ 20 ቀን 2011 ዓ.ም**

# ለዛ

*"እንኳን ለሠርቶ አደሮች ቀን አደረሳችኹ!"*




## ጠቅላላ ዕውቀት

• የታይፕ መኪናን የፈጠረችው ሴት ሳይንቲስት ስሟ Qwert Yuiop ነው፡፡ በእንግሊዘኛው ታይፕ በላይኛው የፊደል መስመር ላይ የሚገኙት አስርቱ ቃላት Qwertyuiop ሲሆኑ ስለፈጠራ ባለቤትነትና ማስታወሻ ተብሎ የተደረደሩ ናቸው።

• በኢሜል የተላከው የመጀመሪያው ቃል Qwertyuiop ሲሆን እነዚህም በአንግሊዘኛው ታይፕ በላይኛው የፊደል መስመር ላይ የሚገኙት አስርቱ ቃላት ናቸው፡፡ ዘመኑም 1971 ዓ.ም ሲሆን ይህን የኢሜይል መልዕክት በማስተላለፍ የመጀመሪያው ሰው ሬይ ቶም ሊንሰን የተባለ አሜሪካዊ ነው።

• በ1811 ዓ.ም በአሜሪካ በተከሰተው ርዕደ መሬት የሚሲሲፒን የወንዝ ፍሰት አቅጣጫ ወደ ኋላ በመቀልበሱ ይህ ወንዝ አሁን የሚፈሰው ከተፈጥሮው በተቃራኒ አቅጣጫ ነው።

• ስልክ የፈጠረው ሳይንቲስት ኤሌክሳንደር ግርሐም ቤል ሲሆን፤ ሚስቱና ወላጅ እናቱ ጆሮአቸው በፍፁም አይሰማም ነበር። በመሆኑም እነዚህ መስማት የተሳናቸው የቅርብ ቤተሰቦቹ የእርሱን የፈጠራ ውጤት ተጠቃሚ ለመሆን አልቻሉም።

## ለምን ብዬ ሌባ

የሰው ልጅ ሀጢያቱ ሰንኮፉ   እንዲነቀል
በቀራንዮ ላይ በሌቦቹ መሀል
ጌታችን ሲሰቀል የሾህ አክሊል ደፍቶ
ስለእኔ ሊሰዋ በደሙ ሊያፀድቀኝ
ሲኦልና ገነት ቆመው አየኋቸው በግራና በቀኝ።
በግራው መስቀል ላይ ርቃኑን ተሰቅሎ
ሊሞት ያለው ሌባ
ጥሩ ቃል ተናግሮ ገነት እንዲገባ
የእጅ አመሉ ላይ
የአፍ አመል ጨምሮ
ባልተወደደ ቃል መሲሁን ተናግሮ
ነፍሱን አጣደፋት ለሲኦል ቀጠሮ።
የቀኙ ሌባ ግን ጌታውን ያወቀ
ለብዙ ዓመት ሰርቶ አንዴ አምኖ ፀደቀ።
እንዴት ያለ ዕድል ነው
ወደኋላ ኑሮ ቢሰርቅ የማይገኝ
ምነው የዛን ጊዜ
በቀኝ በኩል ያለው ሌባውን ባረገኝ
ብዬ አሰብኩና በቁጭት እንዳለሁ
የመስቀሉን ምስጢር
ለነፍሴ ጆሮ ግንድ
አንድ ውነት ሹክ አለው
በዓመተ ምህረቱ መፅሐፉ እንዳለው
አሁን ማረኝ አልኩት
ለካ አሁን እድናለሁ፤
እንዲህ ከሆነማ
ታዲያ ለምን ብዬ
ያውም የዚያን ዘመን
ሌባ እሆናለሁ!

(ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን- ቴዲ አፍሮ)

ማረሚያ፡- ይህ ከላይ ያለው ግጥም ባለፈው ሳምንት እትማችን ላይ በተፈጠረ የዲዛይን ችግር ተቆርጦ የቀረ በመሆኑ ይቅርታ እየጠየቅን በድጋሚ አውጥተነዋል።



# “ወያኔ በአዲስ አበባ ጉዳይ የታሪክ ቦንብ ነው የተከለው”

አምባሳደር ካሳ ከበደ (በተለይ ለግዮን)

አምባሳደር ካሳ ከበደ በባለፈው ሳምንት ቆይታችን በሀገሪቱ ያለውን ወቅታዊ ችግሮች፣ የለውጡ ቡድን በአንድ ዓመት ጊዜው ያከናወናቸውን ተግባራትና ተግዳሮቶቹን በተመለከተ፤ ሰፋ ያለ ትንታኔ ሰጥተውናል። በዚህኛው ዕትማችን ስለ አቶ ለማ መገርሳና አቶ ገዱ አንዳርጋቸው አዲስ ሹመት፣ “ዶ/ር ዐቢይ ከስልጣን መውረድ አለበት” ስላሉት የቀድሞው የኢሠፓ አባልና የደርግ ባለስልጣን ስለነበሩት ሻለቃ ዳዊት ወ/ጊዮርጊስ አስተያየት፣ ስለአዲስ አበባ ታሪካዊ ባለቤትነትና የተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች የሰጡንን ቃለምልልስ አማባሳደርን በስልክ ካሉበት አሜሪካን ያነጋገራቸው የግዮን ጋዜጠኛ ፍቃዱ ማ/ወርቅ እንደሚከተለው ያስነብበናል። መልካም ቆይታ።

**ግዮን፡- ሕወሓት ከትግል ጊዜው ጀምሮ እስካሁን ድረስ ለሱዳኑ አልበሽር ቀኝ እጅ እንደነበረ ይታወቃል። አሁን በተፈጠረው ሁኔታ አልበሽር ወደ እስር ገብተዋል፡፡ ይሄ ነገር ለህወሓት ሰዎች ትልቅ ዱብዕዳ ሆኖባቸዋል ይባላል። ከዚህ አንፃር አስቀድመው ካሰቧቸውመንገዶች ጋር ዕንቅፋት ይገጥማቸዋል ብለው ያስባሉ? ሁኔታው ለኢትዮጵያ አዲስ ዕድል ይፈጥራል የሚሉ ወገኖችም አሉና።**

አምባሳደር ካሣ፡- እኔ እንደማየው ሱዳን ጥገኛ አገር ነው። በሌሎች አገሮች ድጎማ የሚተዳደር አገር ነው። በዚያ ምክንያት ነፃ የሆነ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ኖሮት አያውቅም። እናም የኢትዮጵያን ጠላቶች በመደገፍ ረገድ የአልበሽር አገዛዝ ብቻ ሳይሆን ከሱም በፊት የነበሩትን ሕወሓትን፣ ሻዕቢያን፣ ኦነግን ይረዳ ነበር፡፡ እናም ሱዳን የፀረ ማዕከላዊ መንግስታቱ መናኸሪያ ነበረች። አልበሽር ጋር በምንሄበት ጊዜ ወደ መጨረሻው ላይ ነው የመጣው እርሱ፡፡ የደርግ መጨረሻ ዘመን፤ የእስልምና መርህ ይዞ ተነስቶ ስለነበረና የሌሎች አረብ አገራት ፍላጎት አስፈፃሚ ስለነበረ፣ ሕወሓትን ማገዝ ብቻ አይደለም፣ አብሮ ከጎን ተሰልፎ የተዋጋበት ግዜም ነበረ።

መለስ ስልጣን ከያዘ በኂላ በአልበሽርና በመለስ፤ ወይም በሕወሓት መካከል የነበረው ግንኙነት በጣም እየጠነከረ ሄዷል። እንደምናስታውሰው ትግራይን እንደ አንድ ነፃ የጎረቤት አገር በመቁጠር፣ በክልል በዓላቸው ላይ ሁሉ የመገኘት ፕሮቶኮልን ያልጠበቀ አካሄድ እንደነበረ ሁሉ እናስታውሳለን። እና አሁን የአልበሽር መውረድ በሱዳንና በሕወሓት መንግስት መካከል የነበረውን ግንኙነት ባህርይ ሊለውጠው እንደሚችል ግልፅ ነው። ግን ተተኪው ወታደራዊ አካል ወይም ጊዜያዊ አስተዳደር ስልጣን እንደጨበጡ በቅድሚያ መልዕክተኛ የላኩት ወደ አዲስ አበባ ነው። በዚያ ግንኙነት ላይ ምን እንደተነጋገሩ ባናውቅም፤ መልካም ግንኙነት መፈለጋቸውን ግን መገመት እንችላለን። ስለዚህ እንደ አልበሽር ግዜ የሰፋ ሁኔታ ሊከተሉ አይችሉም፤ የሱዳንና የኢትዮጵያን ግንኙነት ለማሻሻል ግን የተሻለ ሁኔታ የተፈጠረ ይመስለኛል።

የሱዳንና የኢትዮጵያን ግንኙነት ማሻሻል በምንልበት ጊዜ ሱዳን በሌሎች አገሮች ላይ ጥገኛ መሆኗን ስለምናውቅ፤ ዛሬም የቱርኮች ተፅዕኖ እዚያ አከባቢ ጠንከር ያለ ስለሆነ፤ ሌሎች ኃይሎችም ስላሉ የኛ የዲፕሎማሲ ኃይሎች ሱዳን ሙሉ በሙሉ ነፃ አለመሆኗን መሰረት በማድረግ ከሱዳን ጋር ብቻ ሳይሆን አዲስ የሚቋቋመውን መንግስት ሊመርዙብን ከሚችሉ የእስልምናና የአረብ ኃይሎች ጋር ለመግባባትና የእነሱን ጠላትነት ለማዳከም የዲፕሎማሲ ስራ መሰራት ያለበት ይመስለኛል። ይህ ከተደረገ ከአልበሽር ዘመን የተሻለ ግንኙነት ከሱዳን ጋር መፍጠር የሚቻል ይመስለኛል። ►

**ግዮን፡- በቅርቡ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ ፣ ለአቶ ለማና ለአቶ ገዱ አዲስ ሹመት ሰጥተዋል። በተጨማሪም ጠ/ሚ/ሩ በአንድ አመት ግዜ ውስጥ ሹመትና ተሿሚዎችን መለዋወጣቸው አነጋጋሪ ሆኗል። በዚህ ላይ ያለዎት አስተያየት ምንድን ነው?**

አምባሳደር ካሣ፦ ተገቢ ነው፣ተገቢ አይደለም ለማለት ያስቸግራል። ምክንያቱም የለውጥ ሂደት ነው ብለናል። ይሄ የለውጥ ሀይል ስልጣን በሚረከብበት ግዜ በኢትዮጵያ መስተዳድር ውስጥ ቁልፍ የሥራ መደቦችን የሚይዙት እነማን ናቸው? እነማን መሆን ይገባቸዋል? የትኛው የሥራ መደብ ለየትኛው የድርጅት አባል ሊሰጥ ይገባል? የሚል ቀመር አዘጋጅተው አለመምረጣቸው ግልፅ ነው። ይህን ቀመር ለመስራት የሞከሩት ስልጣኑን ከጨበጡ በኋላ መሆኑ በግልፅ እየታየ ነው። ያ አለመኖሩ ይመስለኛል እነዚህን ተለዋዋጭ ሁኔታዎች የሚፈጥረው። እኔ ይህንን ያለመረጋጋት ብዬ አልወስደውም።

አለመረጋጋት ብዬ ስል አሁን የፌደሬሽኑን ማዕከላዊ ስልጣን የተቆጣጠረው ቡድን መሪ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ ቢሆኑም፣ እሳቸው የሚመሩት ቡድን ኢህአዴግ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። በዚህ ምክንያት እሳቸውም ወጥተው ተናግረዋል እኮ፣ "20 ሚኒስትሮች ለመሾም ምን ያህል አታካች ድርድር ማድረግ እንደነበረብን አታውቁም" ብለውናል። ሁሉም አባል ድርጅቶች ከአዴፓ ሌላ የደቡቡም፣ የትግራዩም፣ የአማራውም "ለዚህ የሥራ መደብ የኔ ሰው ይመደብ" ብሎ ይሞግታቸው እንደነበረ ግልፅ ነው። በዚያ በውስጣቸው ከተደረገ ድርድር በኋላ ነው እንግዲህ እነዚህ ውስጣዊ ሀይሎች የሚወጡት። በዚያ አይነት ድርድር የመጡ ሰዎች፣ ለተመደቡበት ቦታ ይመጥናሉ ማለትም አይደለም። ስለዚህ ተመድበው በተግባር በሚፈተኑበት ግዜ "አይ ካንተ በኩል፣ ወይም ከዚህ በኩል የመጣው ሰውዬ ይህን አልቻለም" የሚል ሁኔታ ከተፈጠረ፣ መፍትሄው የግድ ማንሳትና መለወጥ ነው። በመሆኑም ይሄ የሽግግሩ ባህርይ የመሪ ካድሬዎች ምደባን በተመለከተ ቅድመ ዝግጅት አለመኖሩን የሚጠቁም ነው፡ ፡ ወደፊት እየተሳካላቸው እንዲሄድ ከመመኘት ባሻገር አጥር ላይ ተንጠልጥሎ መንቀፉ ውጤት የሚያመጣ አይመስለኝም።

**ግዮን፡- በቅርቡ ሻለቃ ወ/ጊዮርጊስ "ጠ/ሚ/ሩ ስልጣን መልቀቅ አለባቸው" የሚል ፅሁፍ በማህበራዊ ሚዲያ መልቀቃቸውን ተከትሎ የተለያዩ ሀሳቦች እየተነሱ ነው። በአንድ ወገን ገና በአንድ አመት ጊዜ ጠ/ሚሩን መገምገም ይከብዳል የሚሉ ሲኖሩ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሻለቃ ዳዊትንም የሚደግፉ አልታጡም፡ ፡ እርስዎ በቅርበት ያውቋቸዋልና የተነሱትን ነጥቦች እንዴት ይመለከቷቸዋል?**

አምባሳደር ካሣ፦ በእኔ ዕድሜ ሦስት መንግስታትን አይቻለሁ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ፡ ፡ ከትምህርት ቤት በኋላ በነበረኝ ጊዜ ማለት ነው። የቀዳማዊ ኃይለስላሴን መንግስት አይቻለሁ፣ በቅርበት ሠርቻለሁ፣ ለሹመትም በቅቻለሁ። በደርግም ዘመን በተለያዩ መደቦች አገልግያለሁ። በኢህአዴግ ዘመን ከዚህች አንድ አመት በስተቀር በውጭ ነው የኖርኩት፣ ግን ከኢትዮጵያ ጉዳይ አልተለየሁም። እከታተላለሁ፡ ፡ እና አንድ የሚገርመኝ ነገር አለ። በ"ይውረድ" አባዜ የተለከፉ ሠዎች አሉ። እነዚህን ሠዎች ጠጋ ብለህ ስታያቸው በወጣትነትም ይሁን በትምህርት፣ አልያም ከዚያ ከፍ ባለ የመስመር መኮንንነት በጦሩ ውስጥ ያለፉ ቢሆኑም ጥያቄውን ያነሳሉ። "ኃይለስላሴ ይውረድ" አሉ፣ ኃይለስላሴ ወርዶ ማነው የሚመጣው? "ይውረዱ" ሲሉ ግን መልስ ይዘው አይደለም የሚነሱት፣ ይሄን የይውረድ አባዜ ልትለው ትችላለህ።

ከዚያ በኋላ አስራ ምናምን ዓመት ቆይተን ፣ በዚህም በዚያም ከውጭ ሀይሎችም ጋር ተነጋግሮ ደግሞ "መንግስቱ ኃ/ማርያም ይውረድ፣ ደርግ ይጥፋ" ተባለ። ደርግ ጠፍቶ ማነው የሚመጣው? እንግዲህ ሕወሓት የኢትዮጵያ ህዝብ ምርጫ አልነበረም። ብቻ ይውረድ… ይወረድ የሚለው ፕሮፓጋንዳ ገነነ፣ ወረደ። ከዛስ በኋላ የመጣው ምንድነው? አሁን ደግሞ አንፃራዊ ተስፋ በፈነጠቀበት ጊዜ፣ "ኢትዮጵያ ከሽፋለች፣ ሩዋንዳን ትመስላለች፣ ሱማሌን ትመስላለች፣ ልትበተን ነው እና ዐቢይ ይውረድ! ዐቢይ ይውረድ" የሚሉ ሠዎች ዐቢይን የሚተካው ኃይል መኖር አለመኖሩን ያገናዘቡ አይመስሉም።

በሁለተኛ ደረጃ እነሱ የሰጉበትን የአገር መናጋት ችግር የእሱ መውረድ ሊያረጋጋ እንደሚችልም እርግጠኞች አይደሉም። እንዲህ ጊዜያዊ የሆነ የህዝብ አስተዳደር ነው ብሎ መመኘት ይቻላል፡ ፡ ግን ያ ቅንጦት ነው። የኢትዮጵያን ተጨባጭ ይዘት ያለመገንዘብ ነው። እዚህ ላይ አንድ ታሪክ ልናገር፡-

"ቀዳማዊ ኃ/ስላሴ ይውረዱ" ተብሎ ዕንቅስቃሴ በተደረገበትና ደርግ ወደ ስልጣን እየመጣ በነበረበት ወቅት፣ አባቴ የግቢ ሚኒስትር ነበሩ፡ ፡ እናም እንዲታሰሩ ንግግር መደረጉን እዛው የደርግ አባል ከሆኑ ሰዎች ሰማን። ምን ይሻላል? ብለን ወዳጆቻችን ከነበሩ የደርግ አባላት ጋር ስንመክር፣ በተለይ አንድ ኤርትራዊ ወዳጄ ሻለቃ ነጋሽ ተስፋፅዮን ይባላል፣ ዛሬ ኤርትራ ገብቶ ጀነራል መሆኑን ሰምቻለሁ። ይህንን የነገረኝ ነጋሽ ነበርና በጉዳዩ ስንነጋገር "መንግስቱ ኃ/ማሪያም የሚባል ሰውዬ ነው መሪያችን፣ እቀርበዋለሁ፣ እሳቸው ሪዛይን (Risigen) ቢያደርጉ ለምን እንነካቸዋለን? ብዬ መነጋገር እችላለሁ፣ ምክንያቱም እሳቸው በወሎ ድርቅ አይጠየቁም፣ ለለአግባብ በመበልፀግ አይጠየቁም፣ በስልጣን በመባለግ አይጠየቁም፣ ይታሰሩ የተባለው ለንጉሱ ቅርብ ሆነው ንጉሱን እየመከሩብን ነው" ተብሎ ነው ይለኛል። እንግዲያውስ ሪዛይን (Risigen) ያደርጋሉ፣ በኔ ይሁንብህ አልኩት። በወቅቱ አባቴን ግቢ አይምጡ ብለው ወታደሮቹ ከልክለዋቸው ቤት ውለው ስለነበረ ሄጄ ነገሩን አስረድቻቸው ወረቀት አርቅቀህ አምጣ ብለውኝ፣ እኔም አዘጋጅቼ ሠጠኋቸውና አንብበው ፈርሙበት ስላቸው። "አይ ይሄንንማ ህይወቴን ለማትረፍ ብዬ አልፈርምም" አሉኝ። ለምን ብዬ ስጠይቃቸው "መጽሐፌን አንብባችሁ የለም ወይ፣ እዚያ ላይ እኮ ኢትዮጵያ ምንግዜም የንጉሡ ነገስት የዘውድ አገር ነች ብዬ ፅፌያለሁ፡ ፡ ያንን ያልኩበትን ምክንያት አልተረዳችሁም" ይሉኛል። እኔም እነሱ እኮ የጠሉት ያንን ነው፣ ዘውዱን ለማስወገድ ነው የተነሱት፣ አሁን የዘውድ አገር ነች ብለው እንዴት ይተርፋሉ? አልኳቸው።

አባቴም "እነሱም፣ አንተም ያልገባችሁ አንድ ነገር አለ ላስረዳህ" ይሉኛል። "እኔ ኢትዮጵያን የምመለከታት እንደ አንድ ስልቻ ነው። እዚያ ስልቻ ውስጥ የተለያዩ ነገሮች ይኖራሉ። ግን ደግሞ የስልቻውን አፍ ሰብስቦ የቋጠረ ገመድ አለ። ያ ገመድ ዘውዱ ነው። አሁን ያንን ዘውድ እናስወግድ በምትሉበት ጊዜ እዚያ ስልቻ ውስጥ ያለው በሙሉ የሀይማኖቱ፣ የዘሩና ሌላው ክፍፍል ሜዳ ላይ ተዘረገፈ ማለት ነው፡ ፡ ከዚያ በኋላ ምን ሀይል ነው ያንን ሰብስቦ ወደ ስልቻው አስገብቶ መልሶ የሚቋጥረው? የተጠሉት እርሳቸው ጃንሆይ ከሆኑ የዘውዱ ኢኒስቲትዩሽኑ (Inistitution) መትረፍ አለበት። እሳቸውን ማንሳት አለማንሳት ሌላ ጥያቄ ነው" የሚል ሀሳብ ይዘው ተከራክሩና ባቀረብኩት ወረቀት ላይ ያንን ስንሰርዝ፣ አንዱን ስንከት ከሞላ ጎደል በቀረው ላይ ተስማምተን፣ ያንን አስገብተን ነው ከእስር የተረፉት። ያ ነገር አሁንም ድረስ ውስጤ አለ።

በደርግ ጊዜም "መንግስቱ ኃ/ማሪያም ይውረድ" በሚባልበት ወቅት፣ የኢፌድሪ መንግስት ይውረድ! ኢሠፓ ይወገድ በሚባልበት ጊዜም ጦርነት እየተካሄደ፣ በኋላ "ሕወሓት ይሄን አገር ሰብስቦ ይይዛል ወይ?" ብዬም ሥጋት ነበረኝ፡ ፡ ያው እንደምናየው አሁን በመካከላችን ያለው ክፍፍል፣ የሀይማኖቱ ጎልቶ ባይወጣም የዘሩ ጎልቶ እየታየ ነው። አሁን ደግሞ ያለንበትን ሁኔታ መመልከት ይቻላል። ከዳር ሆነው ደግሞ የኛን መፈራረስ የሚጠብቁና የሚፈልጉ ታሪካዊ ጠላቶች እንዳሉንም እናውቃለን። በዚህ ወቅት ተተኪውን ሳታዘጋጅ ወይም መኖሩ በግልፅ በማይታይበት ጊዜ፣ አገር ውስጥ አለመረጋጋት ተፈጥሯል፣ በአንዳንድ አካባቢዎች ሠላም ተናግቷል ከሚል በመነሳት፣ ያንን እንዴት እናስተካክል? የሚል ጥረት ከማድረግ ይልቅ "መፍትሄው መሪውን ማስወገድ ነው" ብሎ መነሳቱ ሀላፊነት የጎደለው ተግባር ይመስለኛል።

**ግዮን፡- በቅርቡ አምቦ ላይ አማራና ኦሮሞን የተመለከተ ጉባኤ ተካሄዷል። ይህ ጉባኤ ከዚህ በፊትም በባህርዳር ተደርጎ ነበር። በቀጣይ አዳማ ይደረጋል ተብሎ ቢነገርም፣ ከአመት በኋላ ነው በአምቦ የተካሄደው። ከዚህ ያህል ጊዜ በኋላ እንዲካሄድ የተፈለገው ለምን ይሆን? ጉባኤውንስ እንዴት ተመለከቱት?**

አምባሳደር ካሣ፦ ጅምራችን ላይ ሳምንት እንዳነሳነው ኦዴፓና አዴፓ ውስጥ ለውጥ የፈለጉት ሀይሎች ሕወሓትን ለመተካት የራሳቸውን የቤት ስራ ሰርተዋል። ከለውጡ ስድስት ወራት በፊት ጀምሮ ለዚህ ጉዳይ ሲዘጋጁ እንደነበር ገልጫለሁ። ኦዴፓና አዴፓ መነጋገርና ለለውጡ መዘጋጀት የጀመሩት ቀደም ብለው መሆኑን ያሳያል። የዚህ የአማራና ኦሮሞ ህብረት ይህንን ሊያስገኝ ይችላል የሚለውም ቀመር የተጠነሰሰው አስቀድሞ እንደሆነ ግልፅ ነው። በዚያ መሰረት ነው እንግዲህ አነ አቦ ለማ ወደ ባህር ዳር መሄዳቸውና "ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው" የሚለው ሀረግ መገለጡ፣ ጎንደር በሠላማዊ ሠልፍ "የበቀለ ገርባ ደም ደማችን ነው" የሚል ነገር መስተገባቱ። ሁለቱ ተባብረው የሕወሓትን አመራር ካስወገዱ በኋላ አብረው መስራታቸው፣ "ኦሮማራ" የሚባል ዕንቅስቃሴ ጀምረው በህዝቡም ደረጃ መንፈሱ ይሰርፃል፣ ይቀጥላል የሚል ተስፋ አድሮም፣ ተጀምሮም እንደነበረ እናስታውሳለን።

በመካከል በተለያዩ ምክንያቶች ተንትኗል፡ ፡ እኔ እንደገመገምኩት ለአመራሩ ቅርበት ካላቸው አንዳንድ ሠዎችም እንደተረዳሁት

የኦዴፓና አዴፓ ግንኙነት 80% በመግባባት ላይ የተመሰረተ ነው። ነገር ግን 20% የሚሆን የማያግባቧቸው ጉዳዮች አሉ። ሊጎተት የቻለው 80 በመቶውን ትተው 20 በመቶው ላይ ስላተኮሩ ይሆናል። አሁን በቅርቡ ግን አንዳንድ የመግባባት ሂደቶች ተመልክተናል።

**ግዮን፡- እነዚህ መግባባቶች ምን ምን ናቸው። መጥቀስ ይቻላል?**

አምባሳደር፡- እኔ ትልቅ ግምት የምሰጠው የሁለቱ ድርጅቶች አመራሮች ተነጋግረው በኦዴፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ አዴፓን የወከሉ፣ የአዴፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ኦዴፓን የወከሉ የማዕከላዊ ኮሚቴ ተወካዮች ተገኝተው፤ አስተያየት እንዲሰጡ ማድረጋቸው፣ መነጋገራቸው፣ መደራደራቸው እና መስማማታቸው ይሄ ትልቅ ለውጥ ነው። አሁን በእንጥልጥል የቀረው የኦሮማራ ጉዳይ በሁለቱም ክልሎች አዳዲስ መሪዎች ስለተመደቡ ዶ/ር አምባቸውና አቶ ሽመልስ አብዲሳ በእነሱ እንዲተገበር አድርገው ይህንን ጉባኤ አምቦ ላይ ማካሄዳቸው በጣም የሚያበረታታ ነው። ምክንያቱም ስለኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች መግባባት ነው የምንነጋገረው። ስለኢትዮጵያ አንድነት ነው የምንነጋረው። እና ያንን በምንልበት ግዜ 60 በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ኦሮሞና አማራ መሆኑን እናውቃለን። ኦዴፓና አዴፓ የኢትዮጵያን አማራና ኦሮሞ ማግባባት ከቻሉ የኢትዮጵያን አንድነት ለማቅረብ ከዚያ የተሻለ መሳሪያ የሚኖር አይመስለኝም። ደግሞም እነዚህ ሁለት ኃይሎች ከተግባቡና ከተቀራረቡ ማግኔት ነው የሚሆኑት፣ ሌሎችን ለመሳብ። በደቡብ ያሉትን ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በቀላሉ ሊስቡ ይችላሉ። አፋርንም፣ ሶማሌንም ሌሎቹንም ሊስቡ ይችላሉና የዚያ ጅምር ሊሆን ይችላል ይሄ ጉባኤ። አሁንም ጥያቄ ያለው የትግራይ ክልልን በሚመለከት ነው።

**ግዮን፡- ሌሎች አጋር ድርጅቶችስ ጋር ይህ የመሳብ ነገር ይታይ ይሆን?**

አምባሳደር ካሣ፡- እስካሁን እንደምንሰማው መሠረታዊ የሆኑ ጉዳዮች አሉ። የሕገ መንግስቱ ጥያቄ አለ፣ በጎሳ የተደራጁት ክልሎች ጉዳይ አለ። ያ ከምርጫው በፊት ሊከናወንና ምላሽ ሊያገኝ የሚችል ጉዳይ አይመስለኝም። ህገ መንግስቱ ሊሻሻል የሚችለውና የሚገባው የኢትዮጵያን ህዝብ የሚወክል መስተዳድር በኢትዮጵያ ህዝብ ይሁንታ ከተመረጠ በኋላ ነው ብዬ አምናለሁ። ይሄ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ነው ከጎሳ አደረጃጀትም ልንላቀቅ የምንችለው። ከዚያ በኋላ በሚኖረው ሂደት ነው የሚመስለኝ እንጂ ይሄ ዛሬ ካልወለዳችሁት የሚለባው አግባብ አይደለም። እነ ዐቢይም ይህን የማድረግ (mandete) ማንዴት የላቸውም። የኢህአዴግ ተወካዮች መሆናቸውን አንርሳ። እናም (Realistic) ሪያልስቲክ እንሁን ነው የምለው።

**ግዮን፡- የለውጡ ቡድን መሪ ናቸው በሚባሉት አቶ ለማ መገርሳ እና ዶ/ር ዐቢይ አህመድ ላይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ህዝቡ በተለይም በውጭው አለም የሚገኘው ዜጋ የተለያየ ስሜት እንደያዘ ይነገራል። እርስዎ በቅርበት እዚያ ያለውን ነገር ይከታተሉታልና አመለካከቱና ክፍፍሉ ምን ይመስላል? መረዳቱስ በምን መጠን ይለካል?**

አምባሳደር ካሣ፡- እስራኤሎች አንድ ተረት አላቸው። ምን ይላሉ? "ስኳር መላስ የለመደ፣ ኮምጣጤ ያስጠላዋል" አስቀድሜ እንዳልኩት ነው። በለውጡ መጀመሪያ ላይ ለመተግበር ቀለል የነበሩ ነገሮች እንደውም ዐቢይ ቸኮለ በሚያስብል ሁኔታ ተተግብረዋል። ከዚያ በኋላ ያለው ሂደት ግን ፈታኝ ሆኗል። ዲያስፖራ በምንልበት ግዜ ዲያስፖራ አገር ቤት ያለው ህዝብ ነፀብራቅ ነው። ግን አመለካከቱን የሚቀርፁት ሀይሎች አገር ቤት ካሉት የበለጠ የተወሳሰቡ ኮንክሪት(concereet) ናቸው። አንደኛ በውጭው አለም ያለው ሰው የፖለቲካና የዲሞክራሲ ሁኔታ፣ የሰብዓዊ መብት፣ የሰላምና መረጋጋት ሁኔታ በሂደት ኖሮ ያወቀው የመሰከረው ነው። ያንን ለአገሩ ይመኛል።

በሌላ በኩል ደግሞ አገር ቤት ያሉት የፖለቲካ ሀይሎች የተለያዩና እርስ በእርስም የሚቃረኑ ስለሆኑ (ይህን ስል በኢትዮጵያ ስም የሚንቀሳቀሱ ሀይሎች ለማለት ነው እንጂ አገር ቤት የሚታወቁትን፣ የተመዘገቡትን ብቻ ማለቴ አይደለም) እነኛ ወገኖች ሁሉ በዲያስፖራው ላይ ተፅዕኖ አሳዳሪዎች ናቸው። አሁን ከቅርብ ግዜ ወዲህ ሆነ የተባለው ግን በመላው ዲያስፖራው ኮሚኒቲ፤ እኔም የአማራው ተወላጅ ስለሆንኩኝ በአማራው በኩል የተከፋፈለ (sprit) መንፈስ መኖሩን እየታዘብኩ ነው። በአንድ በኩል ፕራግማቲክ (pragmatic) የሆኑ፣ ይህንን የለውጥ ሂደት እንዲቀጥል ከማገዝ የተሻለ አማራጭ የለም፤ በምን እናግዝ እያሉ ታጥቀው የተነሱ የአማራ ልጆች አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ በፌስቡክም (በማህበራዊ ሚዲያው) ከተለያየ አቅጣጫ የሚሰነዘረው "ኢትዮጵያ ተዳከመች፣ ወደቀች ተበታተነች"ና ሌላም ሌላም የሚለው፤ "እነ ዐቢይ አታለሉን ደብቀውን ነው እንጂ ከመነሻው ፍላጎታቸው የኦሮሞን የበላይነት ለማግነንና ትግራዮችን ተክተው፤ ኦሮሞን ባለዘመን ተጠቃሚ ለማድረግ ነው"፣ ኦሮሞን የበላይ ለማድረግ እንትና ኬኛ!.... ኬኛ! የሚለውን የሚያቀነቅኑ ወገኖች አድርጎ የመመልከት፣ የመከፋትና የመጠራጠር ነገር እየታየ ነው። ያንን ሊቀለብስ የሚያስችል የተግባር ዕርምጃና የአፀፋ ፕሮፓጋንዳ ስራ የሚያስፈልግ ይመስለኛል። እኔ ግን በግሌ ይሄ ነው ብዬ አላምንም።

አስቀድሜ እንዳልኩት እዚህ ኦሮሞው ህብረተሰብ ውስጥ ያለውን ጉዳይ በሦስት ከፍዬ ለማየት ነው የሞከርኩት። አንዱ ይሄ "ኬኛ! ኬኛ!" የሚለውን መሰረት አድርጎ የሚንቀሳቀሰው ስራ ያጣውንና ተስፋ የቆረጠውን ወጣት ነው። ወጣት ደግሞ ፍራስትሬትድ (frastreated) ከሆነ አገርን ይጎዳል። ሁልጊዜ ፍሬስትሬሽን ወደ አግሬሽን ነው የሚመራው፤ ይሄንን መገንዘብ አለብን። በአንድ በኩል እነ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ የህዝቡን አስተያየት መመለስ አለባቸው። በሌላ በኩል የራሳቸውን ላለማጣት መሳሪያቸው ህዝቡ ስለሆነ ዲፕሎማሲያዊም ሆነ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴያቸውን ልንገነዘብላቸው ይገባል። እኛ የምንመኘው ሁሉ መሆን አለበት የሚለው አያስኬድም።

**ግዮን፡- ብዙዎች አዴፓ የአማራውን ህዝብ መብቶች የሚያስከብር አይደለም፤ የነበረውን መብት ከዚህ በፊትም ለሕወሓት አሳልፎ ሰጥቶ ነበር፤ አሁንም ለኦዴፓ አሳልፎ ሊሰጥ ነው ፤የሚሉ ሀሳቦች ይሰነዝራሉ። እርስዎ በዚህ ላይ ያለዎት ሀሳብ ምንድን ነው?**

አምባሳደር ካሣ፡- ይህንን መቀበል ያቅተኛል። አዲስ አበባ በነበርኩበት ግዜ የአዴፓን አመራሮች አግኝቼ የማነጋገር ዕድሉ ነበረኝ። ከዚያ በኋላም ባህርዳር ላይ ጉባኤያቸውን ሲያካሄዱ ጋብዘውኝ እዚያም ተገኝቼ ታዝቤያለሁ። ከጉባኤውም በኋላ እንደገና ከአመራሩ ጋር እየተገናኘሁ ምን እያደረጉ እንደሆነ ለመረዳት ሞክሬያሁ። አንደኛ የሠው ኃይል ምደባን በተመለከተ እኔ እንደተረዳሁት በአራቱ የኢህአዴግ ድርጅቶች መካከል ድርድር እንደተካሄደ፤ በድርድሩ አዴፓ የሚፈለገውን ለማግኘት ጠንክሮ እንደሰራና እስካሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ "ከስረናል ወይም አጥተናል" የሚል ስሜት እንደሌለ፤ ወደፊትም የተሻሉ የስራ መደቦችንም ለመጨመር እንደሚተጋና እንደሚሰራ ዕቅድ እንዳለ ነው የተረዳሁት።

**ግዮን፡- በድርድሩ ወቅት ቅሬታዎች ነበሩ ማለት ይቻላል?**

አምባሳደር ካሣ፡- አይመስለኝም። ያላግባቧቸው ወይም የማያግባቧቸው፣ እስካሁንም ሳይግባቡባቸው የቀሩ 20 በመቶ የሚሆኑ ጉዳዮች አሉ ብዬ የራሴን ስሌት ቀደም ብዬ ተናግሬያለሁ። እነዚያ ደግሞ የሰው ሀይል ምደባን በቀጥታ የሚመለከቱ አልመሰለኝም። ውዥንብር ያለው በአዲስ አበባ ባለቤትነት ጉዳይ ላይ ነው። በአዴፓ በኩል አዲስ አበባ የኢዲስ አበቤዎች ነች፣ የኢትዮጵያ ፌዴራል ከተማ ነች የሚል አቋም መኖሩን በመግለጫቸው ጭምር አሳውቀዋል። ኦዴፓም አሳውቋል። በኦዴፓ በኩል ግን መሪዎቹ እየወጡ በሚናገሩበት ጊዜ የኦሮሞ ህብረተሰብ ውስጥ ያሉ ተቃዋሚዎቻቸውን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ለአዴፓ መሪዎች የሚሉትን ሁሉ ለእኛ ደፍረው ለማለት የቻሉ አይመስልም። ከአሁን በፊት የተደረገውን የህዝብ ቆጠራ መሰረት በማድረግ ከአዲስ አበባ ህዝብ አብዛኛው አማራ ነው የሚል እምነት አለ። የኦሮሞዎች ቁጥር በአዲስ አበባ ውስጥ አናሳ ነው የሚልም ነገር አለ። ኦሮሞዎች ይህንን ቁጥር ለመለወጥ መታወቂያ እየሰጡ ነው የሚልም ጥርጣሬ አለ። ከጥርጣሬም ያለፈ ሆኗል። ኦሮሞ አዲስ አበባ ውስጥ የመኖር መብት አለው ፤የለውም የሚለው ሌላ ጥያቄ ይመስለኛል።

**ግዮን፡- እርስዎስ አዲስ አበባ የማን ናት ይላሉ?**

አምባሳደር ካሣ፡- እኔ የማየው ኢትዮጵያ የሚባል ዳር ድንበር ያለው፤ አንዴ እየጠበበ ፣አንድ ጊዜ እየሰፋ ብዙ ሺ ዘመናት ያስቆጠረ አገር አለን። መሬት አለን። እላዩ ላይ ህዝብ አለ። ያ ህዝብ በዚህ በረጅም ዘመን ውስጥ ከሰሜን ወደ ደቡብ፣ ከደቡብ ወደ ምስራቅ፣ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ፣ ከዚያም ወደ መሀል እየተዘዋወረ ነው የኖረው። መሬቱ ግን እዚያው ነው። እዚያ ቋሚ መሬት ላይ አፄ ምኒልክ አዲስ አበባን መስርተዋል። አንድ ማዕከላዊ መንግስት የመንግስቱን ማዕከል የሚመሰረትበት ሌላ መሬት ሊኖር አይችልም። ከአገሩ መሬት ቆርሶ ነው የሚመሰርተው። አፄ ሚኒልክም ያንን የመረጡትን ቦታ ከትመዋል። ለምን ያንን መረጡ? የተለያዩ ምክንያቶች ይኖራሉ። ቀዳሚው ምክንያት ከእርሳቸው በፊት የነበሩ ነገስታት በዚያው አከባቢ በእንጦጦ፣ በየረር ነበሩ የሚል ትርክት አለ። በሌላ በኩል ደግሞ ከአንኮበር ወደ እንጦጦ መጥተው ከሠፈሩ በኋላ ባለቤታቸው ፊንፊኔ የሚባለውን የፍልውሃ አካባቢ (እንደውም እስከ ቅርብ ጊዜ



ድረስ ያ አካባቢ እቴጌ መስክ ነበር የሚባለው) እቴጌ መጥተው ሠፈሩበት፡፡

ከዚያም ቤተ መንግስቱ የሚሰራበትን ቦታ መርጠው ቤተ መንግስቱ ተሰርቶ በዙሪያው ደግሞ ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ፤ ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ ለሌጋሲዮኖች (ኤምባሲዎች) መሬት እየቆረሱ እየሰጡ አሰፉት፡፡ በተለይ ታዝበን ከሆነ ለሌጋሲዮኖቹ ወንዝ የሚሻገሩ መሬቶች ነው የተሰጡት፡፡ ሌጋሲዮኖች ድልድይ እንዲሰሩላቸው፡፡ የፈረንሳይ ድልድይ፣ የጀርመን ድልድይ፣ የጣሊያን ድልድይ፣ የእንግሊዝ ድልድይ የምንላቸው ያኔ የተሰሩ ናቸው፡፡ በዚህ መልኩ ነው እንግዲህ የመናገሻ ከተማቸውን የመሰረቱት፡፡

ከዚያን ግዜ ጀምሮ አዲስ አበባ የሌላ አካባቢ ግዛት አካል ሆና አታውቅም፡፡ ይሄ በንግስተ - ነገስታት ዘውዲቱ ግዜ ቀጥሏል፣ በልጅ እያሱም ያው ነበረ፡፡ በቀዳማዊ ኃ/ስላሴም ቀጥሏል፤ እስከ ጣልያን ወረራ ድረስ፡፡ የጣልያን ወረራ ግዜ ጣልያኖች ክልሉን አስፍተው አዲስ አበባን ሸዋ ብለውት ነበረ፡፡ በቀዳማዊ ኃ/ስላሴ ዘመነ መንግስት ደግሞ እንደገና ተመልሶ "አዲስ አበባና አካባቢዋ" የሚል አስተዳደር ነበረ፡፡ ይህን የማውቀው የኔ አባት ከንቲባ ስለነበሩ ነው፡፡ ጣሊያን ከወጣ በኂላ ራስ አበበ ለጥቂት ወራት፤ ራስ መስፍን ስለሺም ለጥቂት ጊዜ ከንቲባ ነበሩ፡፡ እነሱን ተክተው ለአምስት አመት የአዲስ አበባ ከንቲባ የነበሩት የኔ አባት ናቸው፡፡ ያኔ እሳቸው የሚያስተዳድሩት አዲስ አበባ ከተማ "አዲስ አበባና አካባቢዋ" ነው ይባል የነበረው፡፡ ይሄ ደግሞ ደርግ በኢህድሪ ከፈጠረው ጋር ይመሳሰላል፡፡

**ግዮን፡- የሚመሳሰለው ምናቸው ነው?**

አምባሳደር ካሣ፡-የኢህድሪን የአዲስ አበባን ካርታ አይተን ከሆነ ኢህድሪ ሚኒሲፓል(Minisepal) አዲስ አበባ የሚባል ክልል ፈጥሮ፤ ከሚኒሲፓል አዲስ አበባ ደግሞ ሠፋ ያለ ሜትሮፖሊታን (Metropolitan) አዲስ አበባ የሚል እስከ ሞጆ፣ እስከ አዲስ አለምና ሌሎች ሠፋ ብሎ አዲስ አበባም የራሷ የግብርና ምርቶች አምራች ሀይል እንዲኖራት በማሰብ ጭምር ነበር ያደራጀው፡፡ ጓድ ግዛው የአዲስ አበባ ከንቲባ ሲደረግ የተመረጠበት መስፈርትም የግብርና ባለሙያ በመሆኑ ነበር፡፡ ለሚኒሲፓል አዲስ አበባ ከንቲባ የነበረው ዶ/ር (አሁን ስሙ ጠፋኝ) መሀንዲስ ነበረ፡፡ አዲስ አበባና አካባቢዋ የሚባለው ሸዋ ጠቅላይ ግዛት እየተጠናከረ ሲሄድ፣ መናገሻ፣ የረርና ከረዩን የመሠሉ በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙ አውራጃዎች እንዲጠናከሩ ተደረገና ዙሪያዋ የሚለው ቀርቶ ከንቲባው የከተማዋ ገገር ብቻ ነው የተደረገው፡፡ በቀዳማዊ ኃ/ስላሴ ዘመነ መንግስት፡፡ በደርግም እስከ ኢህድሪ ድረስ ቀጠለና ህገ-መንግስት ከታወጀና ምደባ ከተደረገ በኂላ ማዕከሉ ሚኒሲፓል አዲስ አበባ፤ ዙሪያው ደግሞ ሜትሮፖሊታን አዲስ አበባ ተብሎ ነበር የተከለለው፡፡ ያንን እንደገና ወያኔ አፍርሶ አዲስ አበባ እንዲጠብና ሚኒሲፓሉ ብቻ እንዲሆን አድርጓል፡፡

ወያኔ ያን ባደረገበት ግዜ በአዲስ አበባ ጉዳይ የታሪክ ቦንብ ነው የተከለው ባይ ነኝ፡፡ ለአዲስ አበባ ቢታሰብ ኖሮ በኢህዲሪ ዘመን በየአውራጃው የኢሰፓም፣ የአስተዳደርም ኃላፊዎች ተመድበው ይሄ ሜትሮፖሊታን የተባለው ሠፋ ያለ ክልል የአዲስ አበባ አካል መሆኑ ተረጋግጦ ነበር፡፡ ያንን የሚያስለውጥ ራሽናል (Rational) የሆነ ምክንያት አልነበረም፡፡ ከአዲስ አበባ ዙሪያ ምንም እንኳን ኦሮሞዎች ቢኖሩም በአንዳንድ አከባቢዎች ደግሞ ከእነሱ ጀርባ ያለው አማራ ነው፡፡

ከዚህ በመነሳት አሁንም እኔ የሚታየኝ የአንድ አገር መንግስት የራሱ የሆነ መናገሻ ከተማ ያስፈልገዋል፡፡ በፌደራል በፌደሬሽን የተደራጀ መንግስት ይህንኑ ነው የሚያደርገው፡፡ ከኛ ቀደም ያሉትን ብንመለከት ሁለት ማሳያዎች መውሰድ እንችላለን፡፡ የአሜሪካንን ያየን እንደሆነ ዋሽንግተን ዲሲን የፌደራል መንግስቱ መናገሻ ከተማ ሲያደርጉ፤ (Destrict of colombia) በፌደራል መንግስቱ ስር ያለች ልዩ ወረዳ ነች ብለው በአቅራቢያ ከነበሩት ክልሎች መሬት ቆርሰው በማዋሃድ ነው፡፡ ሌላዋ ምሳሌ ናይጄሪያ ነች፡፡ አቡጃ የፌደራል መንግስቱ መናገሻ ከተማ ነው የሆነው፡፡ በህገ መንግስታቸው አቡጃን ምንድን ነው ያሉት? The Spical federal teretorie (ዘ ስፔሻል ፌዴራል ቴሪቶሪ) ልዩ ፌዴራላዊ ግዛት ነው ያሉት፡፡ ሌሎችም ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል፡፡ ማዕከላዊ መንግስት የፌደሬሽኑን ማዕከል ሌላ መሬት፣ ሌላ አገር ሄዶ ሊያመጣ አይችልም፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ነው መቋቋም ያለበት፡፡

ለዚያ የተመረጠው ደግሞ በአፄ ሚኒልክ የተቆረቆረውንና እስከዛሬ የዘለቀውን መሬት ነው፡፡ ሌሎቹ እንዳደረጉት አዲስ አበባም The Spical federal teretorie (ዘ ስፔሻል ፌዴራል ቴሪቶሪ) መባል አለበት፡፡ ራሷን የቻለች ክልል መሆን አለባት፡፡ በላይዋ ላይ የሰፈረው ህዝብ ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ ስለሆነ ለኢትዮጵያ ህዝብ የሚሰጠውን መብት ሁሉ መጋራት ስለሚገባው የራሱን አመራር እየመረጠ፣ የፌደራል መንግስቱም ሆነ የራሱ የማዘጋጃ ቤት የሥራ ድርሻዎች ተለይተው፤ ህዝቡ በመረጠው በራሱ መተዳደር አለበት ብዬ አምናለሁ፡፡

**ግዮን፡- እናመሰግናለን፡፡**

**ከአምባሳደር ካሣ ከበደ ጋር በቀጣይ ዕትሞቻችን በምስራቅ አፍሪካ የኢትዮጵያ ሚና፣ በባንዲራና በህገ መንግስት እና በሌሎች ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥተን እንደምንወያይ አስቀድመን ለማሳወቅ እንወዳለን::**

**ማረሚያ**

በባለፈው ሣምንት በቁጥር 53 ዕትም በአምባሳደር ካሳ ከበደ ቃለ ምልልስ ላይ የተጠቀሱት የእንግሊዘኛ ቃላት "ኮንሲስተንት" የሚለው "ኮንስቲትዎንት" በሚል "ካፒታል ኢንሴንቲብ" የሚለው "ካፒታል ኢንቴንሲብ" በሚል፤ "ሌቨር" የሚለው "ሌበር" በሚል እንዲስተካከል በታላቅ ይቅርታ እንጠይቃለን!

**ዝግጅት ክፍሉ**

# የሃገር ባለውለታዎችን ማክበር ታላቅነት ነው

ለሃገራቸው ታላላቅ ተግባራትን ያከናወኑ ብዙ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ ዘመናት ኖረው አልፈዋል፡፡ የእነዚህን ታላላቅ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ታሪክ ለተተኪ ትውልድ ማሳወቅና ማስተላለፍ የሃገር ፍቅርን ከማስረጽ አኳያ ጠቀሜታው የጎላ ሲሆን ለሃገር ህልውናም መሠረት ነው፡፡ ለሃገራቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካበረከቱት ታላላቅ ኢትዮጵያውያን መካከል በመንፈሳዊና አለማዊ ተግባራት ሀገራቸውን በቅንነት ያገለገሉት መልአከ ብርሃናት ገብረ አጋዕዝት ገብረ ሚካኤል አንዱ ናቸው፡፡

መልካቸው ከዚህ ላይ በስዕላቸው የተገለጠው መልአከ ብርሃናት ገብረ አጋእዝት በ1878 ዓ.ም ጥር 25 ቀን በደብረ ብርሃን ከተማ ከአባታቸው አለቃ ገብረ ሚካኤል ከእናታቸው ከወ/ሮ ጥሩነሽ በዘመኑ ተወለዱ፡፡ አባታቸው በጣም የተማሩ የብሉያትና የቅኔ መምህር ስለ ነበሩ ዜማንና ቅኔን እያስተማሩ በመንፈሳዊ ትምህርት እየቃኙ አሳደጓቸው መልአከ ብርሃናት ገብረ አጋዕዝት ለንቃትና ለትጋት ለቸርነትና ለየዋሃነት ገና ከልጅነታቸው የታደሉና በአእምሮ ጠባይዕ የታነጹ በመሆናቸው ሁሉን የመውደድና በሁሉ ዘንድ የመወደድ ጠባይ ነበራቸው ገና በለጋነታቸውም የዕድሜ ወጣትነታቸውን የአእምሮአቸው ሽምግልና ስለ ተጫነው ግዕዘ ህጻናትን እስካለፉበት ዘመን ካልሆነ በቀር በልጅነት ጠባይ የተገመቱበት ጊዜ አልነበረም፡፡ መንግስትም የማስተዳደርና የስራም ዕድል እንዳላቸው ስላወቀ እንደ መልካም ተክል እየተንከባከበ ከሹመት ወደ ሹመት በማሳደጉ መልአከ ብርሃናት ገብረ አጋዕስት በቤተ ክህነት እንደ ብርቅ ሆነው ይታዩ ነበር፡፡

በ1910ዓ.ም በደብረ ሲና አውራጃ የምትገኘውን የአፋፍ ወይራ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን አለቅነት ተሾሙ ከዚያም ሁለት አመት ተኩል ያህል እንዳስተዳደሩ በ1913ዓ.ም የአንኮበር ጊዮርጊስ ደብር አለቅነት ተሰቷቸው ሶስት አመት ያህል ከቆዩ በኋላ ንቃታቸውና ትጋታቸው ዕድላቸውን እያፋጠነው ስለሄደ ተወልደው ያደጉበትን የአባታቸው ዕልቅና በ1916ዓ.ም ተሾሙ::

በዚህ ጊዜ መልአከ ብርሃናት ገብረ አጋዕዝትና ደብረ ብርሃን እንደ ቃል ኪዳን ባልና ሚስት ዕድላቸው የተያያዘ ሆኖ ተገኝና የሁለቱም ዕድል ስመ አጠራሩን እያጋነነ መሄድ ጀመረ ከላይም



መልአከ ብርሃናት ገብረ አጋዕዝት




ባለቤታቸው ወ/ሮ በየነች ማንመክቶ

እንደተናገርነው መልአከ ብርሃናት ገብረ አጋዕዝት በአለባበሳቸውና በአቋቋማቸው በቅልጥፍናቸውና በስልጣኔአቸው ይልቁንም በደግነታቸው በሁሉ ዘንድ ዓይነ ግቡነት (ለሁሉ አይን ሞልቶ መታየት)ስለ ነበራቸው የቤተ ክህነቱን ስራ ሳይተው በሃገር ግዛቱም ስራ ገብተው እንዲያስተዳድሩ መንግስት አጭቷቸው ከጠላት ወረራ በፊት በነበረው ክልል መሠረት የደብረ ብርሃንና ያውራጃዋ ምክትል ገዢ ሁነው እንዲሰሩ በመደረጉ አስተዳዳሪነታቸው በመንግስትና በህዝብ ዘንድ የተወደደ ሁኖ ተገኝና ዋና ሃገረ ገዢ ሁነው እንዲያስተዳድሩ ጠቅላላው ሹመት ተፈቀደላቸው፡፡

በዚህ ጊዜ በቤተ መንግስቱና በቤተ ክህነቱም በኩል ያለውን ስራ ለማቃናት ብዙ ፍሬ ያለው ተግባር እንደ ፈጸሙ ከሰሚው ይልቅ በአይኑ የተመለከተው ስለሚበዛ ወደ ዝርዝሩ መግባት አያሻም ይሆናል ▸

እንጂ ይዘርዝር የሚባል ሲሆን ሰፊ ገጽ እንደሚወስድ እርግጥ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሌላውም ሁሉ ቢታለፍ በቤተ መንግስቱ በኩል ከዚሁ ከደብረ ብርሃን ላይ ግቢውን በጊዜው ሁኔታ አሳድሰው ለግብርም ማብሊያ የሚሆን ሰፊ አዳራሽ አሰርተው ከተማውም እንዲደምቅ የቡሎ ወርቁን ትልቅ ገበያ ከከተማው ውስጥ እንዲቆም አድርገው የስልክ ሽቦ አዘርግተው በሌላ በኩል ተቀይሶ የነበረውን የመኪና መንገድ ስለ ከተማው ድምቀት ከተማውን አቋርጦ እንዲሄድ ለመንግስት አመልክተው ከተማው


ንምራ ፡
አዲስ ፡ አበባ
ቀን ፡ ፲፱፻
ዓ. ም.
የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡
የጽሕፈት ፡ ሚኒስቴር ።
ጉዳዩ ፡
የጽሕፈት ፡ ሚኒስቴር ።


እንዲለማና ስመ አጠራሩ እንዲከብር አድርገዋል በቤተ ክህነትም በኩል ለደብረ ብርሃን ከተማ የአስራ ሁለት መምህራን ቀለብ አስፈቅደው መምህራኑም ከሩቅ ቦታ አስመጥተው የመጻህፍትና የቅኔያት የዜማና የንባብ ትምህርት እንደ ምርት እንዲታፈስ አድርገዋል፡፡ በዚሁም ላይ መምህራኑና ተማሪዎቹን እንዳይርባቸው በልብስ እየተንከባከቡ ሲያስደስቷቸው እንደ ነበር የማያረጋግጥ መምህርና ተማሪ አይገኝም በየጊዜውም ለመንግስት እያመለከቱ ለመምህራኑ ጉርሻና ሽልማት ለተማሪዎቹ ብዙ የአቡጀዲ ጣቃ በማሰጠት ያባትና የእናት ያህል ሁነው ችግራቸውን መከላከል የማይዘነጋ ሞያቸው ነበር፡፡

በተለይ በፈረስ ስማቸው አባ ዝናቡ ገብሬ በመባል የሚታወቁት መልአከ ብርሃናት ገብረ አጋዕዝት የቤታቸው ማዕድ እንደ አብርሃም ማዕድ ለሁሉ የተዘረጋ በመሆኑ ከፍትፊቱ ፊቱ ያጠግባል እንደሚባለው አላፊ አግዳሚውን ወጪ ወራጁን በብሩህ ገጽ እየተቀበሉ ሲጋብዙ ልግስናቸው ያንድ ቀን ቁጠባ አሰናክሎት አያውቅም ይልቁንም ደብረ ብርሃን ከትግሬ ከጎንደርና ከወሎ ወደ አዲስ አበባ የሚመጣ መንገደኛ መተላለፊያ በመሆኗ መላከ ብርሃናት ገብረ አጋዕዝት በዚሁ በኩል የሚተላለፉትን መኳንንትና ሊቃውንትስለመንግስታቸውና ስለ ሃገራቸው ክብር በሚያስደስት ግብዣ እያስተናገዱ እንደሚያስተላልፉ ሁሉ የሚያውቀው ነው፡ ፡ ከሁሉም ይልቅ መላከ ብርሃናት ገብረ

## የአለቃ ገብረ አጋዕዝት ሃላፊነቶች

- የአፋፋ ወይራ ማርያም ቤተክርስቲያን አለቃ
- የአንኮበር ጊዮርጊስ ደብር አለቃ
- የደብረ ብርሃን አውራጃ ምክትል ገዥ
- የደብረ ብርሃን ዋና ሀገረ ገዥ
- የደብረ በግዕ አቡነ ህፃን ሞግ ደብር አለቃ
- የአዲስ አበባ (እንጦጦ) ቅዱስ ዑራኤል ደብር አለቃ
- የደብረ ብርሃን ማዘጋጃ ቤት ሹም
- የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሊቀ ካህናት
- የብፁዕ ወጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ረዳት


አለቃ ገብረ አጋዕዝት ባለቤታቸው ወ/ሮ በየነች እና ልጃቸው አቶ ማህተመወርቅ


ንምራ ፡
አዲስ ፡ አበባ
ቀን ፡ ፲፱፻
ዓ. ም.
የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡
የጽሕፈት ፡ ሚኒስቴር ።
ጉዳዩ ፡
አለቃ ፡ ገብረ ፡ አጋዕዝት ፡
የጽሕፈት ፡ ሚኒስቴር ።

ከንጉሠ ነገሥቱ የተሰጣቸው የሹመት ደብዳቤ

## ያበረከቷቸው ስራዎች

- በደብረ ብርሃን ሰፊ አዳራሽ አሰርተዋል
- የቡሌ ወርቁ ትልቁ ገበያ በከተማው ተመስርቷል
- የስልክ ሽቦ አዘርግተዋል
- በደብረ ብርሃን ከተማ የሚያቋርጥ የመኪና መንገድ አሰርተዋል
- የመፃህፍት የቅኔ ዜማና የንባብ ትምህርት ቤት ከፍተዋል፡፡
- በደብረ ብርሃን የቧንቧ ውሃ በማስገባት
- የኤሌትሪክ መብራት በማስገባት

አጋዕዝት በየጊዜው ከክብር ወደ ክብር ከደረጃ ወደ ደረጃ እየተረማመዱ ሲሄዱ ለታላቅ ለታናሹ ባንድ ጎብረ መልክዕ ሁነው የትህትናቸውን አርዓያ ከማሳየታቸው በቀር የታላቅነታቸው ስሜት ትህትናቸውን ተጭኖት የታየበት ጊዜ አልተገኘም::

ይህንንም በመሰለው ትጋት ለደብረ ብርሃን ከተማ ልማትና ዕድገት ሌት ከቀን ሲጥሩ በ1924ዓ.ም የደብረ በግዕ አቡነ ህጻን ሞዓ ደብር አለቅነትን በመንግስት ፈቃድ ተሹመው በዚያ ሁለት አመት ያህል እንደ ቆዩ በ1926ዓ.ም ለእንጦጦ ማርያም ደብር (መንበረ ጸሀይ) ሶስተኛ የሆነው የአዲስ አበባ ቅዱስ ዑራኤል ደብር (ደብረ ጽጌ) አለቅነትን በግምጃ ሱሪና በሃር ጥላ ሙሉ ማአረግ ተደርጎላቸው ተሾሙ፡፡

በዚሁም ሁለት አመት ያህል እንደ ቆዩ ልዑል አልጋ ወራሽ መርዐድ አዝማች አስፋ ወሰን ወደ አዲስ አበባ በመጡበት ጊዜ አብረው መጡ በዚህም ጊዜ የወራሪው ግፈኛ ሃይል እየገፋ ስለ መጣ ከወራሪው ጠላት ጋር ግንባር ለግንባር ገጥመው ለመዋጋት ከጉብዝና በላይ በሆነ ጀግንነት እስከ ዕረፍታቸው ቀን ጀብዱ የሰሩት ስመጥሩው ጀግና ደጃዝማች ፍቅረማርያም(አባ ተጫን)የአርበኝነትን መሠረት ሲጥሉ መልአከብርሃናት ገብረ አጋዕዝትም ስለሃገራቸው ነጻነት ቀናዒ ሁነው ጠላትን በመከላከልና አርበኞችንም በማነቃቃት አብረዋቸው ሠርተዋል፡፡ጀግናው አባ ተጫን ሲሞቱ ግን ሰዎቻቸው ወደየክፍሉ ሲበታተኑ መልአከ ብርሃን ገብረ አጋዕዝትም ለጠላት በሰላማዊነት አርአያ እየታዩ ከልጆቻቸው ጋር ተቀምጠው ጠላትን በጸሎትና በዕንባ መካሰስ እንደሚሻል ስለ ገመቱ ወደ ደብረ ብርሃን ከተማ ገብተው ተቀመጡ፡፡

ወራሪው ጠላት የፖለቲክ ሰው መሆናቸውን ስላወቀ ፈቃዱ ሳይሆን የደብረ ብርሃንን ልቅናና ለደብረብርሃን ኮሚሣሪያቶ በተከለለው አገር ሊቀ ካህናቱን ሰጠሁህ አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ መልአከ ብርሃናት ገብረ አጋዕዝት በሚቻላቸው ሁሉ የኢጣሊያ ባለስልጣኖች ከአጥፊነታቸው የሚታገሱበትን ምክር በልዩ ልዩ ዘዴ እያሳሰቡ የቅንነት ተግባራቸውን ከመፈጸምና ከማስፈጸም ሳያቋርጡ የወረራውን ዘመን አሳለፉት፡፡ አሸናፊው ንጉሠ ነገሥታችን ግርማዊ ጃንሆይ ቀዳማዊ ሃይለሥላሴ በድል አድራጊነት ከዙፋናቸው ላይ ከተገኙበት ቀን ጀምሮም የዕድላቸው መሠረት የሆነውን የደብረ ብርሃንን ልቅና ፈቅደውላቸው በዚሁም ላይ የመንፈሳዊ ጉባኤ አማካሪ ሁነው ሳሉ የማስተዳደር ችሎታና ስጦታ እንዳላቸው የሚያውቀው መንግስት በልቅናቸው ላይ የደብረ ብርሃን ማዘጋጃ ቤትን ሹመት ደርበው እንዲሠሩ ስላደረገ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ከብዙ ዘመን ጀምሮ በደብረ ብርሃን ከተማ የነበረውን የውሃ ችግር ለማስወገድ በግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድ ርቀቱ በግምት ከሁለት ኪሎ ሜትር ከማያንስ ዳገትነት ካለው አስቸጋሪ ቦታ ለከተማው ህዝብ ውሃ በቦንባ እንዲገባለት አስደርገው እነሆ ዛሬ የደብረ



የደብረ ብርሃን ቤታቸው (አሁን ያለበት ሁኔታ)



የአዲስ አበባ ቤታቸው (አሁን ያለበት ሁኔታ)

▶ብርሃን ከተማ ዓይነተኛ ችግሩ ተወግዶለት ንጉሰ ነገስቱን እያመሰገነ በደስታ ይኖራል፡፡

ይልቁንም በደብረ ብርሃን ከተማ አትክልት ባለመኖሩ ግልጽና አውላላ ሁኖ የነፋስ ሃይል ይበዛበትና ይበረታበት ስለ ነበረ በትጋታቸው ብዙ የባህር ዛፍ አስተክለው የአትክልቱ ህብር ለከተማው ጌጥ ከመሆኑ ሌላ ይሄው ዛፍ ለማገዶና ለቤት ሥራ ለነፋሱም መከላከያ እንደሚጠቅም ተስፋ የሚሰጥ ሆኖ ተገምቷል፡፡ከዚህም ሌላ የኤሌክትሪክ መብራት እንዲገባ ከተማውም እንዲስፋፋ ሳንድ ጊዜ እንኳ ምኞታቸውንና ትግላቸውን ያቀዘቀዙበት ሰዓት አይገኝም፡፡

ከዚህም ሁሉ በኋላ በ1937ዓ.ም (በዘመነ ማቴዎስ) በግንቦት ወር በግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድ ከደብረ ብርሃን ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው መጥተው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ካህናት ሆነው እንዲሰሩ ለከፍተኛው ሹመትና መዓረግ ስለ ተመረጡ ከዚያ ጊዜ ጀምረው እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር መሻሻል ለብጹዕ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ረዳት ሁነው ያደረጉት ድካም በብዙ ወገን ፍሬውን አበርክቷል፡፡


ይሁን እንጂ ሰው ምንም ዓዋቂና የከበረ ቢሆን ጊዜው ሲደርስ ከሞት ፊት መሰወር ስለማይቻለው ባለፈው የግንቦት ወር ከመንግስት ተልከው ወደ አክሱም ሄደው በድንገት ስለታመሙ ስለ ህመማቸው ለመረዳት ወደ ዓድዋ ሆስፒታል በገቡ በአምስተኛ ቀናቸው ሰኔ 4(ረቡዕ) /1940 ዓ.ም ከቀኑ በአራት ሰዓት በሃምሳ ሁለተኛ ዘመናቸው ዓርፈው የአገልጋዩን ውለታ የማይረሳው መንግስት ሬሳቸው ወደ ተወለዱበትና ወደ አደጉበት ደብረ ብርሃን መጥቶ ከአባታቸው አለቃ ገብረ ሚካኤል አጽም አጠገብ እንዲያርፍ ስለ ፈቀደ ከዓድዋ በመኪና ተጉዞ መጥቶ ሰኔ 6 ቀን (ዓርብ)በ5 ሰአት ተኩል ደብረ ብርሃን ከተማ ደረሰ ሬሣውንም ለመቀበል እስከ ደብረ ሲና ድረስ በየመንገዱ ብዙ ተቀባይ በአውቶሞቢል ሲተላለፍ ይታይ ነበር፡፡


ከአዲስ አበባም በየአውቶሞቢሉና በየአውቶቡሱ ለቀስተኛው ሲጎርፍ የቱን ያህል ሰውን ወዳጅ እንደነበሩ ምስክር እንደማያሻ ራሱ ማስረጃ ሁኖት ነበር፡፡ከከተማው ጫፍ ድረስ ለቀስተኞቹ ሬሳውን ተቀብለው የጉዞ ፍታት እየተደረገ ብጹዕ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ሊቃውንቱና ካህናቱ መኳንንቱና ህዝቡ በተሰበሰቡበት የሀዘን ጥሩንባ እየተነፋ ህዝቡ ሁሉ በእንባ እየታጠበ ሰባት ሰዓት ሲሆን ግብአተ መሬት ሆነና የቀብሩ ሥርዓት ተፈጸመ፡፡

ይልቁንም የዘመድ ቁስ ሲፈታም ሲያለቅስ የተባለው ቃል በደብረ ብርሃንና በሌሎቹም ካህናት ስለ ተፈጸመ እንደበታቸው ጸሎቱን ሳያቋርጥ ዕንባቸው እንደ ሰን ውሃ ሲፈስ ይታይ ነበር በከተማው የሚገኙት የመንፈሳዊ ትምህርት ቤት ተማሪዎችም ልብን በሚነካ ስሜት የሃዘኑ መግለጫ የሆነውን መዝሙረ ብካይ አሰምተው ህዝቡ ተሰናበተ፡፡

ዜና ቤተ ክርስቲያን የመልአከ ብርሃናት ገብረ አጋዕዝት ሞት ምንም እንኳ ጉዳቱ ለቤተ ክርስቲያን ቢሆን ለባለቤታቸውና ለልጆቻቸው የሀዘን ተካፋይነቱን በመግለጽ ሁሉን ማድረግ የባህርዩ የሆነ አምላክ መጽናናትን እንዲያዝላቸው መልካም ምኞቱን ይገልጻል፡፡

ምንጭ-ዜናቤተክርስቲያን ዘኢትዮጵያ ቁ.20(ገጽ203)


የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡
፬፻
አልጋ፡ወራሽ፡ተፈሪ፡መ፡
፪፻፵፲
የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን፡
ይድረስ ካለቃ ገብረ እግእዝት
እንደምን ሰንብተሃል እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅናነኝ፡
የጻፍከልኝም የብጹዕ ዮርዮኖስ፡ ከለሣሳብህም እግዚአብሔር ይ
ስጥልኝ፡ ቀቁ ሞውዓሞ ሰሞቹ ነበር፡ እውነም እንዳ ጊዜ መጥ
ተህ ሁሉንም ነገር እንነጋገርዋለን። መስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፲፱
ዓ.ም አ.አ.


ቍጥር ፩ ፻፻
ቀን፡ ፲፱፻፴፩ ዓ፡ም፡
ጌ፡ መንን፡
ለቄጊ መነን፡
ይድረስ ከአለቃ ገብረ አጋዕዝት
እንደምን ሰንብተሃል እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህናነኝ
እዚህ ያሉ ... በስጋ ነገር ለትዕዛዝ ... ደርገናቸው
... ስለ ... ስለ ... ደስ አለኝ ከዚህ ቀደም
... መገዣ ተብሎ ... ገንዘብ አምሣ ብር ...
... አምሣ ብር ... በመቶ ብርስ
... ገዝተህ እንደ... የሚገዛ ይገኝ እንደሆነ እየተጨመ
... አድርገህ እንድትገብዛቸው ይሁን ... ቀን
፲፱፻፴፩ ዓመት

# ስለ ሀዘኑ መግለጫ

# ካለቃ ሳሙኤል የተጻፈ

መወድስ ቅኔ ህያው እግዚኣብሄር ለመልአከ ብርሃን በሞት እምነ መላእክት አሕፀፅኮ፡፡

ሞተ መላእክት ለከ እንዘ ፈቃድከ አኮ ድህረ አንተ እንከውይነሰብ መላእይከ ረሰይኮ፡፡

ናሁ እምዘ ፈነኮ እምነ መላእክት እኣላፍ እስመ እየሃፅፅ በተልእኮ ፡፡

ንሕነሰ እንበይነዝ ከመ ኢንግበር ተሐውኮ፡፡

እምዓለመ ሞት ለኤልያስ ዓለመ ሕያዋን አስተሐለፍኮ፡፡

ወእፎ እምቅድሜነ አንተ ለመልአከ ብርሃን ሰወርኮ፡፡

እንዘ ንሕነ በብርሃኑ ለስመ ዚአከ ንባርኮ፡፡

# ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ "ዕንቁላሉን ሰብረው የወጡ" ታማኙ ፕሬዝዳንት!

በሮቤል ምትኩ



ከሀገር መሪነትም ሆነ ከድርጅት አባልነታቸው በፍቃዳቸው በመልቀቅ፣ ከከንቱ ዝናና ሀብት ይልቅ እውነተኛ ደስታ የሚገኝበት የሕዝብ አገልጋይነትን በመምረጥ፤ መንገድ ተዘግቶላቸው፣ ቀይ ምንጣፍ ተነጥፎላቸው፣ በተንጠላላው ቤተ መንግስት በጠባቂዎች ታጅበው ይኖሩ የነበሩት ታላቁ ሰው ለህዝብና ሀገር ሲሉ ዝቅ ብለው መኖርን የመረጡት ከአስራ ስድስት ዓመታት በፊት ነበር::

የርዕሰ ብሄርነታቸው መብት ተገፍፎ፣ ያለ አንዳች ድጋፍና ዕርዳታ እንደ አልባሌ ዕቃ የተጣሉት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ከመለስ ዜናዊ ኢህአዴግ በተቃራኒው በመቆማቸው፣ ስልጣን ከለቀቁባቸው ጊዜያት በኋላ በነበሩት በርካታ ዓመታት እጅግ አሳዛኝና ፈታኝ የመከራ ዘመኖችን ለማሳለፍ ተገደዋል:: "ክብሬን፣ ጥቅሜንና ዝናዬን" ያላሉት ፕሬዝዳንት ነጋሶ፤ በአጃቢ ደህንነቶችና ሞተረኞች ልዩ እጀባ ለሰባት ዓመታት በተንሸራሸሩበት፣ የአዲስ አበባ አውራ ጎዳና ላይ ለአስራ አምስት ዓመታት በላይ እንደማንኛውም ተራ ዜጋ በሚኒባስ ታክሲ ተመላልሰውበታል:: ከዛም ከፍ ሲል በእግራቸው ተረማምደውበታል::ለመሆኑ ዝቅ ብሎ ከመኖር ባሻገር፣ በዚያ ድቅድቅ ጨለማ ዘመን ራሳቸውን ለመስዋዕትነት አዘጋጅተው፣ ነገሮችን በአደባባይ የተጋፈጡት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ማን ናቸው

## ደምቢ ዶሎ– ቄስ ጊዳዳና ዶ/ር ነጋሶ

ኢትዮጵያን ለሰባት ዓመታት በፕሬዝዳንትነት ያገለገሉት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በምዕራብ ወለጋ ደምቢዶሎ ከተማ ነው የተወለዱት:: አባታቸው ቄስ ጊዳዳ ሶለን የቤተል ቤተክርስቲያ መስራች እንደሆኑ ይነገርላቸዋል:: በበርካታ ክፍላተ ሀገራት እየተዘዋወሩ ወንጌል በመስበክ የሚታወቁት፣ አይነስውሩ ወንጌላዊ ቄስ ጊዳዳ ሶለን የመጡበት መንገድ፣ ሕይወትን የተጋፈጡበት፣ መከራና ችግሮችን አልፈው ያሰቡትን ያሳኩበት መስመር የማረካቸው የውጭ ዜጎች የነጋሶን አባት ታሪክ በእንግሊዘኛ ጽፈው ለህትመት አብቅተውታል:: የቄስ ጊዳዳ ሶለን ግለ ታሪክ መጽሐፍ ከአመታት በፊት ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ለህትመት በቅቶም ነበር:: ቄስ ጊዳዳ ገና ብላቴና ሳሉ ነበር ከአለም ፈታኝ መከራ ጋር የተጋፈጡት:: "የጨለማ ሌላኛው ገጽታ" በተሰኘው መጽሐፋቸው ላይ እንደተረኩት ገና በአምስት ዓመት ታዳጊነት ዕድሜያቸው ነበር አይኖቻቸው ከብርሃን ተጣልተው ማየትን ያቆሙት::

ከወጣትነት ዕድሜያቸው አንስቶ ወንጌል እየሰበኩ፣ "ኢየሱስ ያድናል" እያሉ የቀሪ የሕይወት ዘመናቸው ተጋሪን ሲያፈላልጉ ነበር ከደንቃ ማዶ- አረንገማ ወንዝን ሲሻገሩ ከምትገኘው ትንሿ "ኩሬ" መንደር ዲንሴ ሾሊ የተባለች ወጣት በሚስዮናውያን ጓደኞቻቸው አማካይነት የተመረጠችላቸ:: በዚህ መልክ ትዳር የመሰረቱት ሁለቱ ጥንዶች አስር ልጆችን በሕይወት ዘመናቸው ቢያፈሩም የመጀመሪያና ስምንተኛዋ ልጆቻቻቸው ብዙም ሳይቆዩ ነው ይህቺን ዓለም በሞት የተለዩዋት:: ከመጨረሻው ልጅ ኤልሳኢ ጊዳዳ አንድ እርከን ቀድመው ጳጉሜ 3 ቀን 1935 ዓ.ም ዶምቢዶሎ መሀል ከተማ፣ ቤተል ቤተ ክርስቲያን መንደር ነው ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የተወለዱት::

ነጋሶ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በዶምቢዶሎ፣ አልፎ አልፎም አባታቸው በወንጌል ስራ ምክንያት ወደ ሚዛን ተፈሪ በመጓዛቸው እየተሸከረከሩ ለማመር ተገደዋል:: ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የአስራ አንደኛ ክፍልን በዕደ ማርያም ትምህረት ቤት ተከታትለዋል:: ከልጅነታቸው አንስቶ በቀለም ትምህርት የላቀ ውጤት በማስዝመዝገብ የሚታወቁት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በመንፈሳዊ አገልግሎቱ ዘርፍም ገና በታዳጊነት ዕድሜያቸው ጠንካራ እንቅስቃሴ ያደርጉ እንደነበር ግለ ታሪካቸው ያስረዳል::

የአስራ ሁለተኛ ክፍልን በድሮ ቀዳማዊ ኃ/ ስላሴ፣ በአሁኑ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ግቢ ውስጥ በሚገኘው በዕደ ማርያም ት/ቤት ውስጥ እያሉ ነበር ነጋሶ ጊዳዳ ከፖለቲካ ጋር የተወዳጁት:: ገና ከማለዳው የገቡበትና የተሳተፉበት የመጀመሪያው ስብሰባ ደግሞ በሜጫና ቱለማ ማህበር የተዘጋጀ ሲሆን፣ የስብሰባው መሪና ተናጋሪ ጄነራል ታደሰ ብሩ እንደ ነበሩም ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ያስታውሳሉ::"በዛን ወቅት የነበረው የንጉሱ አገዛዝ ከበዝባገሮች ጋር የሚተባበር ነበር:: ተማሪው ደግሞ ስርዓቱ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶችን የማያስከብር እንደሆነ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ትግላችን ጠንካራ ነበር" በማለት የጥንቱን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ የሚገልፁት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፤ በዚህ የፖለቲካ የተቃውሞ እንቅስቃሴያቸው ላይ እያሉ ሁለቴ ለአጭር ገዜያትም ቢሆን ለዕሥር ተዳርገዋል

ከአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ በታሪክ የትምህርት ዘርፍ በዲግሪ ከተመረቁ በኋላ በቀጥታ ወደ መምህርነት ሙያ የገቡት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በ1965 ዓ.ም ክረምት ላይ ነበር ትዳር ▶

የመሰረቱት:: ከዛ ቀደም ብሎ ባለው አፍላ የወጣትነት ዘመናቸው በደምቢዶሎ፣ ሚዛን ተፈሪና አዲስ አበባ ከተለያዩ ልጃገረዶች ጋር ፍቅር ጀማምረው እንደነበርም “የነጋሶ መንገድ” በተሰኘው ግለ ታሪክ መጽሐፋቸው ላይ ሳይሸሽጉ ጠቃቅሰዋል:: ከወ/ሮ ደሊቱ ጋር በትዳር የተቆራኙት ነጋሶ በአመቱ “ኢብሳ” የተሰኘ የመጀመሪያ ልጃቸውን ያገኙ ሲሆን፤ ወደ ጀርመን ለትምህርት ከተጓዙ ከአንድ ወር በኋላ ደግሞ “ጃለሌ” የተሰኘች ሴት ልጅ ተወልዶላቸዋል::

አፄ ኃይለ ስላሴ ከስልጣን ከተወገዱ በኋላ ከጥቂት ሳምንት ቆይታ በኋላ ነበር ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ለመስራት ወደ ጀርመን ያቀኑት:: በወቅቱ የባህር ማዶ ጉዞአቸውን አስመልክተው ከነገሯቸውና ከሸኟቸው ሰዎች መሀል የኦነግ (የኦሮሞ ነፃነት ግንባር) መስራችና ሊ/መንበር ሌንጮ (ዮሐንስ) ለታ አንዱ ነበሩ:: አቦ ሌንጮ በሽኝቱ መሀል ነገሶን ምን ለመማር እንደወሰኑ ይጠይቋቸዋል:: ነጋሶም ታሪክ ለማጥናት እንደወሰኑ ይገልጻሉ:: ይሄኔ ሌንጮ ለታ “አንተ ሄደህ ታሪክ ተማር፤ እኛ እዚሁ ሆነን ታሪክ እንሰራለን” በማለት ያሾፉባቸዋል::በዚህ መልክ የትምህርት ሕይወታቸውን የገፉት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በታሪክ ሶስት ዲግሪዎችን አግኝተዋል:: ወይም ዶክትሬታቸውን ይዘዋል::

## ፕሬዝዳንት ነጋሶ፣ የስልጣን ዘመናቸው

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ከ1987 ዓ.ም እስከ 1993 ዓ.ም ድረስ ለሰባት ዓመታት የሀገሪቱ ፕሬዝዳት በመሆን አገልግለዋል:: ገና ከጅምሩ ሹመታቸውን በተመለከተ የተለያዩ ቡድኖችና ግለሰቦች ቢዘባበቱም ነጋሶ ግን እንደታሙት እንግዳ ተቀባይና ሸኚ፣ የወያኔ ታዛዥና ተላላኪ ብቻ ሆነው አላገለገሉም:: የማፊያው ቡድን ሀገራዊ ዘረፋና የተትረፈረፈ ጥቅምም አላጓጓቸውም:: የማይመስላቸውን ነገር ፊት ለፊት በመጋፈጥና ለእውነት በመሟገት የሚታወቁት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የመለስ ዜናዊ ሕወሓት በዘር ፖለቲካ ላይ ተንጠልጥሎ በዚህች ሀገር ላይ የሚፈፀመው ግፍና በደል ሞልቶ ሲፈስ፤ የመለስና ጓደኞቻቸው አምባገነንነትና ማን አለብኝነት ገዝፎ ሲመጣ በፅኑ ተቃውመዋል::

ስርዓቱ አስቀድሞ መበስበሱን፣ የህዝብ መብትና ነፃነት መገፈፉን አስቀድመው የተረዱት ክቡር ፕሬዝዳት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ከሰባት ዓመት የርዕሰ ብሄርነት ስልጣናቸው በፍቃደቸው የለቀቁት፤ ከኦህዴድና ኢህአዴግ ጋር የነበራቸውን እህል ውሃ ያቋረጡት፤ በ1994 ዓ.ም የኢህአዴግ ስብሰባ ላይ የውስጣቸውን ያለ አንዳች ፍርሃት ከመግለፅ ባሻገር የስርዓቱን መሪ መለስ ዜናዊ ላይ የሰላ ትችት ከሰነዘሩ በኋላ እንደሆነ ይታወቃል::

## መለስ ዜናዊ፣ የገነት ዘውዴ ልቅሶና አልማዝ መኮ

የሕወሓትን መሰነጣጠቅ ከተቋጨ በኋላ የኢህአዴግን ስብሰባ የመሩት ጠ/ሚ/ር መለስ



ዜናዊ ሲቀናቀኗቸው የቆዩትን ግለሰቦች ሽንፈት አስመልክተው “ጃኬታቸውን አስወልቀን፣ ራቁታቸውን አባረርናቸው” በሚል ተራ ቃል፤ በትግል አጋሮቻቸው ላይ ሲሳለቁ በአዳራሹ የነበረው ታዳሚ ግማሹ በአድናቆት፣ አንዳንዱ ባግራሞትና በዝምታ ተውጦ ዲስኩሩን ሲያዳምጥ አገላለፁ ያልተመቻቸው ዶ/ር ነጋሶ ግን አጋጣሚውን በቸልታ ማለፍ አልፈለጉም::

የመለስ ዜናዊ ዕብሪታዊ አነጋገር በእጅጉ ያናደዳቸው ደፋሩ ፕሬዝዳንት “ይቅርታ ! አሁንስ መንግስቱን መንግስቱን ፣መሰልከኝ” በማለት ሲገልጿቸው ቤቱ ሙሉ ለሙሉ በድንጋጤ ተውጦ ነበር:: አንዳንዶች የነጋሶ ድፍረት ፈፅሞ ያልጠበቁት ሲሆንባቸው፤ ብዙዎች ደግሞ “እንዴት መለስ ዜናዊን ይተቻል” ሲሉ ያለማቋረጥ ማጉረምረም ጀመሩ:: በተለይም ከአጠገባቸው ተቀምጠው የነበሩት፣ በወቅቱ የትምህርት ሚኒስቴር የነበሩትና በ”አፍቃሪ ወያኔነት” የሚታሙት ወ/ሮ ገነት ዘውዴ “መለስን እንዴት ከመንግስቱ ጋር ታወዳድረዋለህ?” በማከለት ልጇን ቀብራ እንደመጣች እናት ስቅስቅ ብለው አለቀሱ::

ሌላኛዋ የመለስ ዜናዊ ታማኝ አገልጋይና የፌደሬሽን ም/ቤት አፈ ጉባኤ የነበሩት ወ/ሮ አልማዝ መኮ ደግሞ፤ ፍፁም አሳፋሪ በሆነ ሁኔታ በመድረኩ ላይ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን የሰደቡበትና የወረፉበት ንግግርም አይረሳም:: ነጋሶ መለስን መተቸታቸው ያንጨረጨራቸውና ከስርዓት በወጣ መልኩ እንዲቀባጥሩ ያስገደዳቸው ወ/ሮ አልማዝ መኮ፣ ለኦህዴድ አባልነት የተመለመሉትና ለነበሩበት ቦታ ያበቋቸው ግን ታላቁ ሰው ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ነበሩ:: ከሁሉም የሚገርመው ደግሞ ወ/ሮ አልማዝ ይህን ከተናገሩ ከአንድ ዓመት ከመንፈቅ በኋላ ለስራ ጉዳይ በሄዱበት አሜሪካ ኢህአዴግን በመክዳት፣ የመለስ ዜናዊን መንግስት “አምባገነንና ጨፍጫፊ ነው” ሲሉ መመስከራቸው ነበር::

አርብ ሰኔ 15 ቀን 1993 ዓ.ም እየተካሄደ በነበረውና መለስ ዜናዊ በሚመሩት ስብሰባ ላይ እጃቸውን በማውጣት “የኢህአዴግ አካሄድ ስላልተስማማኝ እና ህሊናዬ ስላልፈቀደ፣ ከዛሬ ጀምሮ ከኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚም ሆነ ከምክር ቤት ወጥቻለሁ” በማለት ሀሳባቸውን በግልፅ የተናገሩት ዶ/ር ነጋሶን በርካታ የም/ቤቱ አባላት ሀሳባቸውን ለማስቀየር ጥረት ቢያደርጉም አልተሳካላቸውም::

እንዲህ ባለው ለህዝብ ለሀገርና ለሕሊና ባለው ታማኝነት ከኢህአዴግ ጋር የተፋቱት ፤ በአንድ ወቅት “ዕንቁላሉን ሰብሬ ወጥቻለሁ” በማለት የሕወሓት/ ኢህአዴግን ፅንፍ የያዘና በዘረኝነት መንፈስ የታጠረ መጥፎ ቅጥር፣ ያለፍርሃት በመሰባበር ለብዙዎች አርአያ ለመሆን የቻሉት የቀድሞው የኢ.ፌ.ድ.ሪ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በ1997 ዓ.ም ምርጫ በትውልድ መንደራቸው ደምቢዶሎ በግል ተወዳድረው ለአምስት ዓመታት የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባል መሆናቸው ይታወሳል::

በቀጣይነትም አንድነት ፓርቲን በመመስረትና በሊ/መንበርነት በመምራት የሚታወቁት ክቡር ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ እስከ ሕልፈተ ሕይወታቸው ድረስ የኢትዮጵያን አንድነት በመመስከር ግንባር ቀደም ናቸው:: ጥቂት ከማይባሉ የጊዜው የኦሮሞ ልሂቃንና የፖለቲካ ሰዎች በተለየ መልኩ፣ ሀቁን ከመናገር ወደ ኋላ የማይሉት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፤ በሕወሓት ሰዎች የፈጠራ ድርሰት የአማራና ኦሮሞ ብሄሮችን ለማጣላት የተሸረበውን የፈጠራ ታሪክ “ውሸት ነው፤ ምኒልክ ፈፅሞ ጡት አልቆረጡም:: ይህን የሚያሳይ ተጨባጭ ማስረጃ የለም” ሲሉ ደጋግሞው በአደባባይ መስክረዋል:: የታሪክ ምሁሩ ዛሬ አዲስ አበባን ለመጠቅለል ላኮበኮቡ ኃይሎችም “ፊንፊኔ የሚባል ከተማ የለም፤ በርግጥ አዲስ አበባ የቀድሞ ስሟ ሸጋ አገር (ሸገር) ነበር” ሲሉ ታሪክ በራገሮችንም ሞግተዋል::

የለውጡ ቡድን ስልጣን በያዘ ማግስት በወያኔ ተገፍተው፣ የፕሬዝዳንትነት ክብራቸው ተረስቶ፣ ለ15 ዓመታት በችግርና ስቃይ ውስጥ የነበሩትን ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን ክብር በመስጠት አስፈላጊውን ድጋፍ አድርገዋቸዋል:: “እኔ በኦህዴድ ውስጥ እያለሁ ለማና ዐቢይን አላውቃቸውም፤ ወይም አልነበሩም:: ግን የሰራኸው ለድርጅቱ ነውና ክብር ይገባኻል ሲሉ አስታውሰውኛል” ለሚሉት ለቀድሞው ፕሬዝዳንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፤ እነ ለማ መገርሳ መኪና ከመሸለም ባሻገር፣ ለአንዳንድ ነገሮች የሚስፈልጓቸው ወርሃዊ ወጪዎች እንዲሁም የሀገር ውስጥና የውጭ ህክምናዎቻቸው በድርጅቱ እንዲሸፈን አድርገዋል::

በትምህርት ዓለም ጀርመን ላይ ከተዋወቋት ረጊና ጋር ግንቦት 20 1984 ዓ.ም በኢህአዴግ ታጋዮች የጋብቻ ስነ ስርዓት መሰረት ትዳር መስርተው “ተሊሌ አበልት” የተሰኘች ሴት ልጅ ያፈሩት የቀድሞው የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በህክምና ላይ በነበሩበት ጀርመን ሀገር ቅዳሜ ሚያዚያ 19ቀን 2011 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል:: የግዮን መጽሔት ዝግጅት ክፍልም ለቤተሰቦቻቸው፣ለወዳጅ ዘመዶቻቸውና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ መጽናናትን ይመኛል::

### የኢትዮጵያ ሙስሊም፣-

# ከአወሊያ እስከ ሼራተን ከ2003-2011



ሁሴን ከድር



ረቡዕ ሚያዝያ 23/2011 ለኢትዮጵያ ሙስሊም ታሪካዊ ቀን ነበር፡፡ የሰባት ዓመት ውጥረት የረገበበት፣ብዙዎች የሞቱበት፣የቆሰሉለት፣የተገረፉበት ለዓመታት የታሰሩለት ጥያቄ የተፈታበት ቀን ነበር፡፡ በ2003 በአወሊያ የተጀመረው የሙስሊሙ በመጅሊስ ላይ ተቃውሞ እነሆ ረቡዕ ሚያዝያ 23 በድንቅ ሁኔታ ተጠናቋል፡፡ ለመሆኑ ታሪኩ ምን ይመስል ነበር? በወፍ በረር ቅኝት ከ2003 ጀምሮ ያለውን የኢትዮጵያ ሙስሊምንና የመጅሊስን እንዲሁም ከመንግሥት ጋር የነበረውን ፍጥጫ ለመዳሰስ እሞክራለሁ፡፡

## የመጅሊስ አጥር ንቅነቃ ጅማሮ

በኅዳር 20ቀን 2003 በጉራጌ ዞን ሙሕርና አክሊል ወረዳ ደድ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ሰባት መስጅዶች ተቃጠሉ፡፡ ሙስሊሙ ጮኸ፣ ጩኸቱ ግን ሰሚ አጣ፡፡ ከጥቂት ቀናት በኋላም በአዲስ አበባ ጀርመን መስጅድ ወይም ተባረክ መስጅድ የኢማሙ ቤትና የሴቶች መስገጃ ክፍል ተቃጠለ፡፡ ይህም ሆኖ በሙስናና ብልሹ አሰራር የሚብጠለጠለው የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ድምጹን ለማሰማት 22ቀን ድረስ ፈጀበት፡፡ ሙስሊሙ በተቋሙ ላይ የሚያሰማው የማጉረምረም ድምጽ እየጎላ መጣ፡፡

በ2003 ለሐጅ ጉዞ ሳውዲ የሄዱ ምዕመናን በከፍተኛ ሁኔታ ተጉላሉ፡፡ የደረሰባቸውን በደል በመግለጽ በበይነ መረብ www.petitionbazz.com ላይ የፊርማ ማሰባሰብ በማድረግ ለወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ አቤት አሉ፡፡ በወቅቱ የነበሩ የእስልምና ጉዳይ አመራሮች ችሎታ፣ልምድ፣ ብቃት የሌላቸው በመሆናቸው ወርደው በአዲስ ይተኩ የሚለው ጉሩምሩምታ ብቅ ማለት ጀመረ፡፡ በወቅቱ ይታተም የነበረው ‹‹የሙስሊሞች ጉዳይ›› መጽሔትም ጥርሱን ነክሶ የመጅሊስን ጉድ ያዝረከርክ ገባ፡፡

ጅማ ከተማ ከመገባቱ በፊት በምትገኘው አሰንዳቦ ከተማ በፕሮቴስታንቶች ቸርች መጸዳጃ ቤት ቁርአን ተቀድዶ አግኝተናል ያሉ ሰዎች ከፍተኛ ቁጣ ውስጥ በመግባት ሁለት ቸርች አቃጥለው አንዱን አፈረሱ፡፡ የድርጊቱ ፈጻሚዎች ተይዘው ለ18ዓመታት በሚደርስ እስራት እንዲቀጡ ተፈረደባቸው፡፡ ሙስሊሙ በመጅሊሱ ላይ የበለጠ ተቃውሞውን አሰማ፡፡ ጥፋተኛ በተባሉት ልጆች ላይ የተላለፈው ፍርድ አግባብ አይደለም፣የሚከራከርለት ተቋም የሌለው ሙስሊም ሁሌም እንደተበደለ ነው በሚል ተቆጣ፡፡

በመጋቢት 2003 የወቅቱ የመጅሊስ ሊቀመንበር ሸህ አህመዲን ጨሎ በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ሙስሊሙና መጅሊስ ለሁለት ቀናት የቆየ ውይይት አደረጉ፡፡ በመጀመርያው ቀን ውይይት አህመዲን ጀበል መጅሊሱን በከፍተኛ ሁኔታ ተቸው፡፡ የልማት ሥራው እዚህ ግባ የማይባል፣የኢትዮጵያ ሙስሊምን የናቀ እንደሆነ በሰነድ በማስደገፍ ጉዱን አዝረከረከው፡፡ ይህንን መቋቋም ያልቻለው መጅሊስና መንግሥት በማግስቱ ሴራ ጎንጉኖ መጣ፡፡ ‹‹በኢትዮጵያ ወሃቢያ፣ሽዋሪጅ፣ጀመዓተ ተክፊር፣ፊርቀቱናጂያ፣አልኢቲሃዲያ እየተስፋፉ ነው›› የሚል አጀንዳ ተቀርጾ ቀረበ፡፡ ‹‹እነዚህ ተቋማት በጥቅል አልቃኢዳ ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ›› በሚል የማሸማቀቂያ ወጥመድ ተዘጋጅቶ ቀረበ፡፡

## የአወሊያ ንቅናቄ

የዓለም አቀፉ ኢስላማዊ የእርዳታ ድርጅት ሃያተል ኢጋሳ ያስተዳድረው የነበረው አወሊያ የሙስሊም ሚሲዮን ት/ቤት የድርጅቱን ፈቃድ መንግስት በመሰረዙ በአሁኑ ም/ጠ/ሚኒስትር በወቅቱ ትምህርት ሚኒስትር ለአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ በተጻፈ ደብዳቤ የአወሊያ ጉዳይ ክትትል እንዲደረግበት ታዘዘ፡፡ ትምህርት ቤቱን የሚያስተዳድረው አካል ሲታሰስ እጣው መጅሊስ ላይ ጣለው፡፡ የአወሊያ መከራ አደገ፡፡ የመጅሊስ ፈተና ተመነደገ፡፡ ሦስቱ ጥያቄም እያደር ተወለደ፡፡ መጅሊስ ትምህርት ቤቱን እንደተረከበ የማፈራረስ ሥራውን ጀመረ፡፡ 50 የኮሌጁ መምህራንን አባረረ፣የኮሌጁ ተመራቂ ተማሪዎች በዚያን ዓመት እንደማይመረቁ ተነገራቸው፣የመስጅዱ ኢማም ተባረሩ፣የወቅቱ ሌሎች ተማሪዎችም በአስተምህሮቱ ላይ ክለሳ ስለሚደረግ ተብሎ እረፍት ተሰጣቸው፡፡ ተማሪዎቹ እጅግ ተበሳጩ፡፡ በመጅሊሱ መደፈራቸው፣መሳቂያ መሳለቂያ በመደረጋቸው ተቆጡ፡፡ በሰፊው ተመካክረውም የ2003 ረመዳን ከመግባቱ በፊት በነበረ ጁምዓ ሕዝበ ሙስሊሙን በሥልክና በተለያየ መንገድ በመጥራት እያለቀሱ የደረሰባቸውን በደል ለሕዝብ ነገሩ፡፡

ሕዝብ ጉዳዩን ከዳር የሚያደርሱለትን 17 አባላት ያሉት ኮሚቴዎች መረጠ፡፡ ለ17ቱ ኮሚቴዎችም ከ500ሺ በላይ የሆኑ ሙስሊሞች ከመላው ሀገሪቱ የፊርማ ድጋፍ ተደረገላቸው፡፡ በዚህም በሙስሊሙ ላይ በመንግሥትና በመጅሊስ በኩል እየተደረጉ ያሉ ጫናዎች ነጥረው እንዲወጡ ተደረገ፡፡ በመጨረሻም ለሦስት ጥያቄዎች ወደ መታገሉ አመራ፡፡ አወሊያ በገለልተኛ ወገን ይመራ፣መጅሊስ ወርዶ በሕዝብ የተመረጠ መጅሊስ ሙስሊሙን ይምራ፣የአህባሽ አስተምህሮ ይቁም የሚሉ ነበሩ፡፡ ጎልቶ የወጣው መንግሥት በሃይማኖታችን ጣልቃ እየገባ ነውና ይውጣ የሚል ነበር፡፡ መንግሥት አልገባሁም ብሎ ድርቅ አለ፡፡

## ‹‹አዲስ ሰላምን የሚያሰፍን እስልምና››

የኢትዮጵያ ሙስሊም በወቅቱ ይወጡ በነበሩ ▶







የሙስሊሙ ጋዜጣና መጽሔቶች አማካይነት ግንዛቤው እንዲዳብር አመለካከቱ እንዲሰፋ ተደረጎ ነበር። በየቦታው በሙስሊሙ ላይ የሚደረጉት ትንኮሳዎች በመንግሥት ረጅም እጅ ሆን ተብሎ ታቅዶ የሚሰራበት መሆኑን ማስረጃዎች እየተጠቀሱ ይጻፉ ጀመር። የመንግሥት ሹማምንት አንዳንዴም ሳት እያላቸው ሌላ ጊዜም ጥቂት በጥቂቱ የማሳወቅ ስትራቴጂን በመንደፍ የአደባባይ ድፍረታቸውን ማሳየት ጀመሩ። የጉዳዩ አስፈጻሚ የሆኑት የወቅቱ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ዶ/ር ሽፈራው ተክለማርያም የምላስ ወለምታ ያጋጥማቸው ጀመር።

‹‹ዋናው የትምህርቱን አስተምህሮ በተለያዩ ትርጉሞችና ፍቺዎች በመቀያየር በዓለም ሰላም እንዲሰፍን የሚደረገውን በማስቆም፣ በእውቀትና በክህሎት ለመመካት፣ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ሼህ አብደላ አልሐረሪ የሐገራችን ልጅ መሆናቸው አንድ ነገር ሆኖ፤ ከእኛ ይልቅ ለሌላው የዓለም ክፍል ያበረከቱት ድርሻ የበለጠ ስለነበር ይህንንም አስተምህሮ በሀገራችንም ጭምር በምን ዓይነት መንገድ ለማራመድ እንችላለን በሚል የተለያዩ ውይይቶች ሲደረጉ ቆይቷል።››

ይህን ከላይ ያለውን ጥቅስ የተናገሩት የአህባሽ አጥማቂውንና የአብደላ አልሐረሪ ተማሪ የነበረውን ዶክተር ሰሚር ካዲን ከሊባኖስ አስመጥተው በሐምሌ 20/2003 አቀባበል ያደረጉለት ዶክተር ሽፈራው ተ/ማርያም ነበሩ። ይህ ንግግራቸው በወቅቱ መንግሥት በሃይማኖት ጣልቃ አልገባሁም፣ የሕገ መንግሥቱንም አንቀጽ 27(1) አልጣስኩም እያለ ቢከራከርም፤ በባለሥልጣኑ አንደበት ግን መግባቱን ‹‹ገብቻለሁ ምን ታመጣላችሁ›› ዓይነት ንግግሩ አሳወቀ። ዶ/ር ሰሚር የአህባሽ አስተምህሮን በተመረጠለት የሀገሪቱ ክፍል እየተዘዋወረ ማስተማር ጀመረ። ሥልጠናው ለመጅሊስ አመራሮች፣ወደከፍተኛ ትምህርት ለሚገቡ ‹‹ሙስሊም›› ተማሪዎች፣ለመስጅድ ኢማሞችና መድረሳ ሼኮች እንዲሰጥ ነበር መንግሥት ያመቻቸው።

## የሙስሊም መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴዎች

በሕዝብ ሙስሊሙ የተመረጡት መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴዎች ሥራቸውን በከፍተኛ ትጋት ተያያዙት። ከወረዳ እስከ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ድረስ ደረጃ በደረጃ ጉዳዩን ይዘው ይንቀሳቀሱ ጀመር። የአካሄዳቸውን አደገኛነት የተረዳው መንግስት እነሱን ለማስቆም ጥረት ማድረግ ጀመረ። በመጅሊስም የይስሙላ ምርጫ አደረገ። ሆኖም በቀለላሉ ሊሳካ አልቻለም። ከአንድም ሁለት ጊዜ ከፌዴራል ጉዳዮች አመራር ጋር ውይይት ተደረገ። መንግሥት እየተከተለው ከነበረው አቋሙ ዝንፍ ማለት አልፈለገም። ኮሚቴዎቹም ዋጋ ሊያስከፍላቸው እንደሚችል እያወቁ ገፉበት። መንግሥት በዛተው መሠረተ ኮሚቴዎቹን በአሸባሪነት ከሰሳቸው። ኮሚቴዎቹ ከመታሰራቸው በፊት የራሳቸውን ሃሳብ የሚያስደምጡበት ሚዲያም ከፈቱ ‹‹ድምጻችን ይሰማ›› የፌስ ቡክ ገጽ።

ድምጻችን ይሰማ ኮሚቴዎቹ ከታሰሩ በኋላ ሕዝቡን የሚያንቀሳቅስ ሥውር እጅ ሆነ። እስከዛሬ ድረስም የድምጻችን ይሰማ አመራር ማን እንደሆነ አይታወቅም። ሙስሊሙ ኅብረተሰብ በድምጻችን ይሰማ ሥር በመሆን በየጊዜው ሰላማዊ ተቃውሞውን በመንግሥት ላይ ማቀጣጠል ጀመረ። ለስድስት ዓመታትም ይህ ሁኔታ በተለያየ ስልት ቀጠለ።

አቶ መለስ ሞቱ። አቶ ኃይለማርያም ተተኩ። በእሳቸው የሥልጣን ዘመን የአስራ ሰባቱ ኮሚቴዎች አመራር ተራ በተራ ይፈቱ ጀመር። የዶ/አብይ መንግሥት መጣ ትናንት በአሸባሪነት የተከሰሱ ዛሬ ከነሱም በላይ ሰላማዊ ሰው ላሳር ተብለው ተንቆለጳጰሱ። የሰላም አምባሳደር የእርቅ ኮሚሽን የተለያየ ስያሜ የተሰጠው የመንግሥት የሥራ እቅድ ውስጥ እንዲገቡ ተደረገ። ተሰሚነታቸው ኀላ ተጽእኖ መፍጠርም ጀመሩ።

## የተቋማዊ ለውጥ የጋራ ኮሚቴ ጥረት

ዶ/ር ዐቢይ ሥልጣን በያዙ በሦስተኛው ወር በሰኔ 26 ቀን 2010 ‹‹የኢትዮጵያ ሙስሊም መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴንና›› ሰፊው ሙስሊም ከ2003 ጀምሮ ሲከሳቸው፣ሲያስደበድቡት የነበሩት ‹‹የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች›› አመራሮችን በተናጠል አነጋገሩ።

በቀጣይ ጊዜም የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን ችግር ሊፈታ ይችላል የሚል መፍትሔ በማቀድ ከሁለቱ ‹ሕጋዊ› አካላት ሦስት ሦስት አባላትና ሌሎች ገለልተኛ ከተባሉ አካላት ሦስት አባላትን በመጨመር ዘጠኝ አባላት ያሉት ‹‹የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ተቋማዊ ለውጥ የጋራ ኮሚቴ›› በማዋቀር ችግሩንና መፍትሔውን አጥንቶ እንዲያቀርብላቸው ትዕዛዝ ሰጡ። ኮሚቴው ለስድስት ወራት የኢትዮጵያ ሙስሊም ተቋማዊ ችግርን ከሥር መሠረቱ፣በማጥናት የመፍትሔ አቅጣጫውን ከሕግ አንጻር ሊኖር የሚገባውን ቁመና፣ ከሃይማኖታዊ ቀኖና፣ከአስተዳደራዊ መዋቅር….. በአጠቃላይ ከሁሉም አንጻር ሥራውን ሠርቶ በተባለበት ጊዜ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አቀረበ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተሠራውን ሥራ አድንቀው በቀረበው ሰነድ ላይ ሙስሊሙ እንዲወያይበት ከሁሉም ክልሎች ሰዎች በሰነዱ ላይ እንዲነጋገሩ 300 አባላት እንዲመክሩበት ጉባኤ እንዲጠራ አዘዙ። ለመጋቢት 27 ቀን 2011 ተጠርቶ የነበረው ጉባኤ ከዚህ ቀደም በዚሁ መጽሔት በጠቀስነው ሰበበ-ምክንያት ሳይከናወን ቀረ። ሆኖም ሚያዝያ 23ቀን 20011 በሼራተን አዲስ በተደረገ ታላቅ ጉባኤ ከከፍተኛ ሙግትና ፍትጊያ በኋላ የመጅሊስ አመራሮች ወርደው ጊዜያዊ አመራር እንዲመረጥ ተደረገ።

የስምንት ዓመታት ፍትጊያና ድሉ

ባለፉት ስምንት ዓመታት ሙስሊሙ ማኅበረሰብ ሲጠይቀው የነበረው ሕጋዊ ተቋም ምን ዓይነት ይዘትና ቅርጽ ይኑረው በሚለው ርእስ ላይ ሲመክር የነበረው የተቋማዊ ለውጡ የጋራ ኮሚቴ ሥራውን ሠርቶ ካጠናቀቀ በኋላ ጥቃቅን መሰናክሎች ገጥመውት ነበር። በአንድ ወገን የአገራችን ሙስሊም ከጥንት ጀምሮ ሲኀዝበት የነበረው የ‹‹ሱፍይ›› እስልምና አካሄድ ነው መርሃችን በሚልና የለም በሱናና የነብዩ አካሄድ በሆነው መንገድ ነው የምንኀዘው የሚለው የምሁራን ንትርክ ምንም የማያውቀውን ሰፊው ሕዝብ ጎራ ለይቶ እንዲኮራረፍ አድርጎት ነበር። ሆኖም በምሁራን መካከል የሚደረግ የሃሳብ ሙግት ምሁራን በተስማሙበት መንገድ መቋጨቱ አይቀርምና ሐጂ ዑመር ኢድሪስ በአመቻቹት መንገድ ጉዳዮች እልባት እንዲያገኙ ሆኗል።

የብዙዎች የዓመታት ሕልም እውን ሆኖ በርካቶችን በደስታ እምባ ያረጨ ኅብረት ተፈጥሯል። በአስተሳሰብ ተራርቀው ይኀሻሸሙ፣ ክፉኛ ይተቻቹ የነበሩ ወጣት ምሁራንም በይቅርታ በአደባባይ ታርቀዋል፤ ተቃቅፈው ተሳስመዋል። የሚዲያ ጦርነቱም በሰላማዊ ወሬ ተተክቷል። የሰላም ሚኒስትሯ እምባና መሪር ተግሳጽ ባቡሩ ከሳተው ሐዲድ እንዲመለስ አድርጎታል። ሙፍቲ ሐጂ ዑመርን ጨምሮ 26 ከመላው ሀገሪቱ የተውጣጡ ጊዜያዊ የአሊሞች ምክር ቤት /የልሂቃን ምክር ቤት/ ተቋቋሟል። መጅሊሥ ሥልጣኑን ለእነዚህ ልሂቃን ያስረክባል። ሰባት ጊዜያዊ የቦርድ አባላትም ተሰይመዋል። እነዚህ 33 ተመራጮች የወደፊቱን መጅሊስ የሚመሰርቱ ናቸው።


በወረቀት ላይ የስምምነት ሰነድ ይደረግ እንጂ ወደ ተግባር ሲመጣ ምን ሊያጋጥም እንደሚችል ገና አልታወቀም። በግድ ተገፍቶ ሥልጣኑን የለቀቀው የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች አመራር እስከዛሬ ለወደመው በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብና የሰፊው ሙስሊም ንብረት ተጠያቂ ይደረግ ይሆን? በዘመድ አዝማድ የተሳሰረው በመላው ሀገሪቱ ከሁለት ሺህ በላይ ሠራተኞች ያስተዳድር የነበረው መጅሊስ ፍጹም ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሥልጣኑን ያስረክባል? አዲሱ መጅሊስ በየጊዜው እየጨመረ የሚመጣውን የሃጅ ተኀዥ ፍላጎት በምን አቅም ይሆን የሚያስተናግደው? ሙስሊሙ እሮሮ የሚያሰማበት የሃጅ ጉዞ ከዚህ በኋላ በሥርዓቱ ይስተናገድ ይሆን?

በሂደት የሚመጡ በርካታ ጥያቄዎች የሚፈቱት በዚያው ሂደት ነው። እኛም ‹‹በትሻልና ትብስ›› መካከል ያለውን ልዩነት ወይም ደግሞ በ‹‹ትብስና ትሻል›› መካከል የምናየውን ለውጥ በየጊዜው እየተከታተልን እንዘግባለን።

ቸር እንሰንብት

መልካም የረመዳን ዋዜማ።

# “የይሁዳ ሠላምታ” በዘመኑ ፖለቲከኞቻችን ላይ!



ደረጄ ዘውዴ

ከሁሉ አስቀድሜ ለመላው ክርስቲያኖች እንኳን ለብርሐነ ትንሳዔ አደሰረሳችሁ፡፡ ለሙስሊም ወንድሞቻችን እህቶቻችን እንኳን ለፆም ረመዳን አደረሳችሁ ለኢዱም በሰላም ያድርሳችሁ እያልኩኝ እንደ ስሙ አብይ የሆነ የመጨረሻው የአብይ ጾም ሣምንት ሠሞነ ህማማት በመባል የሚታወቅ ሲሆን ከሰኞ እስከ አርብ ባሉት ቀናት መጨባበጥና መሣሣም በኦርቶዶክስ እማኞች ዘንድ ይከለከላል፡፤ምክንያቱም የይሁዳን ሠላምታ ለመኮነን ሲባል የተደረገ ነው፡ ይሁዳ ከጌታ ተማሪዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን በመጨረሻ ጌታውን በ30 ብር አሳልፎ የሠጠ ከሠቃዮቹ ጋር በስውር የተስማማ በመጨረሻም አሳልፎ ለመስጠት የተጠቀመበት መንገድ አቅፎ በመሳም ስለነበር ይህንን ጌታውን አቅፎ እየሳሙ አሳልፎ መስጠትና መጉዳት ለማሰብ ሣምንቱ ተጨባብጦ ተቃቅፎ ሠላምታ ባለመለዋወጥ እንዲታሰብ አባቶቻችን ስርአት አበጅተው እንጠቀምበታለን። በሃገራችን እጅግ የሚያስደንቁ ሀይማኖታዊና ባህላዊ ሀብቶች ባለቤቶች ብንሆንም በተጻናወተን የራሳችንን የመጣል አባዜ ብዙ ሃብቶቻችን ከእጃችን እየጠፉ ይገኛሉ። ዛሬ በሃገራችን ይሁዳ ያስተማረው ትምህርት በሰፊው እየተተገበረ ይገኛል።

ሠላም ላንተ ይሁን እያሉ ሠላም መንሳት ጉንጭእየሳሙ መግደል ሠላም ሠላም በቃል እያሉ በተግባር ተቃራኒ ሆኖ መገኘት በሃገራችን ሠፍኗል። ይሁዳ በቅዱስ መጽሀፍ እንደተጻፈ ይህንን ክፉ ድርጊት የፈጸመው ቀድሞም በውስጡ የነዋይ ፍቅር የነበረውና ምኞቱና ሀሳቡ የተከፈለና በእኔነት የተሞላ ስለነበር ሰይጣን ምኞተንና ሀሳቡን ተከትሎ ወደ ይሁዳ ስለገባበት ተለከፈ በወንጌሉ እንደተጻፈው ሰይጣን በአስቆሮቱ ይሁዳ ገባበት ብሎ ይነግረናል። ከዚያ በኋላ የሰይጣን ጉዳይ አስፈፃሚ ሆነ። ዛሬም ወደ ሀገራችን ስትመጣ ይህ መበላላትና ትርምስ ጥላቻና ቂም በቀል ሞትንና ጥፋትን ከመመኘት አባዜ ውስጥ አላስወጣም ብሎ የመከራ ዝናብ ውስጥ እንድንኖር ያደረገን ልክፍት ካልሆነ ምን ልንለው እንችላለን? ሠይጣን መንፈስ ነው እርኩስ መንፈስ በሠዎች ውስጥ አድሮ ሁለመናቸውን ተቆጣጥሮ የጥፋት ሥራውን ያስፈጽማል።

በዚች ሀገር የምንኖር ህዝቦች የሁሉም ፍላጎት በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው እድገት ሰላም ብልጽግና ወዘተ እነዚህ የሀገራችን ህዝብ ፍላጎት ለማሳካት በተፈጥሮ የታደልናቸው ጸጋዎች በበቂ ሁኔታ አሉን ሠፊ የተፈጥሮ ሃብት መሬት የሠው ሃብት በእያንዳንዱ ህዝብ ውስጥ የራሱ የሥራ ባህል የሽምግልና ባህል የግጭት አፈታት ባህል ወዘተ አሉን እነዚህን ደምረን የህዝባችንና የሀገራችንን እድገት በአጭር ጊዜ ማምጣት ይቻላል ነገር ግን ህዝቡ ሠላም ወዳድና የቆየ የአብሮነትና የመልካም እሴቶች ባለቤት በመሆኑ እንጂ የፖለቲካ መሪዎችና ምሁራን ተብዬዎች የህዝባችንና የሀገራችንን ሠላምና እድገት የማይወዱ ሀይሎች እየሠሩ ያሉት በተቃራኒው ነው::

የፖለቲካ መሪዎቻችንና ሁሉም ዘመነኛ ተዋናዮች ላይ ይሁዳ ውስጥ የገባው ሠይጣን ገብቶባቸዋል::ስለሆነም በየስብሰባውና በየአደባባዩ የይሁዳን ሠላምታ ይለዋወጣሉ::ሃገራቸውንና ህዝባቸውን ለርካሽ ጥቅም አሳልፈው ይሸጣሉ:: በህዝብ ደም፣ በህዝብ ስቃይ በሀገር ውድቀት ይደሰታሉ፡፤ የተለከፈ ሰው ብዙ መገለጫዎች አሉት ራሱ ተረብሾ ሌሎችን ያውካል:: ለፍላፊና ቀባጣሪም ይሆናል:: የተለከፈ ሰው ሁሉንም ነገር ይደበላልቃል::ምንም የተጨበጠ ነገር የለውም፤ የተለከፈ ሁል ጊዜ ጉልበትና አመጽን፣ ማስጨነቅን፣ መተረማመስን ስራው ያደርጋል:: በክፉ መንፈስ የተያዘ ሰው የመጀመሪያ መገለጫው አንደበቱ ነው:: ስለአንደበት መፅሐፍ ቅዱስ ሲናገር “አንደበት እሳት ነው” ይለናል “ከአንድ ምንጭ መራራና ጣፋጭ ውሃ ሊወጣ አይችልም” ይላል::


የሚነድ እሳት በጣም ጠቃሚና ለሰው ልጆች እጅግ አስፈላጊ ኃይል ነው:: የአስፈላጊነቱ ያህል ጥንቃቄውም የዛኑ ያህል ነው:: የጥንቃቄ ጉድለት ከቁጥጥራችን ከወጣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳል:: ለዚህ ነው አንደበታችን ከእሳት ጋር የእግዚአብሄር ቃል ያነፃፀረው የሚነድ እሳት በውሃ እና በአፈር ይጠፋል:: በአንደበት የተጫረ እሳት አንዳንዱ በቀላሉ ማጥፋት አይቻልም:: ለልጅ ልጅ ይተላለፋል:: ዛሬ ሀገራችን ያጋጠማት ምስቅልቅል እንዳንረጋጋና ወደ ፊት እንዳናይ እያደረገን ያለው ዋናው በሽታ የፖለቲካ መሪዎች፣ ምሁራንና አክቲቪስቶች ኃላፊነት በጎደለው ሁኔታ የሚናገሩት ጠቃሚ ያልሆነ የንግግር እሳት በየአካባቢው ግጭት ይለኩሳል:: ባቀጣጠሉት እሳት እኛ ስንለበለብ፣ እነሱ ዕሩቅ ሆነው ይሞቃሉ:: ሪፖርት እያቀረቡ ትርፍና ኪሳራቸውን ያወራርዳሉ::

ከነበርንበት የሞራል ልዕልና የወረድንበት አንድ ደረጃ የአንደበታችን አጠቃቀም ነው:: አንደበታችን የተፈጠረው ለምስጋና፣ ለፍቅር፣ ሰላምን ለማወጅ፣ ለመግባባት፣ በጎውን ለመነጋገር የተሰጠን ፀጋ ሲሆን፤ ዛሬ ለውጠነው ለእርግማን፣ ለምሬት፣ ለወቀሳ፣ ለማለያየት እንድንጠቀምበት ፈቅደናል:: አንደበት የተፈጠረበት ዓላማ ይህ አይደለም:: አንድን ነገር ላልተፈጠረበት ጉዳይ መጠቀም ጉዳት አለው:: ለሰው ልጅ በሁሉ ተግባሮች ውስጥ መልካም ንግግር ማስቀደም ተገቢና ጠቃሚ ነው:: በቤተሰብ ውስጥ የምሬት እና ክፉ ንግግሮች ተገቢ አይደሉምና ውጤታማ አያደርግም:: ዛሬ በየሚዲያውና በየስብሰባው የሚነገሩ ክፉ ዘሮች ውጤቱን በየዕለቱ እያየነው፣ እየኖርነው እንገኛለን:: ተቀባይነት አገኘን ተብሎ በኩሽናችን ውስጥ የምናነደውን እሳት የምንጠነቀቅለትን ያህል፤ ላመነንና ለተቀበለን ህዝብ ጥንቃቄ ሳናደርግ የምጭረው የአንደበት እሳት ስንቱን እያቃጠለ እንደሆነ እያየን ነው:: ብዙ ፕሮፌሰሮች አዳዲስ ነገሮች ለአለም ሲያበረክቱ አይቻለሁ:: ዘንድሮ ግን በዚህ ማዕረግ የሚጠሩ ሰዎች እታች ወርደው ለዘመናት ህዝቦች የገነቡትን ሕይወት ለማፈራረስ ሲሰሩ ሳይ በጣም አፈርኩኝ::

አብዛኛዎቹ አውሮፓና አሜሪካ የኖሩ፣ የሚኖሩ መሆናቸው ያስገርማል:: እውነት ህዝብን ሲያቃቅሩና ሲያለያዩ ጠፍቷቸው ነው ወይስ ተልዕኳቸው ነው? የሆነው ሆኖ የቱንም ያህል ህዝባችንን ቢጎዱትም፣ ቢያደናብሩትም ከእነሱ በተሻለ ስብዕና የተገነባ መሰረት ስላለው የሰበኩትን ያህል አልተሳካላቸውም፤ ለወደፊትም አይሳካላቸውም:: በዚህ ክፉ መንፈስ የተያዘ ሰው ለመዳን መፍትሄው የያዘውን ክፉ መንፈስ ከውስጡ እንዲወጣ ማድረግ ነው:: በክፉ መንፈስ የተያዘን ስብሰባና ውይይት ምክክር ሊያድነው አይችልም:: የክፉ መንፈስ ተልዕኮ የሰው ልጆች ደስታን ማበላሸት፣ ኑሯቸውን ማጎሳቆል፣ አስተሳሰባችንና አመለካከታችንን ማዛባት ነው:: እነዚህ መሪዎች ነን የሚሉ ሰዎች ተለክፈው ካልሆነ ጤነኛ ናቸው ለማለት እንዴት ይቻላል? ስለሆነም ሞኝነት ቢመስልም እናንተ ልሂቃን የፖለቲካ መሪዎች፣ አክትቪስቶች እንደየእምነታችሁ ጊዜ ወስዳችሁ የምትጠመቁ ተጠመቁ:: የምታፀልዩ ይፀለይላችሁ:: ዱአ የምታደርጉ ዱአ ይደረግላችሁ:: ውስጣችሁ የገባውን መንፈስ አባሩት፤ አስወጡት:: የጋረዳችሁን ጨለማ ግለጡ፤ ለሠራችሁት ጥፋት ንስሀ ግቡ:: ለይሁዳ የንስሀ እድል ተሰጥቶት ሊጠቀምበት ስላልቻለ መጨረሻው ጥፋት ሆኗል::

የውርደት መንፈስ ሰባኪዎች፣ የይሁዳ ደቀ መዛሙርት ሆይ ለ30 ብር ህዝብንና አገር ለመሸጥ ቢሞክሩ ይብላኝ ለራሳቸው:: “ቀብረናል፣ አፍርሰናል፣ አበቃላት” ብለው በየበራፋችን ጠባቂ ዘበኛ፣ የቂምና የበቀል ሀውልት ቢያቆሙም፤ ክርስቶስ መቃብሩን ፈንቅሎ እንደተነሳ ሁሉ፤ በትንሳኤው “ሰላም ለእናንተ ይሁን” ብሎ ብርሐንን እንደገለጠ፤ የኢትዮጵያ ትንሳኤም እውን ይሆናል:: ፈጣሪ የብዙ ቅዱሳን፣ የየዋሁን ህዝብ እንባና ፀሎት ችላ አይልምና:: አምላክ የገባውን ቃል የሚጠብቅ ኃያልና ርህሩህ ነውና:: ሀገራችን በብዙ ነብያት የተመረቀች አገር ናት:: የኢትዮጵያ ትንሳኤ በጸሐፍት ፈሪሳውያን እና በይሁዳ ሴራ ቢሰራባትም ትንሳኤዋ ሊዘገይ አይችልም:: ስለሆነም ሁላችንም የአገራችን ህዝቦች ተስፋችንን አንጣል፤ ታላቅ ህዝቦች መሆናችንን አንዘንጋ:: ለአለም ብዙ ነገር ያበረከቱ አባቶች፣ ልጆች መሆናችን አንዘንጋ:: እራሳችንን ሊያሳንሱን በሚፈልጉ ትንንሽ ልክ እራሳችን ዝቅ አናድርግ:: ከምንግዜውም በላይ ያሉንን ሀገራዊ ትውፊቶች፣ ሐይማኖታዊና ባህላዊ እሴቶቻችንን ጠብቀን ሌላ ታሪክ ለመስራት እንነሳ::

# ኢትዮጵያውያን ማሰብ አይችሉም?!



መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

ሚያዚያ 9 ቀን 2011 በወጣው ሪፖርተር ጋዜጣ ለይ አቶ ልዑል አልጀበል የተባሉ ፀሐፊ በሶስት የውጭ አገር ዜጎች ስለ ኢትዮጵያ የተሰጠ አስተያየት ብለው ሠፋ ያለ ዘገባ አቅርበው ነበር፤ እነዚህ የውጭ ዜጎች የጃፓን፣ የናይጄሪያና የኬንያ ዜጎች ሲሆኑ "ኢትዮጵያውያን ማሰብ አይችሉም" በሚል ርዕስ ሰፊ ትችት እንደዘገቡ ነግረውን ነበር፡፡ ነገር ግን ፀሐፊው እነዚህ ሰዎች ከርዕሱ በታች ምን ዓይነት ምክንያት እንዳቀረቡና የሰጡትን ዝርዝር አባባል በጋዜጣው ላይ ሊያሳዩን አልቻሉም፡፡

ይህንን አስተያየት የሰሙ በርካታ ኢትዮጵያውያን እንዴት እንዲህ እንባላለን? በሚል ስሜት የተናገሩትን የቁጭት አስተያየቶችን በስፋት አስነብበውናል፤ በእኔ እምነት ኢትዮጵያውያን በቁጭት በርካታ አስተያየት መስጠታቸው በእጅጉ ተገቢ ሲሆን፤ እነዚህ ሶስት የውጭ ዜጎች "ኢትዮጵያውያን ማሰብ አይችሉም" ብለው መናገራቸው በራሱ በእጅጉ የተሳሳተ ትችት ነው፡፡ ሕዝቦች ደግሞ የሚያሳዩትን እድገትም ሆነ ሥልጣኔ በዋናነት በሚያገኙት አመራር ብቻ የሚወሰን በመሆኑ፤ እነዚህ አስተያየት ሰጪዎች በእጅጉ ለመሳሳታቸው ብዙ መመራመር አያስፈልግም፡፡

እኔ ባሳለፍኩት የስራና የትምህርት ዘመን፣ የአለምን ግማሽ ለማየት ዕድል አጋጥሞኛል፡፡ በዚህ ጊዜ የታዘብኩት ነገር ቢኖር ሕዝቦች ከተፈጥሮ ጋር ግብግብ ገጥመው. ከፍተኛ ሀብት አፍርተው፣ ለተተኪው ትውልድ እያወረሱ እጅግ የተደላደለ ኑሮ መኖር እንደቻሉ ሲሆን፤ ለምሣሌ እስራኤል ከተመሰረተች 1947 እ.ኤ.አ ጀምሮ፤ በዚህች አጭር ጊዜ በዚያ በረሃ ውስጥ ምን ዓይነት ልማት እንዳመጡ ስንመለከት፣ ምናልባት እነዚያ ሰዎች ከኛ የተለየ የማሰብ ችሎታ አላቸው ብለን ልንደመድም እንችላለን፡፡ እጅግ አስቸጋሪ የተፈጥሮ ሁኔታ ባለባቸው አገሮች ማለት ጃፓን፣ ኮሪያ፣ እስራኤል፣ ጀርመን፣ ራሺያ የመሳሰሉ አገሮች ሰዎች ተፈጥሮ ያመጣውን ሁኔታ ተቋቁመው ሕይወታቸውን ለመምራት ምናልባት ከኛ በላይ አእምሮአቸውን ተጠቅመውበታል ብንል ስህተት አይመስለኝም፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን ከድርቅ በስተቀር እንደ መሬት መንቀጥቀጥ፤ ከፍተኛ የሆነ ሙቀትና ቅዝቃዜ፤ ሔሪከን (ሳይክሎን) የመሣሠሉ ከፍተኛ አውዳሚ ክስተቶችን በአገራችን ስለማናስተናግድ በእውነቱ የተዘናጋን ነን ቢባል ስህተት አይመስለኝም፡፡ የተዘናጋን በመሆናችን ደግሞ ብዙ የተፈጥሮ ሐብቶችን በአካባቢያችን መጠቀም እየቻልን፣ በተለያዩ ምክንያቶች ማለት በሐይማኖታዊ፣ በባህላዊ ምክንያቶች እነዚህን የተፈጥሮ ሐብቶች መጠቀም አቅቶን ስንቸገር፣ ስንራብ የታዘቡ የውጭ ዜጎች "ኢትዮጵያውያን ማሰብ አይችሉም" ቢሉን ብዙም ሊደንቀን አይገባም፡፡ ለምሣሌ ጎጃም ውስጥ በርካታ ቦታ የአሣ ምርት ማምረት የሚቻል ሲሆን፣ የአገሬው ሰው በተለያዩ በሐይማኖታዊ ምክንያቶች "አልመገብም" በማለት ሲቸገር ይታያል፡፡ በመላው ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ እንደ አሳማ ያለ በቀላሉ የሚራባና በተወለደ በዘጠኝ ወሩ ለዕርድ የሚደርስ እንስሳ አርብተን መመገብ ገና አልጀመርንም፡፡

ከላይ የጠቀስኳቸው ፀሐፊ ይህንን አባባል የሰሙ ኢትዮጵያውያን በእጅጉ በመቆጨት በርካታ አስተያየቶችን እንደሰነዘሩ ነግረውናል፡፡ ከነዚህም አስተያየቶች መሐል እኛ ኢትዮጵያውያን የበርካታ ታሪካዊ ቅርሶች ባለቤት እንደሆንና የነ አክሱምን፣ ላሊበላን ውቅር አብያተ ክርስትያናትን የገነባን ሕዝቦች እንደሆንን በርካቶች ለመግለፅ ሞክረዋል፡፡ ይህ በዕውነቱ በእጅጉ ትክክል ነው፤ ነገር ግን የአክሱምን ሐውልት የገነቡ እጆች፣ የላሊበላን ውቅር አብያተ ክርስቲያናት የቀረፁ እጆች፣ የፋሲልን ግንብ የገነቡ እጆች አሁን በሶ ጨብጠዋል ለማለት ድፍረቱ ባይኖረኝም፤ በአሁኑ ጊዜ እየሰራናቸው ያሉ ሥራዎች ግን ከአቅም በታች ናቸው ብሎ መናገር የሚቻል ይመስለኛል፡፡

እኛ የላሊበላን ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ስንገነባ በተቀራረበ ወቅት አሁን ሰሞኑን በእሳት የጋየው የፈረንሳይ ኖተርዳም ካቴድራል የተገነባበት ወቅት ነበር፤ ታዲያ ፈረንሳዮች ከዚያ በኋላ ባሉት 850 አመታት ምን ሰሩ? እኛስ? እንዲህ አይነት ጥያቄዎችን እያነሳን የሰለጠነ ውይይት ብናደርግ በእጅጉ ተገቢ ይመስለኛል፡፡በፅሁፌ መግቢያ ላይ እንዳልኩት በውጭ ዜጎች የተሰጠው አስተያየት ሊያበሳጨን ሳይሆን በእልህ ተነሳስተን ጠንክረን ለመሥራት እንደ ግብዓት ልንጠቀምበት ነው የሚገባው፡፡

ባለፉት መቶ አመታት አገሪቱ ወደ ውጭ የምትልከው ምርት ቡና ሲሆን፤ ይህን ምርት ማሳድግና በሌላ ምርት መተካትም በጭራሽ አልቻልንም፡፡ ቻይና የዛሬ መቶ አመት የምትታወቀው በሲልክ ምርት ነበር፤ በአሁኑ ወቅት ቻይና የማታመርተው ምንም ዓይነት ምርት የለም፤ ይህ ነው የኢኮኖሚ ዕድገት ማለት፡፡ ይህ ነው ትውልድን ተጠቃሚ ያደረገ የዕድገት መንገድ፡፡ እኛ ከሉሲ እስከ ኢህአዴግ ዘመን ተፈጥሮ ያበቀለውን ቡና ኤክስፖርት እያደረግን "ኢትዮጵያውያን ማሰብ አይችሉም" የሚለው ትችት ብዙም ሊያስደነግጠን አይገባም፡፡ ይልቁንም ወኔ ለመሰነቅ የሚረዳን ግብዓት ነው፡፡ መሪዎቻችንም እንዲህ አይነት ነገሮችን ሲሰሙ ከማንም በላይ የቁጭት ስሜት ሊያድርባቸው ይገባል፡፡

አሜሪካኖችና ሩሲያዎች እርስ በርሳቸው በሳይንስ የበላይ ለመሆን በሚያደርጉት ፉክክር የአገራቸውን መሰረታዊ ፍላጎት ማሟላት በእጅጉ ቀላል ተግባር ነው የሚሆንላቸው፡፡ እኛ ከእነሱ ጋር እንፎካከር ማለቴ ሳይሆን ከእነሱ ትምህርት ወስደን ቁንፅል ለሆነ አላማ መሮጣችንን ትተን ለግዙፍና ለትልልቅ ግቦች ከሰራን፣ ትንንሾቹ ችግሮች በማህበረሰብ ወይም በግለሰብ ደረጃ በቀላሉ ሊወገዱ ይችላሉ፡፡ ዛሬ በመላው አፍሪካ ውስጥ እያደገ ያለው አስተሳሰብ የብሔር ጥያቄ ሳይሆን እንዴት አድርገን ነው የአፍሪካን ኢኮኖሚ መገንባት ያለብን? እንዴት አድርገን ነው የአፍሪካን ኢኮኖሚ እርስ በርስ የምናስተሳስረው? እንዴት አድርገን ነው አንዳችን ካንዳችን ጋር ተደጋግፈን የምናድገው? ወዘተ የሚሉ ራዕይ ያነገቡ አላማዎችን ይዘን ነው መጓዝ ያለብን፡፡

በአሁኑ ዘመን ኮሚሽን አቋቁመን የብሔር ብሄረሰቦችን ድንበር ለመፈለግ ስንነሳ "ኢትዮጵያውያን ማሰብ አይችሉም" ብንባል ብዙ የሚገርም አይደለም፤ ምክንያቱም በብሄረሰቦች መካከል ድንበር የለም፤ ከሌለ ደግሞ ማንም ፈልጎ አያገኘውም፡፡ ሌላው ሳያባራ እየተነሳ ያለው የክልል ይገባኛል ጥያቄ በአግባቡ ብናየው፤ ክልል የሆኑ ቦታዎች ኢንቨስተር እየራቃቸው፣ የታክስ ገንዘብና የስራ ዕድል ፈጠራ ማግኘት ባልተቻለበት ሁኔታ ክልል መሆን በራሱ ለድህነት እንደሚዳርግ በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም አዲስ አበባ ሕብረ ብሔራዊና ብሄር የለሽ መሆንዋ እንደ ሸንበቆ እንድታድግ እያስቻላት ባለበት ወቅት የክልል ጥያቄ መነሳቱ በራሱ በእጅጉ አስገራሚ ነው፡፡ በቱሪዝም ሐብት ከፍተኛ ገቢ ለማግኘት በዋናነት ከሚረዱ ሁኔታዎች አንዱ ከተለያየ ቋንቋ፣ ብሄር፣ የቀዳ ቀለም ወዘተ ካላቸው ሰዎች ጋር አብሮ የመኖርን ባህል በሠፊው ማዳበር ነው፡፡ ለምሣሌ ደቡብ አፍሪካ በርካታ ማህበረሰብ ዜጎች የሚኖሩባት አገር በመሆንዋ የመቻቻል ልምዱ በእጅጉ የዳበረና በአሁኑ ወቅት በአመት እስከ ሰላሳ አምስት ቢሊዮን ዶላር ከቱሪዝም ብቻ ታገኛለች፡፡ ይህ በአፍሪካ ቀዳሚው ሲሆን ደቡብ አፍሪካ ከኢትዮጵያ ያነሰ የቱሪስት መስህብ ያላት አገር ሆና ይህን ያህል ገንዘብ ማግኘት መቻልዋ በጣም የሚያስቆጭ ነው፡፡ ፡

በመጨረሻም አቶ ልዑል የሰጡትን አስተያየት በማድነቅ እኔም አቅም በፈቀደ መጠን የራሴን አስተያየት ለመጨመር ሞክሬአለሁ፡፡ እነዚህ ሶስት የውጭ ዜጎች የሰጡት አስተያየት አገራችን ያለችበትን ቦታ ሊጠቁመን የሚገባ ግብዓት እንጂ ተንኮል በማሰብ የሰጡት አስተያየት እንዳልሆነ ብንወስደውና በሌላ ጊዜ ከመሰል ትችቶች አምልጠን "ኢትዮጵያውያን ልዩ የአገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች ናቸው፤ ኢትዮጵያውያን የሚገርም ጭንቅላት ያላቸው ሕዝቦች ናቸው፤ ኢትዮጵያውያን ለሳይንስ፣ ለስልጣኔ፣ ለኢንቨስትመንት፣ ለቱሪዝም ወዘተ የሚመቹ ሕዝቦች ናቸው" የሚሉና ተመሣሣይ ትችቶችን ማስተናገድ እንድንችል ተግተን መስራቱ ተገቢ ነው የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

# የኢትዮጵያ ሚዲያ...

ከገጽ 8 የዞረ

ብሄር ላይ አድርጎ እስከሚሰራው ኦኤምኤን እና ድምጸ ወያኔ ድረስ በኢትዮጵያ የሚዲያ ኢንደስትሪ ሜዳ ውስጥ ለመጫወት መድረኩን ተቀላቅለዋል፡፡ በሃገር ውስጥም ኢቢኤስ ላይ ቁልፍ ሰርቶ ታግቶ የነበረው የግል ቴሌቪዥንና ራዲዮ ጣቢያ ፍቃድ መለቀቁ ብዙዎች ሞገድ እየገዙ አየር ላይ እንዲውሉ ምክንያት ሆኗል፡፡ ከዚህ ባሻገርም ከታገዱት ጋዜጦችና መጽሄቶች ወደህትመት መመለስ ጀምሮ በርካታ መጽሄቶች እና ጋዜጦች ለንባብ በቅተዋል፡፡ የሚዲያ ኢንደስትሪው ዳግም ከወደቀበት ስርቻ ብቅ ብሏል፡፡

እንዲህም ሆኖ የኢትዮጵያ ፕሬስ በነጻነት እየሰራ ነወይ? የሚለው ጥያቄ አሁንም በጥያቄ ምልክት ውስጥ ተቀምጧል፡፡ ብዙዎች ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ አሁን ቢያንስ ማዋከብ ማስፈራራት እና ማሰር ከሌለ፣ መገናኛ ብዙሃኑ ያሻቸውን ከሰሩ ነጻ ናቸው ሊባል የማይችልበት መንገድ የለም፡፡ ነገር ግን ይህ ስህተት ነው የሚሉ የፕሬስ ነጻነት ማጣት ማዋከብ አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን የሚያሰሩ መስመሮች መዘጋታቸው የሚያስከትለው ጦስ ውጤት ጭምር ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሚዲያ ከለውጡ አትራፊ ሆኗል የሚሉት "ከእገዳ መነሳት እና ቢያንስ በጸፉትና በተናገሩት ለመታሰር ካለው የፍርሃት ቆፈን ከመላቀቁ ጋር" አያይዘው የሚያዩ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ የመንግስት እና የፖለቲካ ድርጅቶች ሃላፊዎች ሚዲያውን ባገኙት መድረክ ሁሉ ሲወቅሱ መቆየታቸውም በተለይም የሚተቻቸው ሚዲያ ላይ ጥርስ የነከሱ መስለው መታየታቸው የቀደመው ልምድ ዳግም እየመጣ መሆኑን ማመልከቻ ነው ተብሏል፡፡ መጫወቻ ሜዳ ሰጥቶ ጨዋታውን ለመዳኘት መሞከር ዞሮ ዞሮ በእጅ አዙር ለመቆጣጠር ከመሞከር አይዘልም የሚሉት አስተያየት ሰጪዎች የዶክተር ዐቢይ አስተዳደር ፕሬስን የሚመለከትበት አይን አሁንም በጎ ነው ለማለት ያስቸግራል ነው የሚሉት፡፡

በአሁኑ ጊዜ ፕሬሱ ላይ የሚደርሰው ጫና የመንግስት ብቻ ሳይሆን በፖለቲካ ቡድኖችና ጽንፈኛ አስተሳሰብ በያዙ አካላትም በተመሳሳይ የሚታይ ዝንባሌ ነው፡፡ ፕሬስ ለአንድ አካል የማይወግን፣ ውግንናው እውነት ብቻ የሆነ እና ለህብረተሰብ እድገት እና መረጃ ፍሰት የሚሰራ እስከሆነ ድረስ ሊታመን ይገባው ይሆናል እንጂ መጠላት የለበትም፡፡ ይህ መሰረታዊ የሆነ የፕሬስ አላማ ግን በብዙዎች ዘንድ አልታወቀም፡፡

### የዓለም የፕሬስ ነጻነት ቀን በኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ከሞላ ጎደል ከላይ በነበረው መልክ ላይ እያለ ነው እንግዲህ የዓለም የፕሬስ ነጻነት ቀን በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት (UNESCO) ፣ እና በኢትዮጵያ መንግስት ትብብር በአዲስ አበባ ውስጥ የተከበረው፡፡ የዘንድሮው መሪ ቃል ሜዲያ ለዴሞክራሲ በመረጃ ብክለት ዘመን የምርጫ ዘገባ የሚል ነው፡፡ ሚዲያ ለዴሞክራሲ የሚለው ይህ ግዙፍ መርህ ተዘርዝሮ ሲታይ ያለፕሬስ ዴሞክራሲ እውን መሆን እንደማይችል ብቻ ሳይሆን የፕሬስ ነጻነት የዴሞክራሲ መስፈን አይነተኛ መገለጫ መሆኑን ማመላከቻም ጭምር ነው፡፡

የዓለም የፕሬስ ነጻነት ቀን በተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን እና በአፍሪካ ህብረት መሰብሰቢያ አዳራሾች ውስጥ ለሶስት ቀናት ሲካሄድ በዋናነት ከተነሱት አጀንዳዎች አንዱ የሚዲያ ሪፎርም ወይም ተሃድሶ ጉዳይ ነው፡፡ በተለይም የኢትዮጵያን ሚዲያ አፍኖ አላንቀሳቅስ ያለው ጸረሽብር ህግ፣ ጋዜጠኞች በጻፉት ብሎግ አንዲከሰሱና እንዲፈረድባቸው ያደረገው ህግ ፣ የኮምፒውተር ህግ እንዲሁም አሁን ይህን አድርግ ያንን አታድርግ እያለ መንግስት ጣልቃ እንዲገባ ምክንያት የሆነው የብሮድካስት ህግ፤ በተጨማሪም በተለያዩ ህጎች ውስጥ ተበትነው የሚገኙ ፕሬስ ተኮር ህጎች በራሳቸው ለፕሬስ ነጻነት አደጋ መሆናቸው ታይቶ ተሻሽለዋል፡፡ በቅርቡም ለህዝብ ውይይት የሚቀርቡ ሲሆን በመስከረም ወር አካባቢ የፕሬስ ህጉን ጨምሮ ማስተካከያ የተደረገላቸው ህጎች ይጸድቃሉ ተብሎም ይታሰባል፡፡

በዚያ ላይ ናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዴሞክራሲ የተባለው መቀመጫውን አሜሪካ ያደረገ ተቋም የኢትዮጵያን ሚዲያ ሪፎርም ለማገዝ ፍቃደኛ መሆኑን ገልጾ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ የዓለም የፕሬስ ቀንም አንድ የመወያያ መድረክ አዘጋጅቶ በሚዲያው ሪፎርም ላይ ምን ይደረግ ፣ ሚዲያው አሁን ከአለምአቀፉ ማበረሰብ የሚፈልገው ድጋፍ ምንድነው ፣ በቀጣይስ ምን ይደረግለት? የሚል ጥያቄ አንስቶ ውይይት አድርጓል፡፡

በሌላ በኩል ዩኔስኮ ያዘጋጀው ውይይት ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ አንጻራዊ የፕሬስ ነጻነት ለውጥ ቢኖርም አሁንም ግን የላቀ የሚዲያ ቀና ምልከታ አዝማሚያ ያንሳል ነው ያለው፡፡

በቅርቡ በማህበራዊ ድረገጾች የሚለቀቁ አሉታዊ መረጃዎችን ለመከላከል እና የጥላቻ ንግግርን የሚያስቀጣ ለማድረግ የጸደቀው የጥላቻ ንግግር አዋጅ በራሱ ሚዲያው ላይ አሳሪነት እና አዛገርነት ባህሪ ስላለው ቢቀር የሚል ነጥብም ተነስቶ ነበር፡፡ በዚህ በኩል ህግ እያሻሻሉ በዚያ በኩል ደግሞ ህግ እያወጡ ፕሬሱን ማሰር ተገቢ እንዳልሆነና መንግስት ለሚገጥሙ ችግሮች የህግ ማውጣት መፍትሄ ብቻ የሚወስድ መሆኑ ካለፈው አስተዳደር የሚለየው ነገር እንደሌለ ነው የተነገረው፡፡


በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ባለፈው ረቡዕ በተከበረው የፕሬስ ነጻነት ቀን ላይ የተጋበዙ እንግዶች የተናገሩት ደግሞ መገናኛ ብዙሃን እንዳይጠናከሩ በተለይም የህትመት ሚዲያው ከመስመር ሊያስወጣው የደረሰው የወረቀት ዋጋ መናር ላይ መንግስት ምላሽ መስጠት ያልፈለገው የተጠናከረ ፕሬስ እንዲኖር ፍላጎት ስለሌለው ነው የሚል ሃሳብም ተነስቷል፡፡ በተለይ ለውስኪ እና ቮድካ ከቀረጥ ነጻ ፍቃድ ሰጥቶ የጋዜጣ እና መጽሄት ወረቀት ላይ ታክስ መጣሉ ተገቢ አይደለም ተብሏል ተተችቷል፡፡ ይህ ባለበት ሁኔታ ስለፕሬስ ነጻነት ማሰብ አዳጋች እንደሆነ ነው ተደጋግሞ የተነገረው፡፡

### ነጻነት እና ሃይል

ሚዲያ ራሱን ለማስከበር የሚበቃ ሃይል ያለው ተቋም ነው፡፡ በብዙዎች ዘንድ የሚሰጠው ደረጃ የችላ ባይነት ቢሆንም በራሱ በሚፈጥረው ተጽዕኖ ግን አጀንዳ መሆን ይችላል፡፡ ሚዲያው በአዲስ መስመር ላይ ለመገኘት የጋራ ውይይት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በተባበረ ሃይል ጠንካራ አቋም በመያዝ የመገናኛ ብዙሃን ማህበር ወይም ካውንስል በማቋቋም ሙያው በተሻለ ደረጃ ላይ እንዲገኝ ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡ ከዚህ አንጻር የሚዲያ ካውንስሉ እና የሙያ ማህበራቱ ጉዳይም ተነስቷል፡፡ በተለይ በፌስቡክ የተበለጠ ሚዲያ የድካም እና ጫና ውጤት ነውና ራሱን አስከብሮ በመንግስትም የሚፈራ በህዝብም የሚታመን ሚዲያ ለመሆን ጠንካራ የመሰባሰቢያ መድረክ ያስፈልገዋል ነው የተባለው፡፡ ለምሳሌም ከተቋቋመ የሰነበተው የሚዲያ ካውንስል ከማህበራት ማደራጃ ህግ መካለስ ጋር ተያይዞ በይደር የኖረው ምክር ቤት ፍቃድ አግኝቷል፡፡ ብዙው ጋዜጠኛ በማይወክሉን ሰዎች ካውንስሉ ተመሰረተ ቢባልም ቢያንስ ተመስርቶ የማይወክሉ የተባሉትን መለወጥ ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ ካውንስሉ በቅርቡ የአባልነት ምዝገባ እንደሚያከናውን ከአስተባባሪዎቹ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ይህ ሲሆን ማህበራት ሲጠናከሩ እና ልክ እንደጋና እና ኬንያ ጠንካራ ካውንስል ሲኖር የሚዲያው ነጻነትም በዚያው መጠን ይከበራል፡፡

በዚሁ የዓለም ፕሬስ ነጻነት ቀን ላይ የቀረበና አፍሮባሮሜትር በተባለ ተቋም በ34 የአፍሪካ ሃገራት የተካሄደ አንድ ጥናት እንዳመለከተው በአፍሪካ ሃገራት ለመገናኛ ብዙሃን መብት እና ነጻነት ጥበቃ ድጋፍ ለማድረግ የሚፈልግ ማንም የለም፡፡ ይህ አስደንጋጭ ደጋፊ ማጣት መገናኛ ብዙሃን የራሳቸውን መብት ራሳቸው እንዲያስከብሩ መነሻ ምክንያት ይሆናቸዋልና በጉዳዩ ላይ በጽኑ ቢያስቡበት ይበጃል ነው የተባለው፡፡

# ሴቶች እና ዳግማይ ትንሣኤ



ፍቅርተ ተሾመ

### ቅዳሜ(ዛሬ) – ቅዱሳን አንስት ይባላል

ዳግማይ ትንሣኤ የሚከበረው የትንሳኤው ብስራት ላልፈሩት እንስቶች በመነገሩ እና ለሐዋርያት ድጋሚ መገለጡ አስፈላጊ በመሆኑ ክርስቶስ በድጋሚ በማወጁ ነው፡፡ በእስራኤላውያን ሥርዓት መሰረት ለሞተ ሰው በተቀበረ በማግስቱ ቤተሰብ አልያም የቅርብ ዘመዶች ወደ መቃብሩ በመሄድ ሽቶ እንደሚቀቡ ሁሉ ሁለቱ የክርስቶስ ተከታዮች ማርያም መቅደላዊት እና ማርያም ምንተሃፍረት ዮሃና እና ሰሎሜ ወደ መቃብሩ ሄደው እርገቱን ቀድመው ሰሙ፡፡ አመኑ፡፡ ለሃዋርያትም ሄደው ነገሩዋቸው፡፡

ቤተክርስቲያን ይህንን የብስራት ዜና አንድም እያለች አውዱን ታስረዳለች፡፡ ሴቶች ቀድመው መስማታቸው የሞቱን ዜና ቀድማ የሰማችው ሴት እንደመሆኗ የትንሳኤውንም ብስራት በመስማቷ ለካሳ ነው፤ አንድም ሴቶች ለመረጃ ባላቸው ቅርበት ተአማኒነት አላቸው በማለት እንደምታስተምር ሊቀ ጉባኤ ጌታሁን ድምፀ ያስረዳሉ፡፡

ሆኖም ሐዋርያት በነበረባቸው ፍርሃት የተነሳ ይህን የትንሣኤ ብስራት ለማየት ስላልታደሉ በተዘጋ ቤት ውስጥ ተገልጦ ታይቷቸዋል፡፡ ተሰብስበው በአንድነት የነበሩት በኂላ ፅርሃ ፅዮን ተብላ በተጠራችው በማርታ፣ በማርያም እና ማርቆስ እናት ቤት ሲሆን፤ ይህች ቤት ሐዋርያት እግራቸውን ታጥበው ክርስትናን የተነሱባት በኂላም መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉባት ቤት ነች፡፡ ጌታ ሲገለጥ ቅዱስ ቶማስ ለአገልግሎት ከተላከበት አልተመለሰምና ፤አላየሁም አላምንም በማለቱ ጌታ ለ፰ኛ ጊዜ ቶማስ ባለበት ተገልጾላቸዋል፡፡

ቀድሞ በብሉይ አንስት እርኩስ ሆነው በሚቆጠሩባት ጊዜ እንኳን የሙሴ እህት ማርያም የዝማሬውን አገልግሎት አጋፋሪ ሆና የምታመሰግን ነበረች፡፡ በብሉይ መፃሕፍትም እስከ አሁን ድረስ ለጸሎት አገልግሎት የሚውሉትን ዝማሬዎች የደረሱ እንስትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ቅድስት ዲቦራ፣ ነብይት ሀና በመገናኛው ደጃፍ ላይ የነበራቸው አገልግሎትም ይጠቀሳል፡፡

በሐዲስ ኪዳን ምስረታም ሊቀ ጉባኤ ጌታሁን “ሐዋርያት ያልገባቸውን እየጠየቁ ስርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንዲጻፍላቸው መጠየቃቸው ተሰሚነታቸውን ያሳያል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ትምህርተ ህቡዓት፣ ኪዳን እና ሌሎችም የእነርሱ የጥያቄ ፍሬዎች ናቸው” በማለት ይገልጻሉ፡፡

ይህ ሲሆን ታዲያ ሴቶች ከክህነት አገልግሎት ውጪ ናቸው፡፡ ይህም ስርዓት ከጌታ ከራሱ የመጣ እንጂ ሰዎች አላበጁትም፡፡ ይህ የሚና ልዩነት እንጂ የማበላለጥ ጉዳይ አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ጌታ ሐዋርያትን ከመጥራቱ በፊት ሴቶች አማኒዎች ነበሩት፤ ሆኖም እነርሱን ትቶ ወንዶችን መምረጡ የክህነትን ስርዓት ሲያበጅ ነው፡፡ ይህ ስርዓት ነው፡፡

በሀገራችን አልተለመደም እንጂ ይላሉ ሊቀ ጉባኤ



“በእህት አብያተ ክርስቲያናት የሚተገበረው የሴት ዲያቆናት አገልግሎት አለ፡፡ አገልግሎቱ እንደሌላው አገልግሎት ሁሉ የራሱ ሚናዎች አሉት፡፡ በእድሜዋ 60 የሞላት በምግባሯ የተመሰከረላት የተመረጠች ሴት መሆን ይኖርባታል፤ አገልግሎቷ በዋነኛነት ለአቅመ ሄዋን ደርሳ የምትጠመቅን ሴት አንድ ወንድ ካህን እንዳያጠምቅ እና እርሷ ስርዓቱን በአግባቡ በመማር የካህኑን እጅ ይዛ ካህኑ አይኑ ተጨፍኖ ታጠምቃለች” በማለት የዲያቆናይትን ሚና ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም አቃቢት በመሆን እና ሴቶች በምስጢር ሰዓት ማድረግ የሚገባቸውን ስርዓቶች ለሴቶች በሴቶች በኩል ሆና ታስተምራለች፡፡

ብሉይን ከሐዲስ በአንድነት አስታርቃ የምትመራው የኢ.ኦ.ተ.ቤተክርስቲያን በኖህ መርከብ ትመሰላለች፡፡ ኖህ በመርከቡ ወንዶችን በወንዶች ሴቶችን በሴቶች አድርጎ ክፉን ዘመን እንዳለፈ፤ ቤተ ክርስቲያንም ይህን ተከትላ የሴት ምዕመናንን እና የወንድ ምዕመናንን አቀማመጥ ለይታ ታስቀምጣለች፡፡

### ምርቃት

ከትንሳኤ በኃላ እስከ ዳግማይ ትንሳኤ ድረስ ያሉት ዕለታት ስያሜ ያላቸው ሲሆን፡-

ሰኞ- ማዕዶት ይባላል፡- ማዕዶት ማለት መሻገር፣ ማለፍ ማለት ነው፡፡ በዚህ ዕለት በፋሲካ በክርስቶስ ትንሣኤ ከድቅድቅ ጨለማ ወደ የሚደንቅ ብርሃን፣ ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከሲኦል ወደ ገነት፣ ከሃሳር ወደ ክብር መሻገራችንን እናስባለን፡፡

ማክሰኞ- ቶማስ ይባላል፡- በዚህ ዕለት ቶማስ ጌታን አይቶ ማመኑ፤ ጌታዬና አምላኬ ብሎ መመስከሩ ይዘከራል፡፡

ረቡዕ- አልአዛር ይባላል፡- በዚህ ዕለት ትንሣኤና ሕይወት የሆነው ጌታ ኢየሱስ አልአዛርን ከሞት እንዳስነሳው እናስባለን፡፡ ክርስቶስ የሞትን ስልጣን የሻረ የሕይወት ራስ፤ የመቃብርን ሥርዓት ያጠፋ ትንሣኤ፤ በድልም ያረገ ንጉሥ መሆኑን እንመሰክራለን፡፡

ሐሙስ- አዳም ሐሙስ ይባላል፡- በዚህ ዕለት ለአዳም የተሰጠው ተስፋ እና የተገባለት ኪዳን እንደተፈጸመ አዳምና ልጆቹን ነጻ እንደወጣን እናስባለን፡፡

ዓርብ- ቅድስት ቤተክርስቲያን ይባላል፡- በዚህ ዕለት ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ስለመመስረቷ ይሰበካል፡፡ ክርስቶስ ስለ እርሷ ራሱን አሳልፎ ሰጥቶ ቤዛ ሆኖ በደሙ አንጽቶ በትንሣኤው ድል ሰጥቶ እንዳከበራት ይነገራል፡ ፡ ቤተክርስቲያን ማለት ሕንፃውን ሳይሆን አማኞችን ነው፤ ክርስቶስ ለሕንፃ አልሞተምና፡፡

ቅዳሜ- ቅዱሳት አንስት ይባላል፡- በዚህ ዕለት ቅዱሳት አንስት የክርስቶስን አካል ሽቶ ለመቀባት ጨለማ አቋርጠው ወደ መቃብር መምጣታቸውና ትንሣኤውንም ቀድመው ማየታቸው ይሰበካል፡፡

እሁድ- ዳግም ትንሣኤ ይባላል፡- በዚህ ዕለት ክርስቶስ ለሦስተኛ ጊዜ ለደቀመዛሙርቱ ተገልጦ ሰላምን መስበኩ እና ሥልጣንን መስጠቱ ይሰበካል፡፡